# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት


# የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ያማርኛ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኩዋያ መገምገም፣ በአዋሳና አርባ-ምንጭ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

መሰለ መኩሪያ ወንድማገኘሁ

ግንቦት 1990

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

## የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ያማርኛ
## መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን
## ከስነ-ዘዴ አኩዋያ መገምገም፣
## በአዋሳና አርባ-ምንጭ መምህራን
## ማሠልጠኛ ተቋማት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

መሰለ መኩሪያ ወንድማገኘሁ

ግንቦት 1990

# በ1987 ዓ.ም. ለአንደኛ «ሳይክል» ትምህርት ለሚሰለጥኑ መምህራን የተዘጋጀው ያማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኳዋያ ሲገመገም፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር መምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ

አማርኛን በማስተማር የማስተርስ

ዲግሪ ማሟያ

በ

መሰለ መኩሪያ ወንድማገኘሁ

ግንቦት 1990

## ም ስ ጋ ና

የዚህን ጥናት ረቂቅ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ደጋግመው በማንበብ፣ በማስተካከልና ገንቢ አስተያየትም በመስጠት እስከመጨረሻው እርዳታ ላደረጉለት አማካሪው ለዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤል አጥኚው ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡

የየራሳቸው የሆነ ተደራራቢ ሥራ ቢኖራቸውም፣ ጥናቱ በዚህ መልኩ እንዲወጣ የሚያደርግ እጅግ ጠቃሚ ትምህርታዊ ምክር የሰጡትን ምሁራን በሙሉ፣ በተለይ አቶ ይልማ ከበደ፣ ዶ/ር ማረው ዘውዴና ዶ/ር ታደለ አዳሙን አጥኚው ከልብ ያመሰግናቸዋል፡፡

በተጨማሪም የዚህ ጥናት አቅራቢ የሚከተሉት ሰዎች ላደረጉለት ቀጥሎ ለተመለከተው ዕገዛ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርብላቸዋል፡፡

- የናሙና ተቋማት ርዕሰ-መምህራንና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለጥናቱ መደረግ ላሳዩት ትብብር፣
- አቶ መኩሪያ ወንድማገኘሁ፣ አቶ አማረ መኩሪያ፣ ወ/ሮ መሰለች ተሰማ፣ አቶ ዳምጠው ዳርዛና አቶ ዮናስ ካፌን ላደረጉት የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ፣
- ወ/ሮ ተስፋ ዋሲሁን በፅሑፍ ትየባ ረገድ፡፡

# ማውጫ


| ይዘት | ገጽ |
|---|---|
| **ክፍል አንድ፦ መግቢያ** | |
| 1.1. የጥናቱ ዳራ | 1 |
| 1.2. የጥናቱ ዓላማ | 4 |
| 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ | 4 |
| 1.4. የጥናቱ መጠነ-ርዕይ | 5 |
| 1.5. የመሠረታዊ ቃላትና ሀረጋት ብያኔና የምህፃረ-ቃላት ፍቺ | 6 |
| **ክፍል ሁለት፦ ክለሳ ድርሳናት** | |
| 2.1. የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ ሲታይ | |
| 2.1.1. የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ እሳቤ | 9 |
| 2.1.2. የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ምንነት | 9 |
| 2.1.3. የስነ-ዘዴ ምንነት | 11 |
| 2.2. የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኩዋያ መገምገም | |
| 2.2.1. የግምገማ እሳቤ | 11 |
| 2.2.2. የግምገማ መስኮች | 11 |
| 2.2.2.1. የመርሀ-ትምህርት ግምገማ | 11 |
| 2.2.2.2. የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ግምገማ | 12 |
| 2.2.3. የግምገማ ሞዴሎች | 12 |
| 2.2.4. የግምገማ ሞዴሎች አመራረጥ | 13 |
| 2.3. የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን የሚወስኑ ቀዳማይና ይዘታዊ ተላውጦዎች | 13 |
| 2.4. የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኩዋያ በክፍል ውስጥ ለመማር-ማስተማር ክንውንን የሚወስኑ ሂደታዊ ተላዎጦዎች | |
| 2.4.1. የመርሀ-ትምህርቱ የተመሠረተበት ትወራ-ነክ ስልት | 15 |

ይዘት ገጽ


2.4.2. የሠልጣኝ ተማሪው ሚና ---------- 16

2.4.3. የአሠልጣኝ መምህሩ ሚና ---------- 17

2.4.4. በክፍል ውስጥ የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች ያቀራረብ ስልት ---------- 19

2.4.5. የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሚና ---------- 20

2.5. የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚወስኑ ውጤታዊ ተሳውጦዎች ---------- 21

ክፍል ሶስት፣ የጥናቱ ዘዴ

3.1. ለጥናቱ የተመረጠው ሞዴል ---------- 22

3.2. የናሙና መረጣና የተሳታፊዎች አወሳሰድ ዘዴ ---------- 25

3.3. የመረጃ አሰባሰብና ስልቱ ---------- 26

3.3.1. መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና የአሰባሰብ ስልት ---------- 26

3.3.2. መረጃዎችን የማጠናቀርና የአተናተን ስልት ---------- 31

ክፍል አራት፣ የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

4.1. በመሣሪያዎቹ የቀረቡ መረጃዎች ---------- 35

4.1.1. በሰነድ ምርመራው ---------- 35

4.1.2. በክፍል ውስጥ ምልከታው ---------- 35

4.1.3. በመጠይቁ (የቃልና የፅሑፍ መጠይቅ) ---------- 36

4.2. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር ቅድመ-ሁኔታዎችን በተመለከተ

4.2.1. የመርሀ-ትምህርቱ አጠቃሳይ ገፅታ ---------- 39

4.2.2. የመማር-ማስተማር ሁኔታዎች ---------- 42

4.2.3. የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሁኔታ ---------- 45

**ይዘት** **ገጽ**


4.3. መርሀ-ትምህርቱን ስመተግበር የክፍል ውስጥ ተራክቦን በተመለከተ፣

4.3.1. ዝንባሌ፣ ፍላጎትና አመለካከት ---------------------------------- 46

4.3.2. የተማሪው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ -------------------------------- 47

4.3.3. የመምህሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ -------------------------------- 48

4.3.4. የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች ስልታዊ አቀራረብ -------- 50

4.3.5. የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሚና -------------------------------- 51

4.4. መርሀ-ትምህርቱን በመተግበር ከሚገኘው ውጤት አንጻር ሲታይ

4.4.1. የተማሪው በእስተሳሰቡና በአሠራሩ ለውጥ ማምጣትን
በተመለከተ ---------------------------------------------- 52

4.4.2. በተማሪዎቹ አንጻር የትምህርት ዓላማ ግብ መምታቱን
በተመለከተ ---------------------------------------------- 52

ክፍል አምስት፣ ማጠቃለያና አስተያየት

5.1. ማጠቃለያ፣ ---------------------------------------------- 59

5.2. አስተያየት፣ ---------------------------------------------- 62

ዋቢ ፅሑፎች ---------------------------------------------- 64

# የሠንጠረዦች ዝርዝር


| የሠንጠረዡ መለያ ቁጥር | አርዕስት | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | የመምህራን ዳራዊ መረጃ | 38 |
| 2 | የተማሪው አመለካከት መረጃ ጥንቅር | 46 |
| 3 | የተማሪው የክፍል ተሳትፎ መረጃ ጥንቅር | 47 |
| 4 | የመምህሩ የክፍል ተሳትፎ መረጃ ጥንቅር | 48 |
| 5 | የክፍል ውስጥ ክንውኖች መረጃ ጥንቅር | 50 |
| 6 | የተማሪው ትንበያ መረጃ ጥንቅር | 52 |
| 7 | የማዕከላዊ አዝማሚያ መለኪያ መረጃ | 54 |
| 8 | የዝምድና መለኪያ መረጃ | 55 |
| 9 | የብዙዮሽ መለኪያ መረጃ | 55 |
| 10 | የተማሪውን ውጤት ለመተንበይ የሚያስችሉ ተላውጦዎች መረጃ | 58 |

# የአባሪዎች ዝርዝር


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| የአባሪዎች መለያ | |
| አባሪ ሀ፣ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ---------------------------------- | 70 |
| አባሪ ለ፣ የስታክ ሞዴል መደቦች ዝርዝር መግለጫ ------------------------ | 83 |
| አባሪ ሐ፣ የተሳታፊ ተማሪዎች ዳራዊ መረጃ ---------------------------- | 84 |
| አባሪ መ፣ የተማሪው ቅድመ-ልምድና ድህረ-ልምድ መረጃ ---------------- | 87 |
| አባሪ ሠ፣ በሰነድ ምርመራ የትምህርት ዓላማና ይዘት ------------------- | 90 |
| አባሪ ረ፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ---------------------------- | 93 |
| አባሪ ሰ፣ የመጠይቅ (የቃልና የጽሑፍ) መረጃ ---------------------------- | 95 |
| አባሪ ሸ፣ ዕለታዊ የትምህርት ዝግጅት መረጃ ---------------------------- | 101 |

## አጠቃሉ (Abstract)


የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ1987 ዓ.ም ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ በትግበራ ላይ ያጋጠሙትን ችግሮች በማጥናት ውጤቱን ማመልከትና ከውጤቱ አንፃር መፍትሄ ሀሣቦችን መጠቆም ነው።

ለጥናቱ የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኩዋያ ለመገምገም የሚያስችል ተስማሚ የሆነ ሞዴል ተመርጧል። በሞዴሉ መሠረት ከደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር ከሚገኙት ሁለት የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ሶስት ክፍሎች በዕጣ ተወስደዋል። በነዚህ ክፍሎች የሚገኙት 132 ተማሪዎችና የሚያስተምሯቸው ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዳሉ ተነሙነዋል። 12 የትምህርት ባለሙያዎችም በመረጃ ሰጪነት በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርገዋል። ከዚያም መረጃ በሰነድ ምርመራ፣ በምልከታና በመጠይቅ (በቃልና በፅሑፍ መጠይቅ) ተሰብስቦ በገላጭ የምርምር ስልት ተተንትኗል።

በቀረበው መረጃ መሠረት በ1987 ዓ.ም. በተቋም ደረጃ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጀው መርሀ-ትምህርት በሁለቱ ተቋማት በተመረጡት ሶስት ክፍሎች በትክክል በሥራ ላይ ተግባራዊ አለመሆኑ ተረጋግጧል።

ከተሰበሰበው መረጃና ከተገኘው ውጤት አኩዋያ፣ ለመምህራን ማሠልጠኛ የሚዘጋጅ መርሀ-ትምህርት የአንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶችን መርሀ-ትምህርቶች መሠረት ማድረግ እንዳለበት፣ ከመተግበሩ በፊት የመማር-ማስተማር ሁኔታዎች መመቻቸት እንደሚኖርባቸው፣ የጊዜ ጥበት እንዳይኖር በአንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ተማሪው ቅኝት የሚያደርግበትና ለማስተማር ልምምድ የሚወጣበት ጊዜ በመርሀ-ትምህርቱ መካተትና በዕቅድ ደረጃ መያዝ እንዳለባቸውና አዘጋጁ ክፍል አፈፃፀሙን መከታተል እንደሚኖርበት አስተያየት ተሰጥቷል።

# ክፍል አንድ፣ መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ፣

በሀገራችን የመጀመሪያው መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም በ1936 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተቋቋመ:: ከ1945 ዓ.ም. ጀምሮ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የማቋቋሙ ሥራ በየአካባቢው በሠፊው ቀጥሎ አሁን የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ቁጥር 12 ደርሷል:: ከነዚህም ውስጥ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገባቸው የመምህራን ማሠልጠኛዎች ሁለቱ የአዋሳና የአርባ-ምንጭ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ሲሆኑ፤ የአዋሳው በ1969 ዓ.ም. ተቋቋመ፤ የአርባ-ምንጩም በ1980 ዓ.ም. (ት/ሚ 1986 ዓ.ም. ያገናዝቧል):: የመምህራን ማሠልጠኛው ሲቋቋም ዓላማው በአንደኛ ደረጃ (ከ1-6) ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራንን አሠልጥኖ ማስመረቅ ነበር:: ለዓላማው መሣካት ሲባል የተጠቀሱት ተቋማት ከ1936 እስከ 1987 ዓ.ም. 6ኛን፣ 8ኛን፣ 9ኛን፣ 10ኛን፣ 11ኛንና 12ኛን ክፍል ከጨረሱ ተማሪዎች መካከል በክፍል ፈተናቸው ከፍተኛ ውጤት ያገኙ፣ በጠባያቸው የተመሰገኑና ጤናማ የሆኑትን ቃለ-መጠይቅ እየተደረገላቸው በዕጩ መምህርነት ለሳምንታት (ከ4-6 ሳምንታት)፣ ለመንፈቅ፣ ለአንድ፣ ለሁለት፣ ለሶስትና ለአራት ዓመት በተለያዩ ጊዜያት አሰልጥነው አስመርቀዋል:: ከ1988 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ አንደኛ ሳይክል (ከ1-4) ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራንን 12ኛን ክፍል ከጨረሱት ተማሪዎች መካከል እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩ የመመልመያ መሥፈርቶችን በመጠቀም መልምለው እስካሁን ለአንድ ዓመት እያሰለጠኑ ናቸው (ፓንክረስት 1955፣ ት/ሚ 1965 ዓ.ም.፣ ሥ/ት 1987 ዓ.ም.) እና ጌታቸው 1986 ዓ.ም ይመለከቷል)::

የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ማሠልጠን ሲጀምር በየትምህርት ዓይነቱ መርሀ-ትምህርት ተዘጋጅቶለታል:: አዘገጃጀቱም ከስነ-ዘዴው በስተቀር ከሁለተኛ ደረጃ መርሀ-ትምህርት ጋር የተዛመደ ነበር:: በየመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት የአማርኛ ቋንቋም በትምህርት ዓይነትነት ይሰጥ ስለነበር እንደሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች መርሀ-ትምህርቱ በውጭ ሀገር ሰዎች እርዳታ ከሁለተኛ ደረጃ የቋንቋ መርሀ-ትምህርት በቀጥታ ተቀድቶ ስነ-ዘዴው እንደታከለበት 'ይነገራል' (የት/ሚ ሠነድ 1985 ዓ.ም. ያገናዝቧል):: ይህም መርሀ-ትምህርት ከተነደፈበት ጊዜ አንስቶ በተለያየ ወቅት የየሥርዓቱን

ርዕዮተ-ዓለም መሠረት በማድረግ ከ1947-1971 ዓ.ም. በተከታታይ ተሻሽሏል። ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው መርሀ-ትምህርት ግን በአዲስ መልክ በ1987 ዓ.ም. የተዘጋጀው ነው። ይህም የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት መሠረት ያደረገው ፍልስፍና ተማሪ መራሽ፣ ተግባቦትንና ዲሞክራሲን ሲሆን፤ አሁን በተግባር እየተተረጎመ ያለ ነው ቤንደር (1976)፣ ት/ሚ (1986 ዓ.ም.) እና ሥ/ት (1987 ዓ.ም.) ይመለከቷል።

ይህ ጥናት የሚያተኩረው አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ከሚሰጥባቸው አካባቢዎች ባንዱ (በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር በሚገኙት ሁለት መምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት) ላይ ሲሆን፣ አጥኚው በክልሉ በሥራ ቆይታው አዲሱን ያማርኛ ቋንቋን መርሀ-ትምህርት ከመተግበር አንፃር በርካታ ችግሮችን ለመመልከት ችሏል።

ለጥናቱ መነሻ መረጃዎች ለመሻትም ቃኚ ጥናት ተካሂዷል። በዚህም አሰሳ በምልከታ በቃለ-መጠይቆችና በፅሑፍ መጠይቆች አማካኝነት ከተማሪው፣ ከመምህራንና ከክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ከተሰበሰቡት መረጃዎች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚከተሉት ችግሮች እንዳሉት የሚጠቁሙ ሀሣቦችን ለመቃኘት ተችሏል። እነሱም፤

I መርሀ-ትምህርቱን በተመለከተ፣

ሀ. መርሀ-ትምህርቱ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማር ተማሪ የማይመጥን መስሎ መታየቱ፣

ለ. መርሀ-ትምህርቱ ለዓመት የተዘጋጀ ሆኖ ሳለ ግን ለግማሽ ዓመት የሚሰጥ ኮርስ በመሆኑ የጊዜ እጥረት ሲኖር መቻሉ፣

II. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር ቅድመ-ሁኔታዎችን በተመለከተ፣

ሀ. የተማሪው ምልመላ ወጥነት እንደሌለው መታየቱ፣
ለ. የመምህራን ምደባ በፍላጎትና በብቃት ላይ የተመሠረተ አለመሆኑ፣
ሐ. መምህራን ስለ አዲሱ መርሀ-ትምህርት የተደረገላቸው ገለፃም ሆነ ማስተዋወቂያ አለመኖሩ፣

III. መርሀ-ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር የክፍል ውስጥ ተራክቦን በተመለከተ፣

ሀ. በክፍል ውስጥ ከመምህሩ በስተቀር ከተማሪው የጎላ ተሳትፎ አለመታየቱ፣
ለ. በክፍል ውስጥ ድርጊቶች፣ ክንውኖችና ልምምዶች በስልት አለመቀረባቸው፣

IV. የመርሀ-ግብሩ (የመርሀ-ትምህርቱ ትግበራ ሂደት) ግብን በተመለከተ፣

ለብዛኛው ሠልጣኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ስመሆን ስለመፈለጉ፤ ሴላ ሥራ ሥሳጣ ብቻ ያለ ዝንባሌው መምህራን ማሠልጠኛው የገባበት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ችግሮች አጥኚው በተቋሙ ባደረገው ቆይታ የተገኙና ቅኝታዊ ጥናት በማድረግ የተደረሰባቸው ናቸው::

በተጨማሪ በሀገር ውስጥም የተደረጉ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ሥራዎች ተዳስሰዋል:: ሥራዎቹም የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት በመርሀ-ትምህርቱ ሁኔታ፣ በቅድመ-ሁኔታዎች፣ በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎችና በመርሀ-ግብሩ ውጤት አንፃር ችግሮች እንዳሉ ይጠቁማሉ (ኃይሉ 1991፣ መለሰ 1992 እና ጌታቸው 1994) ::

ከሀገር ውጭ ያሉ የመስኩ ፀሐፍት ደግሞ የመርሀ-ትምህርቱ ሁኔታ፣ መርሀ-ትምህርቱ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ያሉ ቅድመ-ሁኔታዎች (ቅድመ-ዝግጅቶች) በክፍል ውስጥ ተራክቦ የተማሪው፣ የመምህሩና የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሚና፣ የድርጊቶች የክንውኖችና የልምምዶች የአቀራረብ ስልትና ከመርሀ-ግብሩ የሚገኘው ውጤት የመርሀ-ትምህርቱን የትግበራ ሂደት የሚወስኑ ተላውጦዎች (ተለዋዋጭ ምክንያቶች) ናቸው ብለው እምነታቸውን ይህንን በተመለከተ ፓይኔ (1974)፣ ለዊ (1977)፣ ሀወስ (1979)፣ ፕራት (1980)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981)፣ ብራንድት (1981)፣ ሆልት (1983)፣ ዩረቡ (1985)፣ ኦሊቫር (1988)፣ ኦርንስቴይን (1988)፣ ማርሽ (1991) እና ፉላን (1992) በቂ ገለፃ አቅርበዋል::

ስለዚህ አንድ የቋንቋ መምህር የሚያስተምረው እፍ የፈታበትን ቋንቋ ባይሆንም በቂ የቋንቋ ክሂሎችና የማስተማሪያ ስነ-ዘዴው ዕውቀት ያለው መሆን እንዳለበት ሀርመር (1991) ያስገነዝባሉ:: የዚህ ጥናት አቅራቢም ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ችግሮች በመነሳት ብቃት ያላቸውን የአንደኛ ሳይክል (1-4) ተማሪዎችን አማርኛ የሚያስተምሩ መምህራንን ለማፍራት የቋንቋውን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት የሚወስኑ ነገሮችንና ችግሮችን በመረጃ ምንጮች ታግዞ በመለየት ተገቢውን መፍትሄ ለመጠቆም ጥናቱን ለማካሄድ ወስኗል::

## 1.2. <u>የጥናቱ ዓላማ፣</u>

የዚህ ጥናት ዓይነተኛ ዓላማ ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የተዘጋጀው ያማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት በሥራ ላይ (ከስነ-ዘዴው አኩዋያ በትግበራ ላይ) ያጋጠሙትን ችግሮች በማጥናት ውጤቱን ማመልከትና ከውጤቱ አንፃር መፍትሄ ሀሣቦችን ለመጠቆም ሲሆን፤ እግረመንገዱን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል፤

### 1.2.1. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር ቅድመ-ሁኔታዎችን በተመለከተ፣

1.2.1.1. መርሀ-ትምህርቱ ግልፅነት አለው ወይ? ለመተግበርስ አያስቸግርም ወይ?

1.2.1.2. የመማር-ማስተማር ሁኔታዎች ተመቻችተዋል ወይ?

1.2.1.3. የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል ወይ? ከተዘጋጁስ ባግባቡ ተሰራጭተዋል ወይ?

### 1.2.2. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር የክፍል ውስጥ ተራክቦን በተመለከተ፣

1.2.2.1. በመርሀ-ግብሩ ላይ የተማሪውና የመምህሩ አመለካከት አዎንታዊ ነው?

1.2.2.2. ተማሪው ሚናውን አውቆ ለመማር ተዘጋጅቷል?

1.2.2.3. መምህሩ ሚናውን አውቆ ለማስተማር ተዘጋጅቷል?

1.2.2.4. የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች አቀራረብ ስልታዊ ነው?

1.2.2.5. የቀረቡት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተስማሚ ናቸው?

### 1.2.3. መርሀ-ትምህርቱን በመተግበር ከሚገኘው ውጤት አንፃር ሲታይ፣

1.2.3.1. በተማሪው ላይ የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ ታይቷል?

1.2.3.2. በመርሀ-ትምህርቱ የተነደፈው ዓላማ ተግባራዊ ሆኗል?

## 1.3. <u>የጥናቱ ጠቀሜታ፣</u>

የጥናቱ ውጤት ተጠቃሎ ሲታወቅ በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ደረጃ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፤

### 1.3.1. አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ሠልጣኝ ተማሪዎች የሚሆን መርሀ-ትምህርትን ለማዘጋጀት የሚያስችል ሀሣብ ለመስጠት፣

1.3.2. የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከመተግበሩ በፊት የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች የሚመቻቹበትን መንገድ ለማመላከት፣

1.3.3. የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የክፍል ውስጥ ተራክቦን በምንና እንዴት መሆን እንዳለበት ሀሣብ ለማቅረብ፣

1.3.4. የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትን በመተግበር ሂደት በክፍል ውስጥ የድርጊቶችን፣ የክንውኖችንና የዕምምዶችን ሥርዓት ለማስያዝ የሚያስችል ስልት ለማመላከትና

1.3.5. የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትን ለመተግበር ተስማሚ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ለመጠቀም::

## 1.4. የጥናቱ መጠነ-ርዕይ (Scope)፣

ይህ ጥናት ትኩረቱ በሀገራችን ከሚገኙት 12 የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር በሚገኙት ሁለት ተቋማት፣ (በአዋሳና በአርባ-ምንጭ መምህራን ማሠልጠኛዎች) ላይ ነው::

በነዚህ ማሠልጠኛዎች የጥናቱ ተሣታፊዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ሠልጣኝ ተማሪዎችና የሚያስተምሯቸው አሠልጣኝ መምህራን ናቸው:: አጥኚው በሠራበትና ወደፊትም በሚሠራበት አካባቢ ጥናት ማድረጉ (as action research) ለመርሀ-ትምህርቱ መሻሻል አስተዋፅኦ አለው ብሎ ስለሚያምን ካለው ጊዜ፣ ገንዘብና ማቴሪያል ሁኔታ አንፃር እነዚህን ሁለት ተቋማት ሊመርጥ ችሏል::

ጥናቱ በ1987 ዓ/ም ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚገመግም በመሆኑ ትኩረቱ፣

I. መርሀ-ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር ካሉ ቅድመ-ሁኔታዎች፣

II. መርሀ-ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር የክፍል ውስጥ ተራክቦንና

III. ከመርሀ-ትምህርቱ ዓላማ አንፃር ከመርሀ-ግብሩ በሚገኘው ውጤት ላይ ያረፈ ነው:: በተጨማሪም የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት በዚህ ጥናት እንደመንግሥት ሠነድነት፣ እንደማስተማሪያ መሣሪያነትና እንደመረጃ ምንጭነት ግልጋሎት ይሰጣል::

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ መተግበር አለመተግበሩን (በሥራ ላይ መዋል አለመዋሉን) እና ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ብቻ ይገመግማል::

## 1.5. የመሠረታዊ ቃላትና ሐረጋት ብያኔና የምህፃረ-ቃላት ፍቺ፣

### ሀ. የቃላትና የሐረጋት ብያኔ፣

1. መርሀ-ትምህርት (Syllabus/Curriculum) - ለአንድ የትምህርት ዓይነትና የክፍል ደረጃ የተመጠኑ ዓላማዎችን፣ ይዘቶችን፣ ክንውኖችን (ስነ-ዘዴዎችን)፣ የክፍለ-ጊዜያት መጠንን፣ ተመጣጣኝ የማስተማሪያ መሣሪያዎችንና የግምገማ ስልቶችን የሚጠቁም የመንግሥት ሠነድና የማስተማሪያ መሣሪያ ነው::

2. ሞዴል (model) - አጠቃላይ የሆነ፣ አንድ የተወሰነ የሥራ ዕቅድን ስመተግበር መንገድ (ስልት) የሚጠቁምና ችግር ስመፍታት የሚያስችል አስረጅ ወይም ምሳሌያዊ አቀራረብ (pattern, paradigm or example) ነው::

3. ትግበራ (implementation) - አንድ ሲከወን የተዘጋጀ መርሀ-ግብር ወይም ዕቅድ የታስመስትን ግብ ስመድረስ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ተመቻችተውስት በሥራ ሳይ መዋሉ የሚረጋገጥበት ሂደት ነው::

4. ስነ-ዘዴ (methodology) - ትወራዊ መሠረት ያስው፣ በክፍል ውስጥ መምህሩ ስተማሪው ሁስተኛ ቋንቋን ትምህርት በማስተማሪያ መሣሪያዎች አማካኝነት በሥርዓት ሥነ-ትምህርታዊ በሆነ መንገድ (Pedagogically) በተግባር የሚያሳይበት ሂደት ነው::

5. የስነ-ዘዴ ዘርፎች (Elements of method) - በመማር-ማስተማር ሂደት በማንኛውም የስነ-ዘዴ ዓይነት (ስምሳሌ:- ተፈጥሮአዊ ስነ-ዘዴ፣ ተግባቦታዊ ስነ-ዘዴ ወዘተ.) ሁሉ ሲገኙ የሚችሉና የአንድ ስነ-ዘዴ አስፈላጊ የሆኑ ትወራዊና ተግባራዊ ክፍሎች ናቸው::

6. ቀዳማይ ተሳውጦዎች/ተስዋዋጮች (Presage Variables) - እነዚህ በመምህሩ አንፃር የሚታዩና በስነ-ዘዴ ሳይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ሲሆኑ፤ የመምህሩን ቅድመ-ሥራ ልምዱን፣ ዕውቀቱን፣ ባሕርይውን፣ አመለካከቱንና ስብዕናውን ያካትታሉ::

7. ይዘታዊ ተሳውጦዎች (Context Variables) - ከተማሪው አንፃር የሚታዩና በስነ-ዘዴ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ሲሆኑ የተማሪውን ቅድመ-ሥልጠና ልምዱን፣ ባሕርይውን፣ ዝንባሌውንና አመለካከቱን ያጠቃልላሉ::

8. ሂደታዊ ተሳውጦዎች (Process Variables) - በመምህሩና በተማሪው የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በማስተማሪያ መሣሪያዎች አማካኝነት በክፍል ውስጥ በሚደረጉ ተራክቦዎች (interactions) ወይም መስተጋብራዊ ሂደቶች (transactions) ላይ የሚያተኩሩና ስነ-ዘዴን የሚወስኑ ተሳውጦዎች ሲሆኑ፤ የድርጊቶችን፣ የክንውኖችንና የልምምዶችን ስልታዊ አቀራረብ ሁሉ ይይዛሉ::

9. ውጤታዊ ተሳውጦዎች (Product Variables) - እነዚህ ደግሞ በአንድ ጊዜ (ወዲያውኑ) እና ረዘም ባለ ጊዜ በተማሪው ላይ በሚታዩ ወይም መታየት ይችላሉ የሚባሉ የባሕርይ ለውጦችን ያካትታሉ:: በዚህ በዓላማው አንፃር ሲከሰቱ የሚችሉ ባሕርያት ስምሳሌ:- የተማሪው የወጣትነት ስብዕና፣ ቶሎ ሥራ ይዞ ራስን የመቻል ፍላጎት፣ በሙያው ላይ ያለው አመለካከትና ዝንባሌ ወዘተ. ስለሚታዩ በስነ-ዘዴ ላይ ተፅዕኖ አላቸው::

10. ቀዳማይና ይዘታዊ ተሳውጦዎች (Presages or inputs and Contexts) የተማሪውንና የመምህሩን ቅድመ-ልምምድ፣ ባሕርይ፣ ስብዕና፣ ዝንባሌ፣ ችሎታ፣ አመለካከት፣ በጠቅላላው ዳራዊ መረጃዎችን የሚያጠቃልሉና ስሥልጠናው ቅድመ-ዝግጅት (antecedent) የተመቻቸ ድባብ የሚፈጥሩ ነገሮችንና ሁኔታዎችን የሚያካትቱ፤ ስነ-ዘዴን የሚወስኑ ተሳውጦዎች ናቸው::

## ለ. የምህፃረ-ቃላት ውሣኔ፣

1. የደ. ኢ. ሕ. ክ. መ. = የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር
2. የአዋ. መም. ማ. ተ. = የአዋሳ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም
3. የአርባ-ም. መም. ማ. ተ. = የአርባ-ምንጭ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም
4. የት. መ. ማ. ማ. ድ. = የትምህርት መሣሪያዎች ማደራጃና ማከፋፈያ ድርጅት
5. የሥ. ት. ዝ. ጥ. ም. ተ. = የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም
6. የድ. ክ. ል. አ. ስ. = የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች አቀራረብ ስልት

7. የ12ኛ ክ. መ. ፈ. = የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና
8. በኢ. ዘ. አ. = በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር
9. በኤ. ዘ. አ. = በኤውሮጳ ዘመን አቆጣጠር
10. የሥ. ት. ዝ. = የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት
11. የመ. ት. ት. = የመርሀ-ትምህርት ትግበራ
12. የመ. ማ. ሂ. = የመማር-ማስተማር ሂደት
13. ቅ. ሥ. ል. = ቅድመ-ሥልጠና ልምድ
14. ድ. ሥ. ል. = ድህረ-ሥልጠና ልምድ
15. ት. ክ. = ትምህርት - ክፍል (Department)
16. ት. ሚ. = ትምህርት ሚኒስቴር
17. ማ. ሰ. = ማህበረ-ሰብ
18. ብ. ሰ. = ብሔረ-ሰብ
19. ክ. ጊ. = ክፍለ-ጊዜ
20. ዓ. ም. = ምህፃረ-ቃሉ ዓመተ-ምህረትን የሚያመላክት ሲሆን፣ በዚህ ጥናት ዘመናቱ ዓ.ም. የሚል መግለጫ ከተከተላቸው የኢ/ዘ/አቆጣጠርን፣ ካልተከተላቸው ደግሞ በኤ/ዘ/አቆጣጠርን እንዲጠቁሙ ተደርገው ተወስደዋል::

<u>ምሳሌ</u>:- አበበ (1986 ዓ.ም. : 24) - በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የቀረበ::

ስታክ (1967:533) - በኤውሮጳ ዘመን አቆጣጠር የቀረበ::

# ክፍል ሁለት፣ ክለሳ ድርሳናት

## ፪.1. የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ ሲታይ፣

### ፪.1.1. የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ አሳቤ፣

አንድ፣ አዲስ የተነደፈም ሆነ ተሻሽሎ የቀረበ መርሀ-ትምህርት፣ በተዘጋጁለት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ታግዞ በመርሀ-ግብሩ፣ በተማሪውና በመምህሩ መካከል በሚደረገው የክፍል ውስጥ ተራክቦ ዕውን ሲሆን የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ይባላል ብለው ለዊ (1977:22)፣ ሀወስ (1979:118)፣ ፐራት (1980:343፣ 425፣ 457)፣ ኦሊቫ (1988:115)፣ ጆንሰን (1989:36)፣ ሜጀር (1991:167)፣ ፉላን (1992:37) እና ፓስነር (1992:186) ያምናሉ::

ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:9-10)፣ ኑናን (1988:122)፣ ጃኮብሰን (1989:10፣ 134) እና ማርሽ (1991:27) የመርሀ-ትምህርት ትግበራ በመማር-ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ላይ የሚያተኩር ሂደት በመሆኑ ስነ-ዘዴ ነው ብለው ይፈርጁታል:: ሪቻርድስና ሮጀርስ (1982:153)፣ (1985:16-17)፣ (1986:15)፣ ሪቻርድስ (1990:11) እና ብራውን (1994:159) ስለ ስነ-ዘዴ የሚሰጡት ሀሣብ ከዚህ ትርጉም ጋር ተቀራራቢነት አለው::

የመስኩ ፀሐፍት ሀሣብ ሲጠቃለል፣ በመማር-ማስተማር ሂደቱ በአዲስ መልክ የተዘጋጀ መርሀ-ትምህርት በክፍል ውስጥ በሥራ ላይ መዋል ከቻለ የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ይባላል:: መርሀ-ትምህርቱ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ መሆን የሚችለውም በማስተማሪያ መሣሪያዎች አማካኝነት በመምህሩና በተማሪው መካከል በሚደረጉት እንቅስቃሴዎችና መስተጋብራዊ ሂደቶች ነው:: ይህ ሂደት ደግሞ የመማር-ማስተማር ስልት በመሆኑ ስነ-ዘዴ ሊባል ይችላል:: በዚህ አካሄድ የመርሀ-ትምህርት ትግበራ የክፍል ውስጥ የማስተማር ሂደት ከሆነ፣ በክፍል ውስጥ የማስተማር ሂደት ደግሞ ስነ-ዘዴ ከተባለ የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ስነ-ዘዴ ሊሆን ይችላል የሚል ይሆናል::

### ፪.1.2. የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ምንነት፣

የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ማለት አንድ በአዲስ መልክ የተዘጋጀ ወይም የተሻሻለ መርሀ-ትምህርት በትግበራው ሂደት ችግሮች ቢኖሩም ባይኖሩም በራሱ

አደረጃጀት ቅደም ተከተል በመጠቀም፣ ለያንዳንዱ የአደረጃጀት ደረጃ ትኩረት በመስጠት በሥሩ የተካተቱት ይዘቶች፣ የመማር-ልምዶችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች በአግባቡ ተሠራጭተው በክፍል ውስጥ ድርጊቶችን የመከወንና የመለማመድ ሂደት መሆኑን ሀወስ (1979:194) እና ፉላን (1992:65) ያረጋግጣሉ::

እንደነዚህ ተመራማሪዎች አባባል፣ አንድ መርሀ-ትምህርት በትግበራው ሂደት ችግር ኖረም አልኖረም በዝግጅት ወቅት ያለፉቸውን ደረጃዎች በሥርዓት በመጠበቅና በመከተል የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎች ከተከወኑ ሂደቱ የመርሀ-ትምህርት ትግበራ መሆኑን ያስገነዝበናል::

### ፪.፩.፫. የስነ-ዘዴ ምንነት፣

ትወራዊ መሠረት ያለው፣ መምህሩ ለተማሪው የሁለተኛ ቋንቋን ትምህርት በማስተማሪያ መሣሪያዎች አማካኝነት በሥርዓት ተግባራዊ የሚያደርግበት የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ስነ-ዘዴ ይባላል ብለው ሪቻርድስና ሮጀርስ (1985:10፣ 11፣ 32)፣ ሪቻርድስ (1990:11) እና ብራውን (1994:159) ያምናሉ::

እነሪቻርድስና ሮጀርስ (1982፣ 1985፣ 1986) የስነ-ዘዴን ትርጉም የሚወስኑ ሶስት ፍሬነገሮች (Elements):- ትወራ-ነክ ስልት (approach)፣ ንድፈ-ትምህርት (design) እና ስልተ-ትግበራ (Procedure) ናቸው ሲሉ ሪቻርድስ (1990:11) ደግሞ ንዑስ ዘርፎችንም በማካተት አሻሽለው ቁጥራቸውን ወደ አምስት ከፍ በማድረግ እንደሚከተለው ያቀርቧቸዋል:: እነዚህም:-

ሀ. መርሀ-ትምህርቱ መሠረት ያደረገው ትወራ-ነክ ስልት ወይም ፍልስፍና፣
ለ. በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት የተማሪው ሚና፣
ሐ. በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት የመምህሩ ሚና፣
መ. በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት በክፍል ውስጥ የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች ያቀራረብ ስልት (ስልተ-ትግበራ) እና
ረ. በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሚና ናቸው:: እነዚህ የስነ-ዘዴን ብያኔ ከመወሰናቸውም በላይ በተለይ መምህራንን በማሠልጠን ሂደት አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልምዶችን ለመፈተሽ መሠረታዊ የሆኑ የስነ-ዘዴ ዘርፎች ናቸው ብለው ሪቻርድስ (1990:11-15) ያምናሉ:: ዝርዝር ይዘታቸው በዚሁ ክፍል በ2.4 የሚቀርብ ይሆናል::

## ፪.፪. የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኳዋያ መገምገም፣

### ፪.፪.፩. የግምገማ እሳቤ፣

በትምህርት ነክ ጉዳዮች ላይ በሥርዓት በትክክለኛ ምንጮች መረጃዎችን ሰብስቦና አቅርቦ በመዳኘት ውሳኔ መስጠት ግምገማ ይባላል ብለው የሙያው ጠበብት ያምናሉ:: ግሬስማን (1973:9)፣ ስታፍልቢም (1973:21)፣ ፕሮቨስ (1973:49)፣ ሀሞንድ (1973:62)፣ ዶል (1977:361-363)፣ ጉባ (1981:35)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:316)፣ ጆርዳን (1983:IV)፣ ክሮንባህ (1983:101-102)፣ ኦርንስቴይን (1988:250-251)፣ ኦሊቫ (1988:463)፣ ሪቻርድስና ሮጀርስ (1986:158) እና ዋላስ (1991:42)::

በትምህርት መስክ ሁለት የግምገማ ዓይነቶች ሂደታዊ (formative) እና አጠቃላይ (Summative) በመባል ይታወቃሉ:: የመጀመሪያው የአንድን መርሀ-ግብር የቀን ተቀን ድርጊቶችና ክንውኖች የሚከታተልና ውሣኔ የሚሰጥ የአጭር ጊዜ ግምገማ ሲሆን፤ ሁለተኛው በመርሀ-ግብሩ መጨረሻ የሚደረግና አጠቃላይነት ያለው የግምገማ ዓይነት ነው ይላሉ ዶል (1977:49)፣ ስተንሀውስ (1975:104)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:317-318) እና ኦርንስቴይን (1988:255)::

### ፪.፪.፪. የግምገማ መልኮች፣

ግምገማ የመርሀ-ትምህርትና የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ግምገማ በመባል የሚታወቁ ሁለት መልኮች አሉት:: እነዚህም በግምገማ ሚናዎችና በውሣኔ ዓይነቶች ተፅዕኖ ይደረግባቸዋል ብለው ለዊ (1977:27-28)፣ ስተንሀውስ (1975:98)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:317)፣ ማደውስ (1983:102)፣ ኦርንስቴይን (1988:249-255) እና ፓስነር (1992:232) እምነታቸውን ይገልፃሉ:: ቀጥለን እያንዳንዱን የግምገማ መልክ እናያለን::

#### ፪.፪.፪.፩. የመርሀ-ትምህርት ግምገማ፣

በመርሀ-ትምህርቱ አጠቃላይ ባሕርይ ላይ ብቻ የሚያተኩር ወይም ከመርሀ-ትምህርቱ ወጣ ብሎ የመርሀ-ግብሩን ሂደት በየደረጃው የማይዳስስ፣ ረጅም ጊዜ (longterm) የሚፈጅና አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት ከተቀመጡበት ሳይንቀሳቀሱ የሚገመግሙት ("arm-chair" ) የግምገማ መልክ የመርሀ-ትምህርት ግምገማ ይባላል

ብለው ኦርንስቴይን (1988:250) ያምናሉ:: ዶል (1977:364) ደግሞ በመጠን ላይ የሚያተኩር (quantitative) የመርሀ-ትምህርት ግምገማ ነው ብለው ስለሚፈርጁት «ጫካውን» ("the whole forest") እንደመገምገም ይቆጠራል በማለት የመርሀ-ትምህርት ግምገማን እሳቤ ይገልፃሉ::

እንደ ጠበብቱ፣ የመርሀ-ትምህርት ግምገማ ማለት በመርሀ-ግብር አጠቃላይ ባሕርይ ላይ ያተኮረ፣ ጊዜ ቢወስድም የማያስቸግርና ዓይነታዊ ሳይሆን መጠናዊ መሣሪያን በመጠቀም ከውጤት ላይ የሚደርስ የግምገማ መልክ መሆኑን ያመላክታል::

### 2.2.2.2. የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ግምገማ፣

በመርሀ-ትምህርት መዋቅሮች ላይ ትኩረት አድርጎ የያንዳንዱን መዋቅር ደረጃ ለአጭር ጊዜ (short term) የሚዳሰስ፣ የሚነበቡ ጥያቄዎች ሁሉ በድርጊትና በክንውን የታጀቡና በመማር-ማስተማር ሂደት በተለይ በክፍል ውስጥ በተማሪውና በመምህሩ መካከል በማስተማሪያ መሣሪያዎች አማካኝነት ያለውን ተራክቦና መስተጋብራዊ ሂደት ተከታትሎ የሚፈትሽ የግምገማ መልክ የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ግምገማ ይባላል በማለት ለዊ (1977:5፣ 70፣ 128)፣ ኢቫንስ (1977:79)፣ በቸር (1978:137-141)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:350)፣ ኦሊቫ (1988:463፣ 483)፣ ኦርንስቴይን (1988:250-251) እና ፓስነር (1992:237) ይገልፁታል:: በተጨማሪም ሲያብራሩ ይህ የግምገማ መልክ እንደመሣሪያ የሚያገለግል ("Instrumental") ወይም ግዴታና ክፊያ የሌለው ("Pay off) ከመሆኑም በላይ በባሕርይው ከሂደታዊ የግምገማ ዓይነት ጋር ተቀራራቢነት ቢኖረውም ሁለቱንም የግምገማ ዓይነቶች ይጠቀማል ይላሉ:: ዶል (1977:367) የግምገማ መልኩ በጥራት ላይ የሚያተኩር (qualitative) ግምገማ ነው በማለት እምነታቸውን ይገልፃሉ::

የመስኩን ምሁራን ሀሣብ ስናጠቃልል፣ የመርሀ-ትምህርትና የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ግምገማ ተደጋጋፊነት ቢኖራቸውም በሚናቸውና በውሣኔ አሰጣጣቸው የሚለያዩ መሆናቸውን ያመላክተናል::

### 2.2.3. የግምገማ ሞዴሎች፣

የተለያዩ ሞዴሎች ለመርሀ-ትምህርት ዝግጅት እንዳሉ ሁሉ ለመርሀ-ትምህርት ግምገማም አሉት:: እነዚህ ሞዴሎች እንደፈጣሪዎቻቸው እምነትና አመለካከት የተለያዩ ናቸው:: ቢለያዩም እርስበርሳቸው ይደጋገፋሉ:: በትምህርት መስክ አንዱ ካንዱ

ስለማይበልጥ እያንዳንዱ ሞዴል በራሱ ምሉዕ ነው። ሆኖም በትምህርት ባለሙያዎች ዕውቅናን ያተረፉ ሶስት ሞዴሎች፣ ሀ. ባሕርይንና ዓላማን መሠረት ያደረገ ሞዴል (behavioural objective model) - በታይለር (1942) የተቀረፀና በተማሪው የትምህርት ቅስሞሽ ላይ ትኩረት የሚያደርግ፣ ለ. ሂደታዊ ሞዴል (the process model) - በስተንሀውስ (1975) የተቀረፀና ድርጊትንና ክንውንን ወይም ተራክቦንና መስተጋብርን አበክሮ የሚያይና ሐ. ሁኔታዊ ሞዴል (situational or research based model) - በሽልበክ (1975) የተቀረፀና በሥራ አካባቢ ሁኔታዎች (Work environment) የሚያተኩር እንደሆነ ዶል (1977:375-382)፣ ለዊ (1977:10-13)፣ ሳሊያ-ባኦ (1978:62)፣ ስክርቭን (1981:98)፣ ማዶውስ (1983:45-48)፣ ጉባ (1981:1-38)፣ ሶይለርና ጓደኞቹ (1981:319-332) እና ኦሊቫ (1988:375፣ 468) ያስገነዝቡናል።

### 2.2.4. <u>የግምገማ ሞዴሎች ስመራረጥ፣</u>

አንዳንድ ሞዴሎች ቀላልና ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ። ሲቀረፁም እያንዳንዳቸው ከአንድ በላይ ሞዴሎች በውስጣቸው ያካተቱ ይኖራሉ። <u>ለምሳሌ</u>:- የስታክ ሞዴል (ጉባ 1981:38) የታይለርንና የስተንሀውስን አጠቃሎ የያዘ ነው፤ ሆኖም አንድ አጥኚ ለሥራው የሚስማማውን አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሞዴል መርጦ መጠቀም ይችላል። የመረጠውንም ለማሻሻል፣ አለዚያም የግሉን ፈጥሮ መገልገል እንደሚችል፣ ጉባ (1981:1-38)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:332-333) እና ኦሊቫ (1988:160፣ 483) እምነታቸውን ይገልፃሉ።

## 2.3. <u>የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን የሚወስኑ ቀዳማይና ደዘታዊ ተሳውጦዎች፣</u>

አንድ አዲስ መርሀ-ትምህርት ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በዝግጅት ወቅት በሥሩ ያካተታቸውን ዘርፎች ማለት አጠቃላይ ዓላማዎች፣ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶችና የአቀራረብ ስልቶች፣ የክፍለ-ጊዜ ሥርጭት፣ የመማር-ማስተማር ልምዶች፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎችና ምዘናዎች (የምዘና መሥፈርቶች) በግልፅ ተጠቃሚው በሚያውቀውና በሚረዳው ቋንቋ መቅረብ አለባቸው። ከዚህም በላይ በመርሀ-ትምህርቱ ትግበራ ሂደት በቀጥታ ለሚሳተፉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሁሉ በቀጥታ ግንኙነትና በመግባባት የመርሀ-ትምህርቱ ለውጥ ለምን እንዳስፈለገ፣ ምን እንደተለወጠ፣ እንዴትና በምን ስነ-ዘዴ መተግበር እንደሚቻል በቅድሚያ ገለፃ ማድረግና በጠቅላላው ከተለወጠው

መርሀ-ትምህርት ጋር ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ብለው የሙያው ጠበብት ያምናሉ። ፓይኔ (1974:108)፣ ለዊ (1977:22)፣ ሀወስ (1979:194-195)፣ ፕራት (1980:428፣ 431፣ 437-441)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:76-77)፣ ብራንድት (1981:15)፣ ሆልት (1983:55-57)፣ ሳሊያ-ባኦ (1987:97-98)፣ ኦርንስቴይን (1988:224-229)፣ ኦሊቫ (1988:115)፣ ማርሽ (1991:25-29)ና ፉላን (1992:9፣ 37፣ 67-69)።

በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ያሉ አሠልጣኝ መምህራን መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር የሚያስችሏቸው ሥልጠናዎችና ሙያዊ ውይይት (work shop) ስለስነ-ዘዴው ሲሰጣቸው፣ ተቋማቱ በተለወጠው መርሀ-ትምህርት አንፃር ተዋቅረውና ተደራጅተው ለዕጩ መምህራን መመልመያ መሥፈርቶች ሲያዘጋጁ፣ በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት የተዘጋጁ አዳዲስ የማስተማሪያ መሣሪያዎች በአግባቡ ተሠራጭተው አጠቃቀማቸው ሲታወቅና ዕጩ መምህራኑን ለማሠልጠን አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ሁሉ በቅድሚያ ሲመቻቹ መርሀ-ትምህርቱን መተግበር ይቻላል፤ ትግበራውም ውጤታማ ይሆናል በማለት ጨምረው ፀሐፍቱ ሀሣባቸውን አጠናክረው ይገልፃሉ። ባርነስ (1982:181)፣ ሪቻርድስ (1985:11-15)፣ ሪቻርድስና ሮጀርስ (1986:20-22)፣ ዱቢንና ኦልሽቴይን (1986:30-31)፣ በርስት (1988:18-19) እና ጆንሰን (1989:36) ከሌሎቹ ጋር የሚያስማማቸውን አስተያየት ይሰጣሉ። የተጠቀሱት ቅድመ-ሁኔታዎች (ቀዳማይና ይዘታዊ ተላውጦዎች) የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚወስኑ ናቸው ብለውም ፀሐፍቱ ያምናሉ።

ዱንክንና ብድል (1970:93-99) እና ስተርን (1983:499)፣ ደግሞ በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት የሠልጣኝ መምህራን ቅድመ-ሥልጠና ልምዶች፣ በሠልጣኞች ላይ በግልፅ የሚታዩና የማይታዩ ስነ-ልቦናዊ ባሕርያት፣ አመለካከቶችና ስሜቶች፤ የአሠልጣኝ መምህራን የሥልጠና ልምዶች፣ የሥራ ልምዶች፣ በመምህራኑ ላይ በግልፅ የሚታዩና የማይታዩ ስነ-ልቦናዊ ባሕርያት፤ ስሜቶችና አመለካከቶች የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚወስኑ ቀዳማይና ይዘታዊ ተላውጦዎች ናቸው ብለው እምነታቸውን ይገልፃሉ።

እንደጠበብቱ አባባል፣ አዲስ መርሀ-ትምህርት በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በትግበራው ሂደት ችግር ይፈጥራሉ የሚባሉ ቅድመ-ሁኔታዎች ሁሉ መመቻቸት አለባቸው። መርሀ-ትምህርቱ ለትግበራ የማያስቸግርና ግልፅ መሆን ይጠበቅበታል። ለሥልጠናው ተፈላጊዎቹ ተማሪዎች ባግባቡ መመልመልና ለማሰልጠን ደግሞ በቂና

ብቃት ያላቸው መምህራን መመደብ ይኖርባቸዋል:: ተስማሚና በቂ የማስተማሪያ መሣሪያዎችንም ማዘጋጀትና ማሠራጨት ያስፈልጋል::

## 2.4. <u>የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነ-ዘዴ እኩዋያ በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ክንውንን የሚወስኑ ሂደታዊ ተሳውጦዎች፣</u>

በስነ-ዘዴና በመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት መካከል ስላለው ዝምድና ፀሐፍቱ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981)፣ ኑናን (1988)፣ ብራውን (1994) በሠጡት ሀሣብ መሰረት የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ስነ-ዘዴ ሊሆን እንደሚችል ቀደም ብሎ በዚሁ ክፍል በ2.1 ተገልጿል:: በተጨማሪም በመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ነገር ሁሉ በስነ-ዘዴ ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረውም ተጠቅሷል:: ሆኖም በመርሀ-ትምህርቱ ወይም በስነ-ዘዴው ላይ ተፅዕኖ አላቸው የሚባሉት ነገሮች ምንድናቸው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው:: ስለዚህ መለስ ብለን 2.1.3.ን ማየቱ ይጠቅማል::

በመስኩ ፀሐፍት ስነ-ዘዴ ትወራንና ተግባርን መሠረት ያደረጉ ዘርፎች እንዳሉት ተገልጿል:: እነዚህ የስነ-ዘዴ ዘርፎች በሪቻርድስ (1990) ተሻሽለው የቀረቡ ሲሆን፣ በተለይ በመምህራን ሥልጠና ሂደት ግልጋሎታቸው ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ካላቸው የተለያዩ ባሕርያትና ሚናዎች አንፃር በስነ-ዘዴ (በመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት) ላይ ተፅዕኖ አላቸው:: ይህንንም በዝርዝር ቀጥለን እናያለን::

### 2.4.1. <u>መርሀ-ትምህርቱ የተመሠረተበት ትወራ-ነክ ስልት፣</u>

ትወራ-ነክ ስልት መምህራንን በማሠልጠን ሂደት አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልምዶችን ለመፈተሽ ከሚረዱት አምስት መሠረታዊ ነገሮች አንዱና የመጀመሪያው ነው:: አንድ፣ ሁለተኛ ቋንቋን በመምህራን ማሠልጠኛ ደረጃ የሚያስተምር መምህር፣ ስለቋንቋው ተፈጥሮና የመማር ሁኔታ በቂ ዕውቀት እንዲኖረው ያስፈልጋል:: መምህሩ በተቋም ደረጃ የተዘጋጀው መርሀ-ትምህርት መሠረት ያደረገው የቋንቋ ትወራና ቋንቋን የመማር ትወራ ምን እንደሆነ፣ በምን ዓይነት የቋንቋ ክሂሎች ላይ እንደሚያተኩርና እያንዳንዱን የቋንቋ ክሂል እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ይህ ትወራ-ነክ ስልት ጥሩ ግንዛቤን ያስጨብጠዋል ተብሎ ይታመናል:: በዚህም መሠረት መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር የሚያስችሉ ስልቶችን ከራሱና ከተማሪው እምነት፣ አመለካከትና ስሜት

ጋር በማጣጣም ይመርጣል፤ ያዘጋጃል:: ስለዚህ መርሀ-ትምህርቱ መሠረት ያደረገው ትወራ-ነክ ስልት በመማር-ማስተማር ሂደት በተለይ በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ (በስነ-ዘዴ) ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል በማለት ሪቻርድስና ሮጀርስ (1982:155-157)፣ (1985:18-19)፣ (1986:16)፣ ሪቻርድስ (1990:12) እና ብራውን (1994:14-15) ያስገነዝቡናል::

በትወራ ደረጃ ባሁኑ ወቅት የስነ-ዘዴ የማዕዘን ድንጋይ (Corner stone of method) የሚባሉት የቋንቋ ዕውቀት፣ ቋንቋን የመማር ዕውቀትና ቋንቋን የመማር-ማስተማር ሂደት ዓላማ ናቸው በማለት ከነሪቻርድስ ጋር ተቀራራቢነት ያለውን ሀሣብ ሰልሽ-ሙርሺያ (1991:12-13) ያቀርባሉ:: በተጨማሪም የሁለተኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ቋንቋን ከመማር አንፃር በመነደፉና በተግባቦት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ተማሪ-መራሽ (learner Centered) ነው ይባላል:: ጌታቸው (1986 ዓ.ም. : ፵) እና ሥ/ትምህርት (1986 ዓ.ም. : 3) ያገናዝቧል::

## 2.4.2. የሠልጣኝ ተማሪው ሚና፣

መርሀ-ትምህርት፣ መምህርና የማስተማሪያ መሣሪያዎች በሌሉበት በትምህርት መስክ ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ መሆን ይቻል ይሆናል፤ ግን ያለተማሪ አይሞከርም:: ስለዚህ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪው በጣም ተፈላጊው የሂደቱ አካል ነው ይላሉ ስለሚናው ሲገልፁ ሪቻርድስና ሮጀርስ (1982:159-160)፣ (1985:22-23)፣ (1986:23) እና ሪቻርድስ (1990:13-14)::

በተማሪው ምክንያት በመማር-ማስተማር ሂደቱ ተፅዕኖ ይኖራል:: በዚህም ተማሪው ለሂደቱ ያለው አስተዋፅኦ ምን ያህል እንደሆነ ስነ-ዘዴው ያንፀባርቃል:: በተማሪው በኩል የተለያዩ የክንውን ዓይነቶች ትምህርቱን በመማር ሂደት በቡድን የመሥራት ባሕርይ፣ እርስበርሱ ያለው ግንኙነት፣ አንዱ ባንዱ ላይ ያለው ተፅዕኖና እያንዳንዱ እንደለውጥ ፈላጊነቱ (Processor)፣ አድራጊነቱ (Performer)፣ ፈር-ቀዳጅነቱ (initiator) እና ችግር ፈቺነቱ (problem solver) የተለያዩ ሚናዎች ይታያሉ ይላሉ እነሪቻርድስ ከላይ ስለተጠቀሰው ሀሣብ ማጠናከሪያ ሲያቀርቡ:: ዱቢንና ኦልሽቴይን (1986:129-136)፣ ሥ/ት (1986 ዓ.ም. : 3-4) እና ሚክካጋርንም (1993:129) ያገናዝቧል::

እነዚህ የተማሪ ሚናዎች ከመማር ትወራ-ነክ ስልት፣ ስለመማር ካለው አመለካከት፣ ከመማር ስልቶች፣ ክንውኖችና ልምምዶች፣ ተማሪው እርስ በርሱና ከመምህሩ ጋር ካለው ተራክቦ፣ ተማሪው ልምምዶችን በመሥራት ደረጃ ራሱን ሲቆጣጠርና ተማሪው ለውጤታማ የመማር-ማስተማር ሂደት ከሚሰጠው ትርጉም ጋር የተዛመዱ ናቸው በማለት ሪቻርድስ (1990:13-14) እምነታቸውን ይገልፃሉ::

የተማሪው ሚና እንደመምህሩ ሚና በሁለት ይከፈላል:: እነዚህም ከፊል የክፍል አያያዝና የመማር ሚናዎች ሲሆኑ፣ የመምህሩ ደግሞ የክፍል አያያዝና የማስተማር ሚናዎች ናቸው:: የክፍል አያያዙን ሚና ተማሪው ከመምህሩ ጋር ይጋራል ብለው ራይት (1987:101-125) ያምናሉ::

በተማሪውና በመምህሩ ሚናዎች ላይ ተፅዕኖ አላቸው ተብለው የሚገመቱት ምክንያቶችም በሁለት ይከፈላሉ:: የመጀመሪያው በሰው ልጆች መካከል ያሉ ግንኙነቶች/የግንኙነት ደረጃ፣ እምነት፣ አመለካከትና ማነቃቂያ (motivation) / ሲሆኑ፣ ሁለተኛው ከክንውን ጋር የተዛመዱ ምክንያቶች / ግቦች፣ ድርጊቶችና ርዕስ-ጉዳዮች / ናቸው ይላሉ ራይታ (1987:45-46)::

ዱንክንና ብድል (1986:99-100) ደግሞ የቋንቋን የመማር-ማስተማር ሂደት (ስነ-ዘዴን) የተማሪውና የመምህሩ የክፍል ውስጥ ባሕርያት፣ በተማሪውና በመምህሩ ላይ በክፍል ውስጥ በግልፅ በሚታዩና በማይታዩ የባሕርይ ለውጦች ይወስናሉ በማለት ሀሣባቸውን ያቀርባሉ:: ስተርን (1983:499) ይመለከቷል::

### 2.4.3. የስሠልጣኝ መምህሩን ሚና፣

በተማሪው ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ሂደት ሁሉ ማስተማር ይባላል:: ማስተማር በስነ-ዘዴ አማካኝነት በሥራ ላይ የሚውልና በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማር ሂደት መምህራን ያላቸውን ሚና የሚገልፅ ነው:: በዚህም አንድ የቋንቋ መምህር ምን ዓይነት የማስተማር ስልት እንደሚመርጥና ምን ዓይነት የክፍል ውስጥ ተራክቦ እንደሚወድ ከክፍል ውስጥ እንቅስቃሴውና ከሚናው ማወቅ ይቻላል:: አብዛኛው የቋንቋ መምህር የሚከተሉትን የሚና ዓይነቶች በክፍል ውስጥ ያሳያል ተብሎ ይገመታል:: ሪቻርድስና ሮጀርስ (1982:160-161)፣ (1985:23-24)፣ (1986:23-24)፣ ሥ/ት (1986 ዓ.ም. : 2-3) እና ሪቻርድስ (1990:12-13) ይመለከቷል:: እነዚህም

የተማሪውን የመማር ሂደት መቆጣጠር፣ ማነቃቃት፣ ተማሪውን ማደራጀትና መምራት፣ በተግባር ምሳሌ መሆን፣ ለተማሪው እንደአማካሪና ጓደኛ መሆን፣ የተማሪውን ፍላጎት ማሰስ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማዘጋጀትና ክንውኖችን በመገምገም መረጃ-ምገባ (ክትትል) ማድረግ ናቸው:: መሰል የመምህሩ ሚናዎች ሊገኙ የሚችሉት ጥሩ የመማር ሁኔታዎች ማምጣት ከሚችል ዝግጅትና በመምህሩ የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት በክፍል ውስጥ ከሚደረጉ ክንውኖች፣ ድርጊቶችና ልምምዶች ነው:: ስለዚህ እነዚህን በተመለከተ መምህሩ ለማስተማሩ ሂደት ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረው ያስፈልጋል ብለው በተጨማሪ እነሪቻርድስ ሀሣባቸውን ያጠናክራሉ::

ፓስነር (1992:186-187) ማንኛውም መርሀ-ትምህርት በመምህሩ በክፍል ውስጥ መተግበር ካልቻለ ትርጉም የለውም:: መምህሩም በክንውኑ ሂደት ለመርሀ-ትምህርቱ ነፍስ ሊዘራ የሚችለው በማስተማሩ ሂደት ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ምክንያቶችን መገንዘብና መቆጣጠር ሲችል ነው:: እነዚህም ቁሳዊ፣ ጊዜ-ተኮር፣ አደረጃጀታዊና ግላዊ ምክንያቶች ናቸው ብለው ያምናሉ::

ፉላን (1992:67-68) ደግሞ የመርሀ-ትምህርትን የትግበራ ሂደት የሚወስኑ ነገሮች ከመምህሩ ሚና አንፃር በመምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ አለመሆን፣ ያለመተማመን፣ ያለመተጋገዝ፣ ያለመማማር፣ የልምድ ልውውጥ አለመኖር፣ በሥራ ውጤታማ አለመሆንና ተስፋ መቁረጥ ወይም የሞራል ጉዳይ ናቸው ብለው ይገምታሉ::

ሰይለርና ጓደኞቹም (1981:78) መምህሩ መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር የሙያ ማሻሻያ፣ የቁሳቁስና የሰው ዕርዳታ እንዲሁም መረጃ-ምገባ ካላገኘ ውጤታማ አይሆንም ብለው ይገልፃሉ::

ፀሐፍቱ በተለያየ አገላለፅ ቢያቀርቡም ዋናው ጭብጥ ስነ-ዘዴን ወይም የመርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት በሚወስኑ ሁኔታዎች ላይ ያተኮረ ነው:: ስለዚህ እንደ ምሁራኑ እምነት መምህሩ ድርሻውን መወጣት ካልቻለ፣ ከጓደኞቹ ጋር ጤናማ ግንኙነት ከሌለውና በሙያው ተደራጅቶ ዕድገት ካላሣዬ በክፍል ውስጥ የማስተማር ሂደቱ (ስነ-ዘዴው) ተግባራዊ አይሆንም፤ ስለዚህ የመምህሩ ሚና ስነ-ዘዴውን ሊወስን ይችላል የሚል ነው::

### 2.4.4. በክፍል ውስጥ የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች ያቀራረብ ስልት ሚና፣

የተሻለ የመማር ሁኔታን ለማምጣት ማስተማር በድርጊቶች፣ በክንውኖችና በልምምዶች የታጀበና እነዚህን እንዴት በክፍል ውስጥ መጠቀም እንደሚቻል የሚረዳውንም ስልት ያጠቃልላል:: መርሀ-ትምህርቱ ምን ዓይነት ድርጊቶችን፣ ክንውኖችንና ልምምዶችን ይጠቀማል? ለስልቶቹ መምረጫ መስፈርቱስ ምንድነው? በየምዕራፉ ለሚቀርበው ለያንዳንዱ የትምህርት ርዕስ ምን ዓይነት የክፍል እንቅስቃሴ ያስፈልገዋል? ወዘተ. ጥያቄዎች የትግበራ ስልቱን (ስነ-ዘዴውን) የሚጠቁሙ ናቸው ብለው ሪቻርድስና ሮጀርስ (1982:163-164)፣ (1985:26-27)፣ (1986:26-27) እና ሪቻርድስ (1990:14) ይገምታሉ::

በመማር-ማስተማር ሂደት የስነ-ዘዴ ዓላማ ቀደም ብሎ ማምጣት ከሚችለው ውጤትና ከሂደቱ ቢታወቅም ስነ-ዘዴው በሥራ ላይ የሚውለው (ተግባራዊ የሚሆነው) በተደራጀ የክፍል ውስጥ የተማሪ፣ የመምህርና የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተራክቦ ነው:: በዚህም ድርጊቶችን፣ ክንውኖችንና ልምምዶችን ከመምረጥ አኩዋያ በትወራ ደረጃ የነበሩ የስነ-ዘዴ ልዩነቶች ግልፅ ይሆናሉ:: እያንዳንዱ ስነ-ዘዴ የራሱ የሆነ የተለያየ የተማሪ-አስተማሪ ቅንጅት፣ አቦዳደንና የክፍል ውስጥ ተራክቦ ይኖረዋል:: መሠረታዊ የሆኑት የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎችና መስተጋብራዊ ሂደቶችም፤ ክርክርን፣ ውይይትን፣ መጠየቅና መልስ መስጠትን ያካትታሉ በማለት እነሪቻርድስ ተጨማሪና ማጠናከሪያ ሀሣባቸውን ይሰጣሉ::

ሲያጠቃልሉም ዘመናዊ የስነ-ዘዴ ዓይነቶች ብዙዎቹ የሚታወቁበት መንገድና መሠረታዊ ባሕርይ ቢኖር የአሠራር ስልታቸውና ልምምዳቸው ነው:: በዚህ መሠረት የተመረጠ ስነ-ዘዴ በዘመናዊነቱ ከሌሎች የታወቀና የተሻለ በመሆኑ የመማር-ማስተማር ስልቶችን፣ መልመጃዎችን፣ ልምምዶችን፣ የትምህርት ምንጮችን (resources)፣ ጊዜን፣ መሥሪያ ቦታን፣ መሣሪያዎችንና ድርጊቶችን በቅደም ተከተል ሥርዓትን ጠብቆ ለመተግበር እንደአመቺነቱ ይዞ ስለሚገኝ መርሀ-ትምህርቱን በሥራ ላይ ከማዋል አንፃር ያቀራረብ ስልቱ ያለው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም ብለው እነሪቻርድስ ይገምታሉ::

እንደፀሐፍቱ፣ የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች ያቀራረብ ስልት ከዘመናዊ የማስተማር ዘዴ የሚመደብ ነው:: ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት በተለይ በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ስልቱ የተሻለና ውጤታማ ነው:: ስለዚህ ስነ-ዘዴን ወይም የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ይወስናል::

## 2.4.5 የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሚና፣

የመርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ ሌሎች የሚወስኑ ነገሮች ቢኖሩ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ናቸው:: የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሚናዎች በክፍል ውስጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ያላቸው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም:: ተፅዕኖአቸውን ዓይነታቸው፣ ባሕርያቸው፣ አዘገጃጀታቸውና የአዘጋጆቻቸው ሁኔታ ይወስናል:: ይኸውም የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ በቀጥተኝነት የሚያገለግሉ ናቸው ወይስ በረዳትነት? ከአርጌው መርሀ-ትምህርት በቀጥታ የተቀዱ ናቸው ወይስ የተሻሻሉ? ማን አዘጋጃቸው? / አሻሻላቸው?/ እንዴትስ መጠቀም ይቻላል? ለመጠቀም ምን ዝግጅት ያስፈልጋል? መሣሪያዎቹ ተገምግመው ያውቃሉ? በማን? ወዘተ. ጥያቄዎች አንድ መርሀ-ትምህርት በአዲስ መልክ የተዘጋጀውም ሆነ ተሻሽሎ የቀረበው በሥራ ላይ ሲውል ስለማስተማሪያ መሣሪያዎች መደረግ ያለባቸውን ሁኔታዎችና መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች የሚጠቁሙ ናቸው:: ጥሩ የሆኑ፣ ብዙዎቹ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ዓላማን ይወስናሉ፤ ክንውኖችን ይጠቁማሉ፤ ስልቶችን ይመርጣሉ፤ መመሪያ ይሰጣሉ፤ ያለማምዳሉ፤ መረጃ-ምገባ ያደርጋሉ:: ቋንቋን ከመማር-ማስተማር ሂደት አንፃር ደግሞ ለቋንቋ አጠቃቀም ምሳሌ ይሰጣሉ፤ ትርጉም ያለውን ክንውን ያቀርባሉ፤ የመግባቢያ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፤ ታዋቂ ትወራዊ መርሆዎችን መሠረት ያደርጋሉ፤ የተማሪውን ስሜት የመሣብና በአዕምሮ የመቀረፅ ኃይል አላቸው:: በዚህም ምክንያት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ቋንቋን የመማር-ማስተማር ሂደት ተፈላጊ አካል ናቸው በማለት ሪቻርድስና ሮጀርስ (1982:161-163)፣ (1985:24-26)፣ (1990:24-26)፣ ራይት (1987:75-79)፣ ሪቻርድስ (1990:14-15) እና ሮስነር (1990:131-136) ግም ታቸውን ይገልፃሉ::

የማስተማሪያ መሣሪያዎች እንደአዘጋጆቻቸው የተለያየ ዓይነትና ባሕርይ ቢኖራቸውም ከዕውኑ ዓለም ጋር የተዛመዱ፣ በቀላሉ የሚገኙና ለማንቀሳቀስ የሚመቹ፣ የተማሪውን የቋንቋ ክሂል ሊያዳብሩ የሚችሉ፣ ተገቢነት ያላቸው፣ የሚያስደስቱ፣ የሚያበረታቱና ከመርሀ-ትምህትቱ ዓላማ ጋር የሠመሩ መሆን እንደሚገባቸው ስቲቨን (1983:27) እና ዱቢንና አልሽቴይን (1986:126-136) እምነታቸውን ይገልፃሉ::

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህ ሲታይ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች እንደ አዘጋጆቻቸው ልዩነት ቢኖራቸውም በሚናቸው የመማር-ማስተማሩ ሂደት አካል በመሆን መርሀ-ትምህርቱን ክስነ-ዘዴ አኩዋያ ለመተግበር ወሳኝነት አላቸው የሚል ነው::

## 2.5. የቋንቋን መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚወስኑ ወጤታዊ ተላውጦዎች፣

አንድ፣ አዲስ ወይም ተሻሽሎ የቀረበ መርሀ-ትምህርት በሥራ ላይ ሲውል ከዓላማው አንፃር የሚያስገኘው ውጤት የመማር-ማስተማርን ሂደት ሊወስን ይችላል:: ይኸውም የመማር-ማስተማር ሂደት ዓይነተኛ ዓላም በተማሪው ባሕርይ የአስተሳሰብና የአሠራር ለውጥ ማምጣት ነው:: በዚህም ተማሪው ችግሩን ራሱ እንዲፈታ ይጠበቅበታል:: እነዚህ ለውጦች በሂደቱ በአጭር ጊዜ በተማሪው ላይ አፋጣኝ ዕድገት የሚያሳዩና ረዘም ባለጊዜ ደግሞ በተማሪው ላይ ቀስበቀስ ሊከሰቱ የሚችሉ ናቸው:: ስለዚህ በዚህ አኩዋኋን የሚገኙ ውጤቶች የተማሪውን የመነቃቃትና የመማር ሁኔታን ይወስናሉ ብለው ዱንክንና ብድል (1986:101-125) እና ስተርን (1983:499) ይገምታሉ::

ራይት (1987:45-46) ደግሞ በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት በስነ-ዘዴ የሚተገበሩ (በሥራ ላይ የሚውሉ) ክንውኖችና በነሱ አማክኝነት የሚደርሱ ግቦች በሂደቱ ላይ በተለይ በተማሪውና በመምህሩ ሚናዎች ላይ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል የሚል ሀሣብ ያቀርባሉ::

የፀሐፍቱ አባባል፣ አንድ መርሀ-ትምህርት ከዓላማው አንፃር የመማር-ማስተማር ሂደቱን፣ በተለይ የተማሪውን እንቅስቃሴ ስለሚወስን ተማሪው በክፍል ውስጥ ማምጣት የሚገባውን ውጤትም ሆነ በጠቅላላው በመርሀ-ትምህርቱ ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ መገኘት የሚገባውን አጠቃላይ ውጤት ላይ ተፅዕኖ እደሚያደርግ ያስገነዝበናል::

ጠቅለል ባለ መልኩ፣ በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍሎች ከ2.3-2.5 የመርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚወስኑ ቀዳማይና ይዘታዊ ተላውጦዎች ካልተስተካከሉ ጥሩና የተመቻቸ የመማር-ማስተማር ሂደት፣ በተለይ የክፍል ውስጥ ተራክቦ አይኖርም፤ ጥሩ የክፍል ውስጥ ተራክቦ ከሌለ ደግሞ ጥሩ ውጤት አይገኝም:: መርሀ-ግብሩ ውጤት ከሌለው መርሀ-ትምህርቱም ዋጋ ሊኖረው አይችልም:: ስለዚህ ቀዳማይና ይዘታዊ፣ እንዲሁም ሂደታዊና ውጤታዊ ተላውጦዎች መመቻቸት፣ ጥሩ መሆንና መደጋገፍ የመርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ በሥራ ላይ ለማዋል አዎንታዊነት አላቸው የሚሉ ፀሐፍት ሀሣቦችን ያካተቱ ሆነው እናገኛቸዋለን::

## ክፍል ሶስት፣ የጥናቱ ዘዴ

ይህ ሥራ አንድ የትምህርት ባለሙያ፣ በተለይ መምህሩ በሥራ መስኩ ላይ ሆኖ እንደሚያደርገው የምርምር ዓይነት (as action research) የሚቆጠር ነው:: አጥኚው ለዚህ ጥናት የሚስማማ የግምገማ ሞዴል መርጧል:: ገላጭ የምርምር ስልትንም መረጃዎችን ለመተንተን ተጠቅሟል::

### 3.1. ለጥናቱ የተመረጠው ሞዴል፣

የመርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ ለመገምገም የተመረጠው ሞዴል ተመጣጣኝነትንና ተደጋጋፊነትን መሠረት ያደረገ የስታክ ሞዴል (Stake's Congruence-Contingency model) ይባላል:: አንዳንዴም የሚያስማማም ሞዴል (Contenance Model) በመባል ይታወቃል:: ይህ ሞዴል የተቀረፀውም በስታክ (1967) ሲሆን ማንኛውንም ትምህርት ነክ የሆነ መርሀ-ግብር ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚረዱ ሶስት መደቦች አሉት:: እነሱም ቅድመ-ሁኔታዎች (antecedents)፣ መስተጋብራዊ ሂደቶች /transactions/ እና ውጤቶች (outcomes) ናቸው:: እያንዳንዱ መደብ መረጃ ከማን፣ ከምንና እንዴት እንደሚሰበሰብ ዝርዝርና ንዑስ ዘርፎች ያካተተ ነው:: የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችም በያንዳንዱ ንዑስ ዘርፍ አንፃር ተጠቁመዋል (አባሪ ለን ያገናዝቧል)::

በርካታ የመስኩ ፀሐፍት የሆኑት ፓይኔ (1974:127-130)፣ ስተንሀውስ (1975:106-108)፣ ብራንድት (1981:2)፣ ሰይለርና ጓደኞቹ (1981:350-356)፣ ባርነስ (1982:182-189)፣ ማዶውስ (1983:287-305)፣ ሀውስ (1984:47)፣ ኦርንስቴይን (1988:259-260) እና ፓስነር (1992:237-238) ስለ ስታክ ሞዴል (የሚያስማማ ሞዴል) ያላቸውን አስተያየት በየሥራዎቻቸው ይገልፃሉ:: የመማር-ማስተማር ሂደትን፣ በተለይ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴን ለመገምገም ዓይነተኛ ምሳሌ ነው ብለውም ያምናሉ::

የሚያስማማ ሞዴል ሶስት መደቦች አሉት ብለናል:: እያንዳንዱ መደብ በዕቅድ ደረጃ ያለና በተግባር የታየ በመባል የሚታወቁ ሁለት ክፍሎች አሉት:: በዕቅድ ደረጃ ያሉት መደቦች ደግሞ አንፃራዊ በሆነ መንገድ በተግባር ከታዩት መደቦች ጋር ተመጣጣኝነት ይጠበቅባቸዋል:: በሌላ በኩልም በዕቅድ ደረጃ ያሉት መደቦች እርስ

በርሳቸው ቀጥተኛ በሆነ መንገድ በተጠየቂያዊ አካሄድና ግንኙነት ተደጋጋፊነት አላቸው:: በተግባር የታዩት መደቦች ደግሞ ሳይንሳዊ መደጋገፍ ይታይባቸዋል::

<u>የስታክ ሞዴል መደቦችን የሚያሳይ ምስል፣</u>




ምንጭ፣ ስታክ (1967:533)

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ፣ አንድ የትምህርት መርሀ-ግብር ወይም የመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ የሚገመግም ሰው በመደቦቹ ቀጥተኛ መደጋገፍ በሚገኙ መረጃዎችና በየመደቦች በታቀዱትና በተግባር በታዩት ሁኔቶች መመጣጠን የሚገኙ መረጃዎች ሰብስቦ በመዳኘት ለውሣኔ ይደርሣል:: ከሁለቱ ባንዱ መንገድ ብቻ መረጃ ሰብስቦ የሚያገኘው ውሣኔ አስተማማኝነት እንደሌለ የሚቆጠር ነው የሚል ይሆናል::

**ሞዴሉ የተመረጠበት ምክንያት (ስታክ 1983:297)፣**

ጠንካራ ጎኖቹን በማየትና ለሥራው ተስማሚ ሆኖ በመገኘቱ አጥኚው ሞዴሉን መርጦታል:: የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በጥንቃቄ በሥራ ላይ ከዋሉ (በተለይ ምልከታው በጥንቃቄ ከተካሄደ) ተጨባጭ መረጃዎችን መሰብሰብ እንደሚቻል የመስኩ ፀሐፍት ያምናሉ (ኢቫንስ 1977:75 እና ሀውስ 1983:54-55)::

ስለዚህ በሞዴሉ ምድቦች ላይ መጠነኛ መሻሻሎች ተደርገዋል:: እነሱም፤

- አጠቃላይነት ያላቸው ሁኔታዎች ሁሉ ከምድቦቹ ተቀንሰዋል::
  - ለምሳሌ:- የትምህርት ቤት አካባቢዎች (ክፍሎች፣ መብራት፣ ወንበርና ጠረጴዛ ወዘተ.)
- በሶስቱም መደቦች መነሻ በሆነው መርሀ-ትምህርት መሠረት በተማሪው፣ በመምህሩ፣ በማስተማሪያ መሳሪያዎችና በሚያስገኙት ውጤት ላይ ትኩረት ተደርጓል::
- በሶስቱም መደቦች ለግምገማ ሂደቱ ያግዛሉ የሚባሉ ክፍሎች ሁሉ ተወስደዋል::
- መረጃን መሰብሰቢያ መሣሪያዎችም የሰነድ ምርመራ፣ መጠይቅና የክፍል ውስጥ ምልከታ ሆነው ተወስደዋል::

**የተመረጠው ሞዴል ጠንካራ ጎን (ስታፍልቢም 1983:122-123)፣**

የስታክ ሞዴል፤

- ዓላማንና ሂደትን መሠረት ያደረገ መሆኑ፣
- ትምህርታዊ ውሳኔዎችን ለመስጠት በማስቻሉ፣
- ነፃ የግምገማ ሞዴል ስለሆነ መምህራንን ለምርመራ በመጋበዙ፣
- በትምህርት መስክ ለሚደረግ ዕድገትና መሻሻል አዎንታዊ አስተዋፅኦ ስላለው፣
- ለመዳኘት የሚያስችል መረጃ በሁለት አቅጣጫ በተሳታፊዎች ፍላጎት ስለሚሰበሰብና
- ሁለቱንም የግምገማ ዓይነቶች ስለሚጠቀም ከሌሎች መሰል ሞዴሎች አንፃር ሲታይ ጠንካራ ጎኑ በጣም የጎላ ሆኖ እናገኘዋለን::

የተመረጠው ሞዴል ደካማ ጎን (ስታክ 1967:7-15)፣

በስታክ ሞዴል መረጃ ለመሰብሰብ ዋናው መሣሪያ ምልከታ በመሆኑ ተጨባጭ ባልሆነ መንገድ (Subjectively) መረጃዎችን ሰብስቦ ይተነትናል:: ተጨባጭ (objective) መረጃ ለመሰብሰብ ያስቸግራል:: ይህ ደግሞ የሁሉም ዋና ዋና መርሀ-ግብርን መገምገሚያ ሞዴሎች የጋራ ባሕርይ ነው (ሀወስ 1983:49)::

## 3.2. የናሙና መረጣና የተሳታፊዎች አወሳሰድ ዘዴ፣

በ1990 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በደ/ኢ/ሕ/ክ/መ/ ከሚገኙት ዘጠኝ ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች ለአንደኛ ሳይክል (ከ1-4) ያሉትን ተማሪዎች ለማስተማር ዕጩ መምህራን ተመልምለው አዋ/እና አርባ-ም/መም/ማ/ተቋማት ለሥልጠና ገብተዋል:: በዚህ የትምህርት ዘመን ከተጠቀሱት ዞኖችና ወረዳዎች ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት፣ ካላቸው የአንደኛ ሳይክል ብዛትን፣ በዝውውር የተሸጋሸጉ መምህራንን፣ የአካባቢው ኋላቀርነትን፣ የተማሪ-አስተማሪ ጥምረትንና የመምህራን የጊዜ ጫናን መሥፈርትነት መሠረት እያንዳንዳቸው ኮታ ተሰጥቷቸዋል፤ በዚህም መሠረት ተመልምለዋል:: በየተቋማቱም ተደልድለዋል:: አርባ-ምንጭ 640 ሠልጣኞች ሲደለደሉ አዋሳም 360፤ በጠቅላላው 1000 ከተደለደሉት ተመልማዮች መሀል አንዳንዶቹ በተለያዩ ምክንያቶች በመቅረታቸው አርባ-ምንጭ 629 እየሠለጠኑ ሲገኙ አዋሳም 338፤ በሁለቱ ተቋማት በሥልጠና ላይ የሚገኙት ሲጠቃለሉ 967 ዕጩ መምህራን ናቸው::

በነዚህ ተቋማት አማርኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚሰጥ ሲሆን ትምህርቱም ለግማሽ ዓመት ነው:: የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ላይ ነው:: ስለዚህ በ1990 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን በአንደኛ ወሰነ-ትምህርት አማርኛ ቋንቋን የሚማሩ ሠልጣኝ ተማሪዎች በፆታ ሳይለዩ 441 ናቸው:: አዋ/መም/ማ/ተ/ በአራት ክፍሎች 171 ተማሪዎች ይማራሉ፤ አርባ-ም/መም/ማ/ተቋምም በሰባት ክፍሎች 270 ተማሪዎች:: ቀድሞ አጥኚው በመምህር የአንድ ክፍል ተማሪዎችን በተሳታፊነት ለመምረጥ በወሰነው መሠረት ከተጠቀሱት 11 ክፍሎች በዕጣ የንሞና ዘዴ ሶስት ክፍሎች ተወስደዋል:: በሶስቱ ክፍሎች የሚገኙት 132 ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህ በዚህ ጥናት የመጀመሪያዎቹ ተሳታፊዎች ሆነዋል::

በጥናቱ ሁለተኛዎቹ ተሳታፊዎች በሁለቱም ተቋማት አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው። እነዚህም በቁጥር ሶስት (አዋሳ መም/ማ/ተ/ 2፣ አርባ-ም/መም/ማ/ተ/ 1) ሲሆኑ በአጋጣሚ የንሞና ዘዴ ሁሉም ተወስደዋል።

በሦስተኛ ደረጃ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

- ከሥርዓተ-ትምህርት የቋንቋ ፓናል፣
  - ከአ/አበባ ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ተቋም፣ የቋንቋ ፓናል አባል
  - ከክልል ትምህርት ቢሮ፣ የቋንቋ ፓናል አባል

- ከሥልጠናና ምልመላ ትምህርት ክፍል፣ የትምህርት ባለሙያዎች
- የሁለቱ ተቋማት ርዕሰ-መምህራንና
- የሁለቱ ተቋማት የአማርኛ (የቋንቋ) ትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ናቸው።

እነዚህም ተሣታፊዎች ያለምንም ምርጫ ከአስፈላጊነታቸው አንፃር በየመሥሪያ ቤቱ መረጃ ይሰጣሉ የተባሉት ግለሰቦች በአጋጣሚ የናሙና አወሳሰድ ስልት ተነሙነዋል።

## 3.3. የመረጃ አሰባሰብና ስልቱ፣

### 3.3.1. መረጃ መሰብበቢያ መሣሪያዎችና የአሰባሰብ ስልት፣

ለመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት መገምገሚያ በተመረጠው ሞዴል መሠረት አጥኚው ለሥራው በቂ መረጃ ለመሰብሰብ ያስችሉኛል ብሎ ያመነባቸውን ሦስት ዋና ዋና መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች መርጦ ተጠቅሟል። እነርሱም፤ ሰነድ ምርመራ፣ የክፍል ውስጥ ምልከታና መጠይቅ (ቃለ-መጠይቅና የፅሑፍ መጠይቅ) ናቸው።

#### 3.3.1.1. የሰነድ ምርመራና የመረጃ አሰባሰብ ስልት፣

በዚህ ሁለት ሰነዶች ተመርጠዋል። የመጀመሪያው በ1987 ዓ.ም. አማርኛ ቋንቋን በተቋም ደረጃ ለማስተማር በአዲስ መልክ የተዘጋጀው መርሀ-ትምህርት ነው። ሁለተኛው ደግሞ የተማዎች የትምህርት ማስረጃ ነው።

## የመርሀ-ትምህርቱ ምርመራና የመረጃ አሰባሰብ ስልት፣

በዚህ የምርመራ ሂደት አጥኚው በመርሀ-ትምህርቱ፣ በማስተማሪያ መፅሐፉ፣ በዓመታዊ (መንፈቃዊ) የትምህርት ዕቅዱና በተማሪው ማስታወሻ የተጠቀሱትን ሁሉ ዘግቧል:: በዚህም መርሀ-ትምህርቱ ከተጠቀሱት ጋር በትምህርት ዓላማው፣ በይዘቱ፣ በስነ-ዘዴው (መልመጃዎቹ)፣ በመርጃ መሣሪያዎቹ፣ በግምገማ ስልቱና በክፍለ-ጊዜ ሥርጭቱ አንፃር ለማገናዘብ እንዲመች ተደርጎ ተወስዷል::

## የተማሪው ሰነድ ምርመራና የመረጃ አሰባሰብ ስልት፣

ተማሪው በክልሉ ትምህርት ቢሮ በተዘጋጀው የመመልመያ መሥፈርት (የብሔረሰብ ቋንቋ፣ የትምህርት ማስረጃና የመግቢያ ፈተና) መሠረት ተቋም መግባቱን ለማረጋገጥ የያንዳንዱ ተሳታፊ ተማሪ ሰነድ ተፈትሿል:: በዚህም ፍተሻ መሠረት የሚከተሉት መረጃዎች ተጠናቅረዋል፤

- ከትራንስክሪፕት ላይ ከ9-12 ክፍል ያለው ያማርኛ ውጤት አማካይ ነጥብ፣
- ከ12ኛ ክ/መ/ፈ/ የምስክር ወረቀት ላይ፤ 12ኛን የጨረሰበት ዓ.ም.፣ ያማርኛ ውጤት እና አጠቃላይ አማካይ ውጤት (GPA)፣
- የመመልመያ መስፈርቶች አጠቃላይ ውጤት እና
- በሥልጠናው ላይና ከሥልጠናው በኋላ ከሙከራዎች፣ አጋማሽና አጠቃላይ ፈተናዎች ውጤት በትክክል ተዘግቧል::

አጥኚው ይህንን የተማሪ ሰነድ ለመመርመር እንዲረዳው ቅድመ-ሥልጠናና ድህረ-ሥልጠና ልምድን መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ቅፅ አዘጋጅቶ ተጠቅሟል(አባሪ ሀን ይመለከቷል):: የመመልመያ መሥፈርቶችንም ከተማሪው ሰነድ ጋር ለማመሳከር በሚመች መልክ ዘግቧል:: በሰነድ መልክ መያዝ ያለባቸውን ደግሞ ፎቶ ኮፒ አድርጎ ለማስቀረት ሞክሯል::

### 3.3.1.2. ምዕከታና የመረጃ አሰባሰብ ስልት፣

የመርሀ-ትምህርትን የትግበራ ሂደት ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ዋናው መሣሪያ ምልከታ ነው። በምልከታ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት የሰውን ልጅ የሚተካ ሌላ መሣሪያ እንደሌለ ስታክ ይናገራሉ (1983:297)።

ምልከታ እንደአጠቃቀሙ ስልት መዝግቦ (ቀርፆ) ማስቀረት (**Ethnography**) እና በሥርዓት ቋሚ የሆኑ ነጥቦች የያዘ ማመሣከሪያ ቅፅ (**fixed system**) በመባል በሁለት ይከፈላል (ሪቻርድስ 1990:44 እና ዋላስ 1991:76) ያገናዝቧል።

መዝግቦ የማስቀረት ስልትን በመጠቀም የሚሰበሰበው መረጃ ከአስቸጋሪነቱና ከወጪው በስተቀር ተጨባጭ መረጃን ይሰጣል ብለው የሚመርጡ አሉ። ቋሚ የማመሳከሪያ ነጥቦችን የያዘውንም ቅፅ ይሻላል የሚሉም አልታጡም። ሁሉም እንደአምነቱና አመለካከቱ በመረጠው መሣሪያ ይጠቀማል። ሁለቱም ቢሆኑ የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው፤ ሆኖም በዘመኑ ተመራጩ የምልከታ ስልት መዝግቦ ማስቀረቱ መሆኑን ድርሳናት ጥቆማ ያደርጋሉ። ቢሆንም አጥኚው የራሱን የምልከታ መሣሪያ (ቅፅ) ለመቅረፅ ስለወሰነ የሚከተለውን ሞዴል ተጠቅሟል።

#### 3.3.1.2.1. የክፍል ውስጥ ምዕከታ መሣሪያ (ቅፅ) መቅረፅ፣

የዚህ ጥናት አቅራቢ ለመጠቀም የፈለገው የመጀመሪያው የምልከታ ስልት መዝግቦ ማስቀረቱን ነበር። ነገር ግን ካለው ጊዜ፣ ከወጪው፣ ከቁሳቁስ ዕጥረትና ከናሙና ተቋማት አቀማመጥ ችግር የተነሳ ሊሣካለት አልቻለም። ስለዚህ የቀረውን ቋሚ ነጥቦችን የሚጠቁመውን የምልከታ ስልት ከመምረጡ በፊት በዚህ ስልት ከበርካታ የክፍል ውስጥ ተራክቦን ለመገምገም ከሚያስችሉ ሞዴሎች የፍላንደርስን (1970)፣ የቤላክን (1966) እና የሚቸልን (1979) መርምሯል። ፍተሻ ባደረገባቸው ሁሉ አንድ የተዛባ አመለካከት ተገንዝቧል። ይኸውም ባሁኑ ጊዜ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ ተማሪ-መራሽ መሆን አለበት፤ ተማሪው በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ሁሉ ዝም ብሎ ተቀባይና ተመልካች አይሆንም፤ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት እንጂ በሚባልበት ዘመን ለተማሪውና ለመምህሩ በየምልከታ ሞዴሎቹ የተሰጠው የማመሳከሪያ ነጥብ ወደ መምህሩ ያደላ ሆኖ አግኝቶታል። ለምሳሌ የፍላንደርስ (1970) የምልከታ ሞዴል ቅፅ

ብንወስድ አሥር የማመሣከሪያ ነጥቦች አሉት። ሰባቱ የመምህሩ ሲሆኑ፣ ሁለቱ የተማሪው ናቸው። እንዱም የዝምታ። ሞዴሉ በመምህሩ እንቅስቃሴ ላይ ብቻ ብዙውን ጊዜ እንድናባክን ይጋብዘናል። ስለዚህ አጥኚው የተለየ የራሱ የምልከታ መሣሪያ (ቅፅ) ቀርጿል። ይህም መሣሪያ ከላይ በምሳሌው እንደተጠቀሰው ሞዴል ቋሚ ነጥቦች ለማመሳከሪያነት ያለው ነው። በክፍል ውስጥ ተራክቦ የተማሪውና የመምህሩ ሚና ምን እንደሆነ የራይትን (1987) ሀሣብ መሠረት አድርጓል። በመሣሪያው ለተማሪውና ለመምህሩ እኩል 10፣10 ነጥቦች እንዲኖራቸው ተደርጓል። ከዚህም ሌላ የተማሪውንና የመምህሩን ተሳትፎ መጠን በቁጥርና በጊዜ ምልከታ አድራጊው እንዲሞላ፣ የባከነ ጊዜ እንዲገልፅ፣ መምህሩ የተጠቀመበት የማስተማሪያ መሣሪያና በክፍሉ-ጊዜው የተሰጡ መልመጃዎች ካሉ እንዲዘግብና በመጨረሻም የግሉን አስተያየት እንዲሰጥ ክፍት ቦታዎች ተትተዋል (አባሪ ሀን ያገናዝቧል)።

3.3.1.2.2. <u>የምልከታ መረጃ አሰባሰብ ስልት፣</u>

ሀ. <u>መረጃ ሰብሳቢዎችን ማስለ፣</u>

አጥኚው የክፍል ውስጥ ምልከታ የሚያደርጉትን ሰዎች ፍለጋ ለሁለቱ ተቋማት (አዋ/እና አርባ-ም/መም/ማ/ተቋማት) ቀረቤታ ያላቸውን አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (አርባ-ምንጭ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት) እና አንድ መም/ማ/ኮሌጅ (የአዋሳ መም/ማ/ኮሌጅ) አስሷል። ከያንዳንዱም ፍቃደኛ የሆኑ መምህራንን ሊያገኝ ችሏል።

ለ. <u>የመረጃ ሰብሳቢዎችንና ምልከታ የሚደረግባቸውን ቁጥር መወሰን፣</u>

የዚህ ጥናት አቅራቢ ምልከታውን ለማድረግ ፍቃደኛ የሆኑትን ሰዎች ካገኘ በኋላ ቀደም ብሎ የሶስት ክፍል ተማሪዎች እንዲሳተፉ በወሰነው መሠረት በሶስቱም የክፍል ተራክቦው እንዲታይ ሶስት ገምጋሚዎች በአንድ ክፍለ-ጊዜ እንዲሆኑ ወሰነ። በየተቋማቱ 3፣3 ሲሆን 6 ሰዎች ተመረጡ። አራቱ በአማርኛ ቋንቋ የተመረቁ ሲሆን፣ ሁለቱ የባችለር ድግሪ የቀሩት ሁለት ደግሞ በማስትሬት ድግሪ የጨረሱ ናቸው። ከስድስቱ ሁለቱም በባችለር ድግሪ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተመረቁ ነበሩ።

ሐ. <u>መርሀ-ግብር ማዘጋጀት፣ ገለፃ፣ ሙከራና ትውውቅ ማድረግ፣</u>

እንደገምጋሚዎቹ ፍቃድ ምልከታ በሚያደርጉበት ተቋም ሶስት፣ ሶስት ሆነው በአንድ ክፍለ-ጊዜ በሳምንት አንድ ክፍል ለመገምገም በወሰኑት መሠረት ከየትምህርት ቤታቸው የትምህርት መርሀ-ግብር ጋር እንዳይጋጭ ተደርጎ ለሶስት ሣምንታት መርሀ-ግብሩ በስምምነት በጋራ ተዘጋጅቷል።

ገምጋሚዎቹ ግምገማ ከመጀመራቸው በፊት በቂ ገለፃ ተደርጎላቸዋል። ለያንዳንዱም ቅፁ እንዲጠና በእጁ ተሰጥቶታል። ከዚህም በላይ ሁለት፣ ሁለት ክፍለ-ጊዜያት ቅፁን ይዘው ክፍል በመግባት ሙከራዎችን አድርገዋል። በሙከራ ጊዜያቸውም ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር ትውውቅ አድርገዋል። በመጨረሻም እያንዳንዱ ገምጋሚ ከክፍል ሳይወጣ ቅፁን ለማስረከብ ተስማምቷል።

መ. <u>ምልከታው በትክክል መካሄዱን ማረጋገጥ፣</u>

አጥኚው ከሁለቱ ተቋማት በአንዱ የክፍል ተራክቦው በትክክል መገምገሙን አረጋግጧል። የሶስቱንም ሳምንታት ከገምጋሚዎቹ ጋር ክፍል ከመግባቱም ሌላ ካለገምጋሚዎች በያንዳንዱ ክፍል በቀሩት ክፍለ-ጊዜያት የሚደረጉትን ተራክቦዎች ገምጋሚዎች ባሉበት ከሚደረጉት ጋር አገናዝቧል። አንዱን ተቋም ደግሞ የተቋሙን ምክትል ርዕሰ-መምህር ትብብር ጠይቆ እንዲከታተልለትና የመገምገሚያ ቅፁን ከክፍል ሳይወጡ ከያንዳንዱ ገምጋሚ እንዲረከብለት አድርጓል።

#### 3.3.1.3. <u>የመጠይቅ መረጃ አሰባሰብ ስልት፣</u>

##### 3.3.1.3.1. <u>በፅሑፍ መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ስልት፣</u>

የፅሑፍ መጠይቁ ለሠልጣኝ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። የጥናቱን ዓላማና ማሳሰቢያ ከያዘው ገፅ በስተቀር ሌላው በአራት አበይት ክፍሎች ተከፍሏል። የመጀመሪያው የተማሪውን ዳራዊ መረጃ 8 ጥያቄዎች፣ ሁለተኛው የተማሪውን አመለካከት 8 ጥያቄዎች፣ ሶስተኛው የተማሪውን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ 14

ጥያቄዎች፣ የመምህሩን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ 21 ጥያቄዎች፣ የድርጊቶችን፣ የክንውኖችንና የልምዶችን ስልታዊ አቀራረብ 5 ጥያቄዎች፣ በአስተሳሰብና በአሠራር ለውጥ ለማምጣቱ የተማሪዎችን ትንቢያ 6 ጥያቄዎች የያዘና እንዲሁም አንድ ጥያቄ ስለመርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ባዶ ቦታ እንዲሞላ ቀርቧል:: ክፍል አራት ደግሞ በመፅሐፉ፣ በስነ-ዘዴው፣ በጊዜውና በግምገማ መሥፈርቶች ላይ ነፃ አስተያየቱን ተማሪው የሚሰጥበት ሆኖ ክፍት ቦታ ተትቷል (አባሪ ሀን ያገናዝቧል)::

ተሳታፊ ተማሪዎች መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት በቂ ገለፃ ተደርጎላቸዋል:: መጠይቁ ከአንደኛ ወሰነ-ትምህርት መጨረሻ ላይ እንዲቀርብ ተደርጎ ስለተዘጋጀ ከአጠቃላይ ፈተና በኋላ ሞልተው መልሰዋል::

#### 3.3.1.3.2. በቃለ-መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ስልት፣

ይህ የመርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ቅድመ-ሁኔታዎችን ከማመቻቸት፣ ከክፍል ውስጥ ተራክቦና ከሚያስገኘው ውጤት አንፃር አጠቃላይ ጥያቄዎች ለሚከተሉት ተሳታፊዎች ተዘጋጅቶ ነበር::

- ለቋንቋ ፓናልና ለምልመላና ሥልጠና ት/ክፍል፣
- ለቋንቋ ትምህርት ክፍልና ለርዕሰ-መምህራን እና
- ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን::

በፅሑፍ የተዘጋጀው አጠቃላይ የሆነው ጥያቄ ለያንዳንዱ ክፍል በቃል ከመቅረቡ በፊት አንድ ቀን ቀደም ተብሎ እንዲዘጋጁበት ተሰጥቷል:: አንዳንዱ ክፍል በፅሑፍ የሰጠ ቢኖርም የጥያቄዎቹ አቀራረብ በምልልስ ወቅት ጥያቄ ጥያቄን የሚተካ በመሆኑ በተቻለው መጠን አጥኚው መጠየቅ የሚገባውን ጥያቄ ማግኘት ከሚገባው መረጃ አንፃር በግንባር ተገናኝቶ ጠይቋል::

### 3.3.2. መረጃዎችን የማጠናቀርና የአተናተን ስልት፣

#### 3.3.2.1. በሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች፣

አሀዛዊ ያልሆኑ መረጃዎች በተፈለጉበት ቦታ ሁሉ ከሰነዱ እንደተወሰዱ ተጠቅሰዋል፤ መነሻፀር የሚገባቸውም ተነፃፅረዋል:: ለውሣኔም እንዲያመች ገለፃ ተደርጎባቸውል::

አሀዛዊ የሆኑ መረጃዎች ደግሞ በስታትስቲክስ የስሌት ቀመር በተገኘው ውጤት መሠረት ቅድመ-ሥልጠና ልምድ ከክፍል ውስጥ ተራክቦ (ከሂደቱ) እና በተቋም ከመጣው የትምህርት ቅስሞሽ (ውጤት) ጋር፣ የክፍል ተራክቦው ከተቋሙ ውጤት ጋር እና ቀጥተኛ በሆነ ግንኙነት ሶስቱም ያላቸው ዝምድና ታይቷል፡፡ በዚህም ቅድመ-ሥልጠና ልምድ ለክፍል ውስጥ ተራክቦ ምን ያህል አስተዋፅኦ እንዳለው፣ የክፍል ውስጥ ተራክቦ ደግሞ በተቋም ለመጣው ውጤት (ለድህረ-ልምድ) ምን ያህል ድጋፍ እንዳደረገ ተገናዝቧል፡፡

ቅድመ-ሥልጠና ልምድ የሚያጠቃልለው፤

- ከ9-12 ያማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤትን፣
- ከ12ኛ ክ/መ/ፈ/ የአማርኛ ውጤትን፣
- በ12ኛ ክ/መ/ፈ/ አጠቃላይ ውጤትን (GPA) እና
- የመመልመያ መሥፈርቶች ጥቅል ውጤትን ነው፡፡

የክፍል ውስጥ ተራክቦው የሚያካትተው፤

- ከተማሪው መጠይቅ የተገኘውን የተማሪውን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ነጥብና
- ከተማሪው መጠይቅ የተገኘውን የመምህሩን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ነጥብን ነው፡፡

ድህረ-ሥልጠና ልምድ ደግሞ ሠልጣኝ ተማሪው በተቋሙ የመጨረሻ ፈተና ያመጣው ውጤት ነው፡፡

### 3.3.2.2. <u>በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች</u>፣

በምልከታው ቅፅ ባለ አምስት መለኪያ መሥፈርቶች ለ20 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነርሱም የተማሪውንና የመምህሩን ተሳትፎ ለመለካት የቀረቡ ሲሆኑ አምስት የተለያዩ ቁጥሮች ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህም፤

4 ሁልጊዜ

3 ብዙጊዜ

2 በመጠኑ

1 አንዳንድ ጊዜና

0 በጭራሽ አይደረግም የሚሉ የጊዜ ድግግሞሾች በአንድ ክፍለ-ጊዜ (በ45 ደቂቃ) ውስጥ የሚከወኑትን ድርጊቶች ለማሳየት ነው፡፡ በስሌት የአምስቱ ድምር 10

ሲሆን አማካዩ ደግሞ 2 ይሆናል። ስለዚህ ከአማካይ በላይና በታች በሚመጡ ቁጥሮች መሠረት ለመጣው ነጥብ ገለፃ ተሰጥቶበታል። ይህ በሠንጠረዥ መልክ የያንዳንዱን ገምጋሚ በየሳምንቱ የሶስት ሳምንታት በተመረጠው ክፍልና ቋንቋውን ለማስተማር ከተመደበው መደበኛ መምህር አንፃር ቀርቦ ተተንትኗል። ከቋሚ ምልከታ ነጥቦች ሌላ የሚሞሉና አስተያየት ለመስጠት የሚያስችሉ ልቅ ጥያቄዎችም በየክፍሉ ስንት ተማሪ እንደተሳተፈና ለምን ያህል ጊዜ ተሳትፎ እንዳደረገ፣ መምህሩ ምን ያህል ጊዜ እንደተሳተፈና የባከነ ጊዜስ ምን ያህል እንደሆነ በምልከታው ቅፅ ተካተዋል። ከነዚህም ተጠናቅረው መቅረብ የሚችሉት በሠንጠረዥ ቀርበዋል፤ ያልቻሉት በመረጃነት በተፈለጉበት ቦታ እንዳሉ ተጠቅሰዋል። ለሁሉም ማብራሪያና ገለፃ ተሰጥቶባቸዋል።

### 3.3.2.3. <u>በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች፣</u>

#### 3.3.2.3.1. <u>በፅሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች፣</u>

በዚህ 54 ጥያቄዎች ባለ አምስት መሥፈርት የሆኑ ቀርበዋል። ከነዚህም፤

ሀ. የተማሪውን ዝንባሌ፣ ፍላጎትና አመለካከት ለመለካት ለቀረቡት 8 ጥያቄዎች መሥፈርቶቹ፤

5 በጣም ከፍተኛ

4 ከፍተኛ

3 መካከለኛ

2 ዝቅተኛ

1 በጣም ዝቅተኛ የሚሉ ናቸው። ድምራቸው 15 ሲሆን አማካያቸው 3 ነው።

ለ. የተማሪውንና የመምህሩን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለመለካት ለተዘጋጁት 35 ጥያቄዎች መለኪያዎቹ ከምልከታው ቅፅ ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

—

ሐ. በክፍል ውስጥ የድርጊቶችን፣ ክንውኖችንና ልምምዶችን ስልታዊ አቀራረብና ተማሪው በአስተሳሰብና በአሰራር ምን ያህል እንደተለወጠ የሚተነብየውን ትንበያ ለመለካት ለቀረቡት 11 ጥያቄዎች መሥፈርቶቹ ደግሞ፤

2 በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ

1 እስማማለሁ

0 መወሰን አልችልም

-1 አልስማማም

-2 በከፍተኛ ደረጃ አልስማማም የሚሉ ናቸው:: እነዚህ ሲደመሩ 0 (ዜሮ) ይሆናሉ፤ አማካያቸውም::

ጠቅለል ባለ መልክ የፅሑፍ መጠይቁን መረጃ አጠነቃቀርና አተናተን ሲገለፅ የሚከተለውን ይመስላል፤

- በፅሑፍ መጠይቁ የተገኙ አሀዛዊ መረጃዎች በምልከታው ክፍል እንደታየው ከአማካዩ በታችና በላይ በሚገኘው ነጥብ አንፃር ተብራርተዋል:: እነዚህም በያንዳንዱ ክፍል በሠንጠረዥ ቀርበዋል::

- በሰነድ ምርመራው ክፍል እንደቀረበው የተማሪውና የመምህሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ነጥብ ከቅድመ-ሥልጠናና ከድህረ-ሥልጠና ልምድ ጋር ያለው ዝምድና በስታትስቲክስ ስሌት ቀመር ታይቷል:: የክፍል ተራክቦው ለድህረ-ሥልጠናው ልምድ (በተቋም ለመጣው ውጤት) ያለው አስተዋፅኦ ምን እንደሆነም ተጠቁሟል::

- አሀዛዊ ያልሆኑ መረጃዎች ደግሞ በመረጃነት በሚፈለጉበት ቦታ እንዳሉ ተጠቅሰዋል::

3.3.2.3.2. <u>በቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች</u>፣

በዚህ መሣሪያ የተሰበሰቡት ሁሉ አሀዛዊ ያልሆኑ በመሆናቸው በሁሉም እንደተደረገው በተፈለጉበት ቦታ ሁሉ ተጠቅሰው ገለፃና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል::

## ክፍል አራት፣ የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት፤

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የመርሀ-ትምህርትን ትግበራ ሂደት ከስነ-ዘዴ አኩዋያ በመፈተሽ ሂደቱን በገላጭ የምርምር ስልት መተንተንና ከውጤት መድረስ እንደሆነ በቀዳሚው ክፍል ተጠቅሷል:: በተጨማሪ በክፍል አንድ የተመለከቱትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንደሚሞክርም ተወስቷል::

የዚህ ጥናት ክፍል ዓላማ ደግሞ ለጥናቱ በተመረጡት መሣሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን ለተጠየቁት መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው::

ስለዚህ በያንዳንዱ መሣሪያ የቀረበው መረጃ በዓላማዎቹ መሠረት ለያንዳንዱ ጥያቄ በተቻለ መጠን የመረጃ ሶስት ምዘናን (data triangulation) ጠብቆ እንደሚከተለው ቀርቧል::

### 4.1. <u>በመሣሪያዎቹ የቀረቡ መረጃዎች፣</u>

#### 4.1.1. <u>በሰነድ ምርመራው፣</u>

ከመርሀ-ትምህርቱ፣ ከማስተማሪያ መፅሐፉና ከሁለቱ ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና ከተማሪው ማስታወሻ ተፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል (አባሪ ሠን ያገናዝቧል)::

ከተማሪው ሰነድ ደግሞ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት የተማሪው ቅድመና ድህረ-ሥልጠና ልምዱ ሲፈተሽ ከ132 ተማሪዎች የ125ቱ ብቻ የተሟላ ሆኖ ተገኝቷል:: ሆኖም ቅድመ-ሥልጠና ሆነ ድህረ-ሥልጠና ልምዱ ለትንተና እንዲመች ሆኖ ተጠናቅሮ ቀርቧል (አባሪ መን ይመለከቷል):: ከዚህም በላይ ቅድመ-ሥልጠና ልምዱ ከክፍል ውስጥ ተራክቦና ከድህረ-ሥልጠና ልምዱ ጋር ያለው ዝምድና (Correlation) እና ድህረት (regression) በስታቲስቲክስ የስሌት ቀመር ታይቷል::

#### 4.1.2. <u>በክፍል ውስጥ ምልከታው፣</u>

ከተገምጋሚ መምህራን አንዳንዶቹ በክፍለ-ጊዜያቸው ለመገኘት ብዙ አስቸግረዋል፤ ሆኖም በተቋማቱ ኃላፊዎች ዕርዳታና ድጋፍ በሁለቱም ተቋማት

ለምልከታ የተመረጡት ሶስት ክፍሎች እያንዳንዳቸው በሳምንት አንድ ጊዜ ለሶስት ሳምንታት ምልከታ ተደርጎባቸዋል:: በያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ ሶስት፣ ሶስት ገለፃ የተደረገላቸው የትምህርት ባለሙያዎች ገምግመዋል:: ለአንዱ ክፍለ-ጊዜ የተሰጠው 45 ደቂቃ በመሆኑ እያንዳንዱ መምህርና ክፍል በሶስቱ ሳምንታት ሶስት ጊዜ ለ135 ደቂቃ (ለ2:15 ሰዓት)፤ በጠቅላላው ለ405 ደቂቃ (ለ6:45 ሰዓት) ምልከታ እንዲደረግ ከተመደበው ጊዜ 45 ደቂቃ ሲባክን ከቀረው 6:00 ሰዓት፤ የመምህሩ የክፍል ተሳትፎ 295 ደቂቃ (4:55 ሰዓት) ሲወስድ፣ የተማሪው የክፍል ተሳትፎ ደግሞ 65 ደቂቃ (1:05) ፈጅቷል:: በ65 ደቂቃ በጠቅላላው 79 ተማሪዎች በሶስቱም ክፍሎች በዘጠኝ ክፍለ-ጊዜያት ውስጥ ተሳትፎአቸውን አሳይተዋል (አባሪ ሬን ያገናዝቧል)::

#### 4.1.3. በመጠይቁ፣

##### 4.1.3.1. የፅሑፍ መጠይቅ፣

የፅሑፍ መጠይቁ በሁለቱም ተቋማት የአንደኛ ወሰነ-ትምህርት መጨረሻ ፈተና እንዳበቃ በዕለቱ ስለተሰጠ እንዲሣተፍ የተመረጠው ተማሪ ሁሉ በትክክል ሞልቶ መልሷል:: በመጠይቁ የተገኘው መረጃ ደግሞ በያንዳንዱ ክፍልና ተፈላጊ ርዕስ አኩዋያ ተጠናቅሮ ከተማሪው አስተያየት ጋር ለገለፃ ቀርቧል (አባሪ ሰን ይመለከቷል)::

##### 4.1.3.2. የቃል መጠይቅ፣

በቃለ መጠይቅ ከሚከተሉት መሥሪያ ቤቶችና የትምህርት ባለሙያዎች መረጃ ተሰብስቧል፤

- ከሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ተ - አራት ሰዎች ተጠይቀው ሁለቱ ብቻ ፍቃደኛ ሆነው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፤
- ከደ/ኢ/ሕ/ክ/መ/ ሥልጠናና ምልመላ ክፍል - አምስት ሰዎች ተጠይቀው ሶስቱ ብቻ በፍቃደኝነት በመጠይቁ ተሳትፈዋል፤
- ከደ/ኢ/ሕ/ክ/መ/ሥ/ት/ክፍል - የተገኘው አንድ ሰው በመሆኑ ራሱ ተጠይቆ በፍቃዱ ምላሽ ሠጥቷል::
- ከአዋ/ እና አርባ-ም/መም/ማ/ተቋማት፤

ሀ. ርዕሰ-መምህራን፤ ከአዋሳ ዋናውና ምክትሉ፣ ከአርባ-ምንጭ ደግሞ ምክትሉ ብቻ ፍቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው አስተያየታቸውን ለመስጠት ችለዋል::

ለ. <u>የቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎች</u>፣ አዋሳ የብሔረሰብ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል ኃላፊ የሆነው በፍቃደኝነት ሲሳተፍ፣ የአርባ-ምንጭም የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ ሆኖ በመገኘቱ በፍቃዱ ተሳትፎውን አሳይቷል::

ሐ. <u>የአማርኛ ቋንቋ መምህራን</u>፣ በሁለቱ ተቋማት አማርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩት ሶስት መምህራን ሁለቱ ብቻ ምንም ሳያስቸግሩ በፍቃደኝነት ለተጠየቁት ቃለ-መጠይቅ መልስ ሲሰጡ፣ ሶስተኛው ግን በጊዜ ዕጥረት በማመካኘት ቢያስቸግርም በተመቸው ጊዜ እንዲሳተፍ ተደርጓል::

በጠቅላላው፣ ለቃለ-መጠይቅ 18 ሰዎች ለማሳተፍ ታቅዶ 12 ብቻ ፍቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው ተሳትፎአቸውን አሳይተዋል:: በዚህ መልክ በሶስቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተሰበሰቡት ውህቦች (data) እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፤

<u>የተሳታፊዎች ዳራዊ መረጃ፣</u>

<u>የተሳታፊ ተማሪዎች ዳራዊ መረጃ፣</u>

ሀ. <u>የተማሪው አፍ መፍቻ ቋንቋ</u>፣ በርካታው ተማሪ አፌን የፈታሁት በብሔረሰቤ ቋንቋ ነው ብሎ ስለመለሰ ትክክለኛውን ውህብ ለማስቀመጥ አልተቻለም::

ለ. <u>የተማሪው ፆታና ዕድሜ</u>፣ 66% ወንድ ሲሆን የቀረው ሴት ነው:: በዕድሜም 49% ከ17-20 ዓመት፣ 47% ከ21-25 ዓመትና 4% ከ25 ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው ሆኗል::

ሐ. <u>ተማሪው ከቤተሰቡ ጋር የሚግባባበት ቋንቋ</u>፣ 66% በብሔረሰቡ ቋንቋ (አፍ በፈታበት ቋንቋ) ሲግባባ፣ የቀረው 34% ደግሞ በአማርኛ ይጠቀማል ለመግባባት::

መ. <u>ተማሪው ከጓደኛ ጋር የሚጠቀመው ቋንቋ</u>፣ 77% በብሔረሰቡ ቋንቋ ሲሆን፣ 23% በአማርኛ ቋንቋ ይግባባል::

ሠ. <u>ተማሪው ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር የሚጠቀመው ቋንቋ</u>፣ 55% በብሔረሰቡ ቋንቋ ሲሆን 45% ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ለመግባባት ይጠቀማል።

ረ. <u>ተማሪው 12ኛ ክፍልን የጨረሰበት ዓመተ-ምህረት</u>፣ በ1989 ዓ.ም. 29% ፣ በ1988 ዓ.ም. 46% ፣ በ1987 ዓ.ም. እና ከዚያ በፊት የጨረሱት ተማሪዎች ደግሞ 25% ሆነው ተገኝተዋል።

ሰ. <u>ተማሪው የ12ኛ ክ/መ/ፈ/ ውጤት በማሻሻል</u>፣ 39.4% ያላሻሻለና 12ኛ ክፍልን እንደጨረሰ ወደ ተቋም የገባ ሲሆን፣ 49.3% ከ1-2 ጊዜ፣ 8.3% ከ3-4 ጊዜና 3% ደግሞ ከ4 ጊዜ በላይ የ12ኛን ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤት ለማሻሻል ፈተናውን የተቀበለ እንደሆነ መረጃው ይገልፃል (ከሀ-ሰ ላለው መረጃ አባሪ ሐን ያገናዝቧል)።

ሸ. <u>ከተማሪው በተለያየ ሙያ የሠለጠነና የሠራ</u>፣ በተለያዩ ሙያዎች ሠልጥኖ የሠራ ተማሪ 3% ሲሆን፣ የቀረው 97% ግን በምንም የሥራ ዓለም ያልተሠማራ በመሆኑ በቀጥታ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ተቋም የገባ ሆኖ ተገኝቷል።

<u>የተሳታፊ መምህራን ዳራዊ መረጃ</u>

<u>ሠንጠረዥ 1፣ የመምህራን ዳራዊ መረጃ</u>

| መም/ ማ/ ተቋም | ክፍል መለያ | ፆታ | | ዕድሜ | አፍ መፍቻ ቋንቋ | የትምህርት ደረጃ | የተመረቀበት ትምህርት | | በተቋሙ የክፍለ-ጊዜ ብዛት | ያገለግሎት ዘመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | | | | ዋና | ንዑስ | | በተቋም | በ2ኛ ደረጃ | ድምር |
| አዋሣ | ቢ (B) | 1 | - | 43 | አማርኛ | 12+4 | አማርኛ | - | 6 | 4 | 15 | 19 |
| | ኤፍ (F) | 1 | - | 38 | ጉራግኛ | 12+4 | ፔዳጎጂ | አማርኛ | 6 | 10 | 3 | 13 |
| አርባ-ምንጭ | ቢ₇ ($B_7$) | 1 | - | 28 | አማርኛ | 12+4 | አማርኛ | - | 21 | 5 | 3 | 8 |

ሁለቱ መምህራን ሲመደቡ ብዙ የሥራ ልምድ እንደሌላቸውና አንዱ መምህር ደግሞ ከሌሎቹ የበለጠ የክፍለ-ጊዜ ጫና እንዳለበት ውህቡ ያመላክታል።

## 4.2. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር ቅድመ-ሁኔታዎችን በተመለከተ፣

### 4.2.1. የመርሀ-ትምህርቱ አጠቃላይ ገፅታ፣

- በተቋም በ1990 ዓ.ም. የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1-4) ተማሪዎችን ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠና በመተግበር ላይ ያለው ያማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከየካቲት 20-30/1987 ዓ.ም. በሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ተቋም መዘጋጀቱን፣

- በዝግጅቱ ከሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ተቋሙ፣ ከመም/ማ/ተቋማቱ፣ ከየክልሉ የሥ/ት/ዝ/ክፍልና ከት/መ/ማ/ማ/ድ/ ባለሙያዎች መሣተፋቸውን፣

- ዝግጅቱ በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት መካሄዱን፣

- የዝግጅቱ ዓላማ የዕጩ መምህራኑን የቋንቋ ክሂሎትን ማዳበርና የማስተማር ዘዴዎችን ማስጨበጥ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ የተለያዩ ይዘቶች መመረጣቸውን፣

- በዝግጅቱ የትምህርቱ ያቀራረብ ስልት የዕጩ መምህራኑን ተግባቦታዊ ችሎታ (**Communicative ability**) የማስተማር ዘዴዎችን ከማዳበር አኳያ በተግባራዊ ክንዋኔ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን መደረጉንና

- በመርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደት የማስተማሪያ መሣሪያዎችና የትምህርት ዓላማዎች ተግባራዊነት የሚረጋገጥበት የግምገማ ዘዴዎች መጠቆማቸውን በመርሀ-ትምህርቱ መግቢያ ተጠቅሷል::

ከቋንቋ ፓናል ሶስት አባላት እና ከሥልጠናና ምልመላ ክፍል ደግሞ ሶስት የትምህርት ባለሙያዎች በቃል ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የመለሷቸው መልሶች ስለመርሀ-ትምህርቱ ዝግጅት ከላይ ከተጠቀሱት ሀሣቦች ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል (ለዝግጅት አባላት ለውይይት የቀረበ የት/ሚ ሰነድም 1986:3 ይመለከቷል)::

### መርሀ-ትምህርቱ በሰነድነቱ ሲመረመር፣

በሰነድነቱ መርሀ-ትምህርቱ ሲፈተሽ ስምንት አጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎችና ለዓላማዎቹ ተግባሪዊነት የተመረጡ ስምንት ይዘቶችን አካቷል:: እነዚህን ይዘቶች ለመሸፈን የተሰጡት ክፍለ-ጊዜያት 52 እንደሆኑም ተጠቅሷል (አባሪ ሠን ያገናዝቧል)::

የመማር-ማስተማር ዘዴውም ተማሪውን በቡድን የሚያሳትፍ እንዲሆን የሚጠቁሙ ስልቶች፣ መርጃ መሣሪያዎችና የግምገማ ዘዴዎችም ተጠቁመዋል::

<u>መርሀ-ትምህርቱ ከማስተማሪያ መፅሐፉ ጋር ሲገናዘብ፣</u>

ከስነ-ዘዴው (የመልመጃዎች አቀራረብ) በስተቀር በትምህርት ዓላማውና ይዘቱ መፅሐፉና መርሀ-ትምህርቱ ተመሣሣይ ናቸው:: ስምንት የትምህርት ዓላማዎችና ስምንት ይዘቶች ሁለቱም አሏቸው:: ስለስነ-ዘዴውም ቢሆን በመፅሐፉ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪውን በደንብ የሚያሳትፉ አለመሆናቸው በመፅሐፉ መቅድም ላይ ከመጠቀሱም በላይ መምህራን የራሳቸውን ጥረት እንዲያክሉበት ያዘጋጆቹ አስተያየት ያስገነዝበናል:: በዚህ ከመርሀ-ትምህርቱ መፅሐፉ ልዩነት እንዳለው መረጃው ይጠቁማል፤ በመርሀ-ትምህርቱ የተጠቀሰው ስነ-ዘዴ ተማሪውን በቡድን እንዲያሳትፍ ሲያመላክት የመፅሐፉ ግን ተቃራኒው ሆኖ ቀርቧል::

<u>መርሀ-ትምህርቱ ከተቋማቱ ዓመታዊ ዕቅድ ጋር ሲገናዘብ፣</u>

በሁለቱ ተቋማት ዓመታዊ (መንፈቃዊ) የትምህርት ዕቅድ ላይ ከመርሀ-ትምህርቱ ዓላማዎችና ይዘቶች ያነሱ ስድስት፣ ስድስት ዓላማዎናና ይዘቶች ተዘግበው ተገኝተዋል፤ ለትግበራ 36 ክፍለ-ጊዜያትም ተይዞላቸዋል:: በሁለቱም ተቋማት ዕቅድ የተጠቀሱት ዓላማዎችና ይዘቶች ከመርሀ-ትምህርቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ለማሳካት ከቀረቡት ይዘቶች የተወሰዱ ቢሆኑም በሁለቱ ዕቅዶች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ይታያል (አባሪ ሠን ያገናዝቧል):: በዓመታዊ ዕቅዶቹና በመርሀ-ትምህርቱ የቀረቡት የትምህርት አቀራረብ ስልቶች (ስነ-ዘዴው)፣ የመርጃ መሣሪያዎች፣ የመገምገሚያ ዘዴዎችና እንዲሁም ለትግበራ የተሰጠው ጊዜ ጭምር ልዩነታቸው የጎላ ሆኖ ተገኝቷል:: ሌላው ቀርቶ በሁለቱ ተቋማት ዕቅዶችም መካከል ከፍተኛ ልዩነት በተለይ በይዘቶቹ አመራረጥ ታይቷል::

<u>መርሀ-ትምህርቱ ከተማሪው ማስታወሻ ጋር ሲገናዘብ፣</u>

በመርሀ-ትምህርቱ ስምንት የነበሩት ይዘቶች በተቋም ዕቅድ መሠረት ግን ስድስት መሆናቸው ታይቷል:: ከስድስቱም ይዘቶች አንዳንዱ ይዘት የመርሀ-ትምህርቱ ይዘት ንዑስ ይዘት ሆኖ የቀረበ ተገኝቷል:: በተመሳሳይ ሁኔታ በተማሪው ማስታወሻ የተገኙት የትምህርት ይዘቶች አራት ብቻ ናቸው:: በሁለቱ ተቋማት በቁጥር ዕኩል ቢሆኑም

ቀድሞ እንደተገለፀው የጎላ ልዩነት ይታይባቸዋል። ሶስቱም መምህራን እንደየዕለታዊ የትምህርት ዝግጅታቸው መሠረት የማስተማር ስልት ለመጠቀም ቢያቅዱም በሁለቱም ተቋማት የተማሪው ማስታወሻ ሲፈተሽ መልመጃዎች አልታዩም፤ ተማሪው የመልመጃ ደብተር እንደሌለውም ታውቋል። ይህም በመጠይቅ ከቀረበው አስተያየት ማረጋገጥ ተችሏል። የየተቋሙ የቋንቋ መምህርም ለተማሪው መልመጃ ለመስጠት ጊዜ አይበቃም የሚል መልስ ሰጥቷል እንጂ መልመጃ አለመስጠቱን አልካደም፤ መልመጃ ከስነ-ዘዴ ዘርፎች አንዱና ዋናው እንደሆነም እያንዳንዱ ከሰጠው መልስ ተረጋግጧል። ስለዚህ በመርሀ-ትምህርትና በተማሪው ማስታወሻ መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ በፍተሻው ሊረጋገጥ ችሏል (አባሪ ሠን ያገናዝቧል)።

<u>መርሀ-ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር ሲታይ፣</u>

እስካሁን በሰነድ ምርመራው የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው መርሀ-ትምህርቱ አጠቃላይ የቋንቋ ዕውቀት፤ የስነ-ልሣን፣ የስነ-ፅሑፍንና የቋንቋ ትወራን የያዘ በመሆኑ የሠልጣኙን የትምህርት ደረጃን አይመጥንም፤ ስለዚህ በትግበራ ላይ ችግሩ ከራሱ ከመርሀ-ትምህርቱ የመነጨ ይመስላል። በተጨማሪም መርሀ-ትምህርቱ ለማን እንደተዘጋጀ በውል አይታወቅም፤ አፉን በአማርኛ ለፈታው ወይስ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማር ተማሪ? መርሀ-ትምህርቱን አዘጋጁ ክፍል በቃለ-ምልልስ በሰጠው መልስ መርሀ-ትምህርቱ የቋንቋን አጠቃላይ ዕውቀት መያዙንና ለማን እንደተዘጋጀ አለመጠቆሙ በትግበራው ሂደት ችግር እንደሚፈጥር ማመኑን ገልጿል። ሶስቱ የቋንቋ መምህራንና የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተዋል። በተጨማሪም መርሀ-ትምህርቱ የአንደኛ ሳይክል (ከ1-4) ትምህርት ቤቶችን መርሀ-ትምህርት ያላገናዘበ በመሆኑ በመሰለን መንገድ ከተጠቀሱት ስምንት አጠቃላይ ይዘቶች ውስጥ ስድስቱን ብቻ መርጠን ወስደን በማስተማር ላይ እንገኛለን፤ እነዚህንም ቢሆን እያደርን ለማሻሻል እንጂ ተስማሚ የመረጥናቸው ይዘቶች ብቻ ናቸው የሚል እምነት የለንም፤ ሁሉንም ለማስተማር የጊዜ ዕጥረት አለና በማለት ጠቅሰዋል። ተማሪውም ስለይዘቶቹ በመጠይቁ በቀረበለት ልቅ ጥያቄ ሲመልስ፤ ይዘቶቹ በዲፕሎማ ወይም በዲግሪ መርሀ-ግብር መካተት የሚችሉ እንጂ በመም/ማ/ ተቋም ደረጃ የሚመጥኑ አይደሉም፤ ምክንያቱም እኛ በመጀመሪያ ደረጃ (ከ1-4) ባሉ ትምህርት ቤቶች ፊደል ከማስለየት፣ ቃላት ከማስመስረትና አጫጭር ዐረፍተ-ነገሮች ከማስነበብ አናልፍም በማለት ሀሣቡን ሰጥቷል። አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲም ይህንኑ አበክሮ ያስገነዝባል (ት/ሚ 1987 ዓ.ም. : 58)።

## 4.2.2. የመማር-ማስተማር ሁኔታዎች፣

የተማሪው ሁኔታ፣ የተማሪው ቅድመ-ሥልጠና ልምድ፤

- ከ9-12 ያግርኛ ውጤት፣ 83%ቱ ተማሪ ከ55-74 አማካይ ውጤት አለው::
- የ12ኛ ክ/መ/ፈ/ ውጤት፣ 60%ቱ ተማሪ 2.00 ነጥብ እንዳለው መረጃው ያሳያል::
- የ12ኛ ክ/መ/ፈ/ ውጤት አጠቃላይ ነጥብ፣ 70%ቱ ተማሪ ከ2.0-2.6 ነጥብ አምጥቷል::
- የተቋም መግቢያ የመመልመያ መሥፈርቶች ጥቅል ውጤት፣ ከተማሪው 42%ቱ ከ55-74፣ 52%ቱ ከ45-54 እና 27%ቱ ከ45 በታች ውጤት እንዳለው መረጃው ያመላክታል::

የተማሪው ስመላመል፣

ከመመልመያ መስፈርቶቹ ዋናዎቹ፤

- 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቀ፣ ሂሣብና እንግሊዝኛን ጨምሮ በአምስት የትምህርት ዓይነቶች አማካይ 2.0 ነጥብና በላይ ያመጣ (ለሴቶች ግን 1.6 እርስበርሳቸው ያወዳድራቸዋል)፣
- ዕድሜው ከ17 ዓመት ያላነሰና ከ30 ዓመት ያልበለጠ፣
- የዞኑንና የልዩ ወረዳውን ቋንቋ፣ ባሕልና ታሪኩን የሚያውቅና
- ከ1987-1989 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ማስረጃ ብቻ ማቅረብ የሚችል መሆን እንዳለበት ከሰነድ የተገኙ መረጃዎች ያመላክታሉ::

የመመልመያ ነጥብ ስሰጣጥ፣

| | |
|---|---|
| - የ12ኛ ክ/መ/ፈ/ ውጤት፣ | ከ35% |
| - ከ9-12 የትራንስክሪፕት ውጤት፣ | ከ25% |
| - የመግቢያ ፈተና ውጤት፣ | ከ40% |
| ጠቅላላ | 100% |

## መመልመያ መሥፈርቶች ተግባራዊነት፤

ከመመልመያ መሥፈርቶች አንፃር የተማሪው ሰነድ ሲፈተሽ የሚከተሉት ስህተቶች ተገኝተዋል፤

- የ12ኛ ክ/መ/ፈ/ውጤት ከሂሣብና እንግሊዝኛ አንዱ የሌላቸው ተማሪዎች ተመልምለዋል::
- በ12ኛ ክ/መ/ፈ/ አጠቃላይ ውጤት ከ1.6 በታች ወንዶችም፣ ሴቶችም ተወስደዋል::
- በዕድሜ ከ30 ዓመት በላይ የሆናቸው ተማሪዎች ከሠልጣኞቹ ውስጥ ተገኝተዋል::
- ያለ መግቢያ ፈተና ተቋም ገብተው በመሠልጠን ላይ ያሉም አሉ::

ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች በላይ የመመልመያ መሥፈርቱ ራሱ ችግር ያለበት ይመስላል፤ ምክንያቱም እንደሰነዱ የምልመላ ሂደቱ የሚካሄደው በሁለት መልክ ነው:: ይኸውም የመጀመሪያው በትምህርት ቢሮዎች የሚደረግ ምልመላ ሲሆን ሁለተኛው በመግቢያ ፈተናው በተቋሙ ሠራተኞች የሚከወን ነው:: ትምህርት ቢሮው እንደመለመለ ለፈተና አቅርቦ አይተውም፤ ከፈተና በኋላ ድጋሚ ምልመላ አድርጎ ያለፉትን በደብዳቤ ለየተቋማቱ ይሸኛቸዋል:: ይህ አሰራር ለግል አመለካከቶች መንገድ የሚከፍት ሆኖ ተገኝቷል፤ ምክንያቱም በሰነድ ምርመራው የተዛባ አመለካከትና ግላዊ አሰራር **(Personal bias)** በጉልህ ታይቷል::

<u>ስምሳሌ</u>:- የመግቢያ ፈተና ውጤት የሌላቸው ሁለት ተማሪዎች በአርባ-ም/መም/ማ/ተቋም በሥልጠና ላይ ተገኝተዋል:: የዚህ ጥናት አቅራቢ ስለሁኔታው ለመጠየቅ በመገደዱ ሁለቱንም ተማሪዎች አነጋግሯቸዋል:: በዚህም አንደኛው በብሔረሰቡ 12ኛን ክፍል የጨረሰ የመጀመሪያው ተማሪ በመሆኑ በልዩ ሁኔታ **(Special Case)** ታይቶ ሊገባ እንደቻለ ከመግለፁም በላይ ሌሎችም በዚህ ጥናት የማይሳተፉ ሠልጣኞች በተመሳሳይ ሁኔታ ገብተው በሥልጠና ላይ እንዳሉ ጠቁሟል፤ አዘጋጁም ይህ ጥቆማ ትክክል መሆኑን አረጋግጧል:: ሁለተኛው ደግሞ በ12ኛ ክ/መ/ፈ/ ውጤት 3.6 ነጥብ ያለው ነው:: የሱ፣ የመልማይ ኮሚቴዎች የተዛባ አመለካከት ያመጣው ችግር ሆኖ ተገኝቷል:: ልጁ የመግቢያ ፈተናውን ያለፈ መሆኑን ያምናል:: በሱ ቦታ ሌላ ተማሪ በአነስተኛ ውጤት እንደተመደበ ስለተረዳ ለትምህርት ቢሮው አመልክቶ በልዩ የደብዳቤ ትዕዛዝ ሊገባና ሥልጠናውን ሊከታተል እንደቻለ

ይናገራል፤ ተመሳሳይ ችግሮች እንዳሉም ጠቁሟል። አዘጋጁም በጥቆማው መሠረት ምንም የትምህርት ማስረጃ የሌላቸው ሁለት ሴት ሠልጣኞችን ለማግኘት ችሏል። እነዚህ ሠልጣኞች በጥናቱ ተሳታፊ ባይሆኑም በምን መልክ ሊገቡ እንደቻሉና ካሁን በኋላስ ምን እንደምጠበቅባቸው የተማሪዎች ቤተ-መዘክር ኃላፊውንና ምክትል ርዕሰ-መምህሩን አነጋግሯቸው ነበር፤ ያገኘው መልስ ግን መረጃቸውን እንዲያሟሉ የግማሽ ዓመት ጊዜ ተሰጥቷቸዋል፤ በዚህ የጊዜ ገደብ ካላሟሉ ይሰናበታሉ የሚል ሆኖ አግኝቶታል። በዚህ መልክ በተቋም ገብተው በመሠልጠን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑም አጥኚው ሊረዳ ችሏል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## የመምህሩ ሁኔታ፣

ስለመርሀ-ትምህርቱ ዕውቂያ የለኝም (አልተደረገልኝም)፤ በወርክሾፕ፣ በሰሚናር ወይም በሙያዊ ውይይት መርሀ-ትምህርቱን በተመለከተ የተሳተፍኩበት ጊዜ የለም፤ መርሀ-ትምህርቱ ለኔ እንግዳ በመሆኑ ዓላማው፣ ይዘቱ፣ የማስተማሪያ መሣሪያውም ሆነ ስነ-ዘዴው አዲስ ስለሆነ በሥራ ላይ ለማዋል በጣም ተቸግሪያለሁ። ግን የአንደኛውን ሳይክል መርሀ-ትምህርትና የማስተማሪያ መፅሐፍ በማዘጋጀትም ሆነ በመገምገም በመሣተፌ ለተቋሙ የተዘጋጀው መርሀ-ትምህርት ከሳይክሉ መርሀ-ትምህርት ጋር ይጣጣማሉ፤ ዕጩ መምህራኑንም ለቋንቋ መምህርነት ያበቃቸዋል ብዬ ያመንኩባቸውን ይዘቶች በመምረጥ ተማሪውን በሚገባውና በመረጥኩት የማስተማር ስልት (ስነ-ዘዴ) ተጠቅሜ አስተምራለሁ በማለት ሶስቱም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቃል ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል። የሁለቱ ተቋማት ርዕሰ-መምህራንና የቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎችም ለመምህራን ስለመርሀ-ትምህርቱ ለውጥ ምንም ገለፃና ዕውቂያ እንዳልተደረገ በሰጡት አስተያየት አረጋግጠዋል። የደ/ኢ/ሕ/ክ/መ/ ትምህርት ቢሮ የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል ደግሞ ስለአዲሱ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ገለፃም ሆነ ትውውቅ እንዲሁም ስለትግበራው ሂደት ክትትል ለማድረግ የሰው ኃይል ዕጥረት አለብን ከማለት በስተቀር መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን ለሰጠት ሀሣብ ተቃውሞ የለውም። ግን ተፈላጊው ሰው በተፈለገው ሙያ ተልኮልን ስለማያውቅ የተቋማቱ አሠራርም በሂደቱ ላይ ችግር ከሚፈጥሩት ምክንያቶች እንደ አንዱ የሚመደብ ነው በማለት ዝግጅት ክፍሉ ይጠቁማል።

የመምህራን ምደባና ድልደላ በተመለከተ የክልሉ ሥልጠናና ምልመላ ትምህርት ክፍል፣ የተቋማቱ ርዕሰ-መምህራን፣ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና እያንዳንዱ ያማርኛ ቋንቋ መምህር ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተዋል። ይኸውም በደ/ኢ/ሕ/ክ/መ/

ያማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕጥረት ስላለ የተገኘው መምህር ያለምንም መሥፈርት ይመደባል በማለት ነበር ሁሉም የመለሱት። የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑም ቢሆኑ ከዚህ የተለየ ችግር መርሀ-ትምህርቱን በሥራ ላይ ከማዋል አኩዋያ አሉ የሚሏቸው የሚከተሉት ናቸው፤

- በተቋም ደረጃ መምህራን እርስበርሳቸው ጤናማ ግንኙነት ያለመኖር፣
- በተቋም ደረጃ በቋንቋ ትምህርት ክፍል ያሉትም እርስበርሳቸው ጤናማ ግንኙነት ያለመኖር፣
- በተቋም ደረጃ የልምድ ልውውጥ አለመደረግ፣
- ሙያቸውን ለማሻሻል የሚጥሩ መምህራን ቢኖሩም ለትምህርት ያለው ዕድልና የመግቢያ መስፈርቶች መጥበብ ተስፋ አስቆራጭ በመሆኑና
- ተቋም ስንገባ ብዙዎቻችን የማሰልጠን ልምዱ የሌለን መሆናችን (የመምህሩን ዳራዊ መረጃ ያገናዝቧል)።

### 4.2.3. የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሁኔታ፣

እነዚህ የትምህርት መሣሪያዎች መርሀ-ትምህርቱን፣ የተማሪውን መፅሐፍና የመምህሩን መምሪያ ያካትታሉ።

#### መርሀ-ትምህርቱ፣

ስለመርሀ-ትምህርቱ ዝግጅት በዚህ ምዕራፍ መግቢያ በ4.2 በስፋት ተጠቅሷል። በስርጭቱ ግን ለሁሉም ተቋማት ዕኩል አልተዳረሰም። በነዚህ ሁለት ተቋማት የተገኙት ቅጅዎች ሁለት ብቻ ሲሆኑ እነርሱም በዕቃ ግምጃ ቤት ተዘግቶባቸው ለዚህ ጥናት ቅኝት መረጃዎችን ለመሰብሰብ አጥኚው እስከወጣበትና መምህራኑንና ርዕሰ-መምህራኑን እስከጠየቀበት ጊዜ ድረስ። መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች እንደልባቸው ለማየት አልቻሉም፤ መምህራን እንደጠቀሱት በተለይ ተማሪው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት መኖሩንም አያውቅም። —

የማስተማሪያ መፅሐፍ (የተማሪው መፅሐፍ)፣

በ1987 ዓ.ም. በደ/ኢ/ሕ/ክ/መ/ ትምህርት ቢሮ አማካኝነት በሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል በኩል ከየተቋማቱ ከተመረጡት የቋንቋና የሥነ-ትምህርት መምህራን እንዲዘጋጁት የክልሉ የሥ/ት/ዝ/ እና የቋንቋ ፓናል ክፍል በቃል ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ በሰጡበት ወቅት ጠቁመዋል (ማስተማሪያ መፅሐፉንም 1987 ዓ.ም. ይመለከቷል)፡፡

መርሀ-ትምህርቱ አጠቃላይ የቋንቋ ዕውቀት እንዳለውና የአንደኛ ሳይክል መምህራንን ለማሰልጠን ብቃት እንደሚጎድለው ቀደም ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ መፅሐፉም ከመርሀ-ትምህርቱ በቀጥታ የተቀዳ በመሆኑ ዕጩ መምህራኑን ለአንደኛ ሳይክል የሚያዘጋጃቸው አይደለም፡፡ በስነ-ዘዴውም ደካማ ነው፡፡ የተካተቱት መልመጃዎች ተማሪውን የሚያሳትፉ አይደሉም፤ ብቃት ይጎድላቸዋል፡፡ መፅሐፍቱን ተማሪው ለማጣቀሻነት እንኳን እንዳይጠቀም በቁጥር በጣም አነስተኛ ናቸው ይላሉ ሶስቱም የተቋማቱ ያማርኛ ቋንቋ መምህራን ለተጠየቁት የቃል ጥያቄ መልስ በሰጡበት ወቅት፡፡ በዚህ የሶስቱም የቋንቋ መምህራን አስተያየት ተቀራራቢና ተመሳሳይ ቢሆንም ሶስቱም የየግላቸውን ማስታወሻ ለማስተማሪያነት እንደሚጠቀሙም ይጠቁማሉ፡፡ ተማሪው ደግሞ ቀደም ብሎ ስለመፅሐፉ ይዘቶች አጠቃላይነትና ለደረጃው አለመመጠናቸውን ከሰጠው አስተያየት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከመፅሐፉ ቁጥር ማነስ የተነሳ ከነጭራሹ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፅሐፍ መኖሩንም የሚያውቁ ተማሪዎች በጣም ውስን እንደሆኑ ጭምር ይጠቁማሉ፡፡ እንደተማሪዎቹ አስተያየት አዘውትረው የሚጠቀሙት ማጣቀሻ መፅሐፍት የአንደኛ ሳይክል መርሀ-ትምህርቶችና መፅሐፍቶቻቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## 4.3. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር የክፍል ውስጥ ተራክቦን በተመለከተ፣

### 4.3.1. ዝንባሌ፣ ፍላጎትና አመለካከት፣

የተማሪው አመለካከት፣

ሠንጠረዥ ፪፣ የተማሪው አመለካከት መረጃ ጥንቅር፣

| መም/ማ/ ተቋም | ክፍል መለያ | የተማሪው ብዛት | ነጥብ | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| አዋሣ | ቢ | 40 | 1255 | 3.9 |
| | ኤፍ | 46 | 1400 | 3.9 |
| አርባ-ምንጭ | ቢ$_7$ | 46 | 1384 | 3.8 |
| ድምር | | 132 | 4039 | 11.6 |
| ጥቅል አማካይ | | | | 3.9 |

(grand mean) ጉልህ አማካይ ነጥብ > 3.0

ለተማሪው በቀረበው መጠይቅ ጥቅል አማካይ 3.9 ያመላክታል:: ይህ ደግሞ ከ3.0 ነጥብ በላይ በመሆኑ ተማሪው አመለካከቱ አዎንታዊ እንደሆነ ይጠቁማል:: ሶስቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑም ተማሪው በቋንቋው፣ በቋንቋው ትምህርትና በመምህርነት ሙያው ላይ ያለው አመለካከት አዎንታዊ እንደሆነ ይገልፃሉ:: ከተማሪዎቻቸውም ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ መሆኑን ጭምር በሰጡት አስተያየት አረጋግጠዋል::

### የመምህሩ አመለካከት፣

መምህራን ሙያቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉት ጥረት፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የሰዓት አከባበር፣ ታዛዥነት፣ ቅንነትና ተባባሪነት ሁሉ ስለቋንቋው፣ ስለቋንቋው ትምህርትና ስለሙያው አንድ መምህር ያለውን ፍላጎት፣ ዝንባሌና አመለካከት በጉልህ ያሳያል፤ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም ከተጠቀሱት ነጥቦች ያጓደሉት ስለሌለ አመለካከታቸው አዎንታዊ እንደሆነ የተቋማቱ ርዕሰ-መምህራንና የቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ያረጋግጣሉ:: መምህራን ራሳቸው ስለአመለካከታቸው በተጠየቁበት ወቅት ከዚህ የተለየ መልስ አልሰጡም፤ ግን በክፍለ-ጊዜ ሥርጭት በተለይ የአርባ-ምንጭ/መም/ማ/ተቋም መምህር ከአካባቢው የአየር ሁኔታ ጋር ሲያገናዝብ ቅሬታ እንዳለውና ከሰዓት በኋላ መሥራት እንደማይቻል ከሰጠው አስተያየት መገንዘብ ተችሏል:: ተማሪዎቹም በሰጡት አስተያየት የአርባ-ምንጭ/መም/ማ/ተቋም መምህር ብቻ ሳይሆን የአዋሳ መም/ማ/ተቋም መምህራኑም አዘውትረው ከሰዓት በኋላ ከሥራ እንደሚቀሩ፣ እንደሚያረፍዱ፣ የመሰላቸት ባሕርይ እንደሚታይባቸውና በክፍል ውስጥ እንደሚነጫነጩ ይጠቁማሉ::

### 4.3.2. የተማሪው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣

ሠንጠረዥ 3፣ የተማሪው የክፍል ተሳትፎ መረጃ ጥንቅር፣

| መም/ ማ/ ተቋም | ክፍል መለያ | የተማሪ ብዛት | የፅሑፍ መጠይቅ | | በምልከታ የተገኘ መረጃ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አንደኛ ሳምንት | | ሁለተኛ ሳምንት | | ሦስተኛ ሳምንት | | ድምር | |
| | | | ነጥብ | አማካይ ነጥብ | ብዛት | አማካይ | ብዛት | አማካይ | ብዛት | አማካይ | ብዛት | አማካይ |
| አዋሳ | ቢ (B) | 40 | 1533 | 2.7 | 76 | 2.57 | 59 | 1.96 | 66 | 2.2 | 201 | 2.4 |
| | ኤፍ (F) | 46 | 1538 | 2.6 | 60 | 2.1 | 55 | 1.83 | 47 | 1.56 | 162 | 1.8 |
| አርባ-ምንጭ | ቢ$_7$ ($B_7$) | 46 | 1612 | 2.5 | 44 | 1.47 | 59 | 1.96 | 51 | 1.7 | 154 | 1.7 |
| ድምር | | 132 | 4728 | 7.8 | 180 | 6.14 | 173 | 5.75 | 164 | 5.46 | 517 | 5.9 |
| ጥቅል አማካይ ነጥብ | | | | 2..6 | ጥቅል አማካይ ነጥብ | | | | | | | 1.96 |

ጉልህ ጥቅል አማካይ > 2.0

በፅሑፍ መጠይቅ ከተማሪው ከተሰበሰበው መረጃ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የጠቅላላው ተማሪ ጥቅል አማካይ ነጥብ 2.6 ነው:: ይህ ደግሞ ከ2.0 ነጥብ በላይ በመሆኑ የተማሪውን የክፍል እንቅስቃሴ ደህና ሊያስመስለው ይችላል:: ሁኔታውን በዝርዝር ለማየት በየተቋማቱ ለአንዳንድ ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች ተማሪው በክፍል ውስጥ በጭራሽ ተግባራዊ የማያደርጋቸው ድርጊቶች፣ ክንውኖችና ልምምዶች እንዳሉ ይጠቁማሉ፤

<u>ለምሳሌ</u>:- ክፍል ቢ ለመጠይቅ 7፣8 እና 9

ክፍል ኤፍ ለመጠይቅ 4፣ 7 እና 8

ክፍል ቢ$_7$ ለመጠይቅ 4፣7፣8 እና 13 ከተሰጡት መልስ መረዳት የሚቻለው የተማሪው አማካይ ነጥብ ከ2.0 ነጥብ በታች ሆኖ እናገኘዋለን (አባሪ ሰን ያገናዝቧል):: በተጨማሪም የያንዳንዱ ተማሪ ነጥብ በስታቲስቲክስ የስሌት ቀመር ሲታይ ተማሪው በተቋም ካመጣው የአማርኛ ትምህርት መጨረሻ ውጤት ጋር ምንም ዝምድናና አስተዋፅኦ እንደሌለው ይጠቁማል (ይህ በ4.4 በዝርዝር የሚቀርብ ይሆናል)::

በክፍል ውስጥ ምልከታው የተሰበሰበው መረጃ የያንዳንዱ ክፍል የሶስት ሳምንታት ጥቅል አማካይ ነጥብ 1.96 እንደሆነ ያመላክታል:: ከዚህም ሌላ በጠቅላላው 79 ተማሪዎች በሶስቱ ክፍሎች በተጠቀሰው ጊዜ እንቅስቃሴ አሳይተዋል:: እነዚህ ለንግግር የተጠቀሙት 65 ደቂቃ (1:05 ሰዓት) ሆኗል (አባሪ ሬን ያገናዝቧል):: የክፍል ውስጥ ምልከታውን ያደረጉ ስድስቱ የትምህርት ባለሙያዎች ምልከታውን ባደረጉባቸው ክፍለ-ጊዜያት በሶስቱም ክፍሎች የተማሪው ተሳትፎ ደካማ እንደሆነ ከሰጡት የግል አስተያየታቸው ማወቅ ተችሏል:: መምህራኑ፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎቹና ርዕሰ-መምህራኑም የሰጡት ሀሣብ ከገምጋሚዎቹ ጋር ተመሳሳይ እንደ ሆነ በቃለ-መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች ያመላክታሉ::

### 4.3.3. <u>የመምህሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣</u>

<u>ሠንጠረዥ 4፣ የመምህሩ የክፍል ተሳትፎ መረጃ ጥንቅር፣</u>

| መም/ ማ/ ተቋም | ክፍል መለያ | የተማሪው | የፅሑፍ መጠይቅ | | በምልከታ የተገኘ መረጃ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አንደኛ ሳምንት | | ሁለተኛ ሳምንት | | ሦስተኛ ሳምንት | | ድምር | |
| | | ብዛት | ነጥብ | አማካይ ነጥብ | ብዛት | አማካይ | ብዛት | አማካይ | ብዛት | አማካይ | ብዛት | አማካይ |
| አዋሣ | ቢ | 40 | 2297 | 2.8 | 79 | 2.63 | 64 | 2.13 | 73 | 2.43 | 216 | 2.39 |
| | ኤፍ | 46 | 1938 | 2.1 | 52 | 1.73 | 51 | 1.7 | 48 | 1.66 | 151 | 1.67 |
| አርባ-ምንጭ | ቢ$_7$ | 46 | 1989 | 2.0 | 41 | 1.37 | 49 | 1.63 | 46 | 1.53 | 136 | 1.51 |
| ድምር | | 132 | 6224 | 6.9 | 172 | 5.73 | 154 | 5.46 | 167 | 5.62 | 503 | 5.6 |
| ጥቅል አማካይ ነጥብ | | | | 2..3 | ጥቅል አማካይ ነጥብ | | | | | | | 1.87 |

ጉልህ ጥቅል አማካይ > 2.0

ለተማሪው ከቀረበው የፅሑፍ መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ የተጠናቀረው መረጃ 2.3 ነጥብ ጥቅል አማካይ ነጥብ ያመላክታል:: ይህ ውጤት ከ2.0 ነጥብ በላይ በመሆኑ የመምህሩን የክፍል እንቅስቃሴ ደህና ሊያስመስለው ይችል ይሆናል:: ነገር ግን የያንዳንዱ የክፍል እንቅስቃሴ በዝርዝር ሲታይ በክፍል ውስጥ በጭራሽ ተግባራዊ የማይሆኑ የማስተማር ስልቶችን እናገኛቸዋለን:: እነዚህም መምህራኑ በክፍለ-ጊዜያቸው ጥሩ ተሳትፎ እንደማያደርጉ ይጠቁማሉ፤

<u>ለምሳሌ</u>:- ክፍል ቢ ለመጠይቅ 10 እና 11

ክፍል ኤፍ ለመጠይቅ 2፣ 3፣ 4፣ 9፣ 10፣ 11 እና 14

ክፍል ቢ$_7$ ለመጠይቅ 2፣ 3፣ 4፣ 9፣ 10፣ 11 እና 14 የሰጡት መልስ

አጠቃላይ አማካይ ነጥብ ከ2.0 ነጥብ በታች ሆኖ እናገኛለን (አባሪ ሰን ያገናዝቧል):: በተጨማሪም በያንዳንዱ ተማሪ ስለመምህሩ የክፍል ተሳትፎ የተሰጠው ነጥብ በስታቲስቲክስ የስሌት ቀመር ሲታይ ከተቋሙ የተማሪው ውጤት ጋር ምንም ዝምድና የሌለውና ለትምህርቱ ቅስሞሽ ምንም አስተዋፅኦ እንዳላደረገ ይጠቁማል (ይህንን በተመለከተ በ4.4 በዝርዝር የሚቀርብ ይሆናል)::

በክፍል ውስጥ ምልከታው በሶስት ሳምንታት የሶስቱ መምህራን የክፍል ተሳትፎ ጥቅል አማካይ ነጥብ 1.87 እንደሆነ ያሳያል:: እንደገምጋሚዎቹ መምህራኑ በነዚህ ሳምንታት ለክፍል ውስጥ ተሳትፎ የተጠቀሙት ጊዜ 295 ደቂቃ (4:55 ሰዓት) ይሆናል:: የባከነ ጊዜ 45 ደቂቃ ብቻ ሆኖ ተገኝቷል (አባሪ ረን ይመለከቷል):: ገምጋሚዎቹ በሰጡት የግል አስተያየት የመምህራን ተሳትፎ ከተማሪው የጎላ ነበር ብለዋል:: የመማር-ማስተማር ስልት (ስነ-ዘዴ) ተማሪ-መራሽ መሆን አለበት በማለት ዕጩ መምህራኑን ሲያስተምሩ ተደምጠዋል፤ ነገር ግን ራሳቸው ተግባራዊ አላደረጉም ሲሉ የመምህራንን የክፍል ተሳትፎ ሁኔታ ገምጋሚዎች በተጨማሪ ይገልፃሉ:: የዚህ ጥናት አቅራቢም እያንዳንዱን የግምገማ ሁኔታ ይከታተል በነበረበት ተቋም የገምጋሚዎች አስተያየት (በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ተሳትፎ የሰጡትን አስተያየት) ትክክለኛነት አረጋግጧል::

በቃለ-መጠይቁ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለክፍል ተሳትፎአቸው ተጠይቀው መልስ ሲሰጡ፤ ተማሪውን በደንብ በቡድን አደራጅቶ ለማወያየትና ለማከራከር እንዲሁም ድርጊቶችን፣ ክንውኖችንና ልምምዶችን በሥርዓት ለማካሄድ ጊዜ የለም፤ በዕለታዊ የትምህርት ዝግጅት መሠረት እንኳን ለመከወን የክፍለ-ጊዜ ርዝማኔ 45 ደቂቃና በሳምንት የአማርኛ ክፍለ-ጊዜ ሶስት ብቻ በመሆኑ አይበቃም:: ስለዚህ ሁሉን

ነገር ራሳችን እንድንፈፅም ሁኔታው ያስገድደናል ይላሉ:: በዚህም ገምጋሚዎቹ የሰጡት ሀሣብ እውነት መሆኑን ያረጋግጣል:: የቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራንም ይህኑ ሀሣብ በሰጡት መረጃ ይጠቁማሉ::

### 4.3.4. የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች ስልታዊ አቀራረብ፣

ሠንጠረዥ 5፣ የክፍል ውስጥ ክንውኖች መረጃ ጥንቅር፣

| መም/ማ/ ተቋም | ክፍል መለያ | የተማሪው ብዛት | ነጥብ | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| አዋሳ | ቢ | 40 | 224 | 1.12 |
| | ኤፍ | 46 | 218 | 0.98 |
| አርባ-ምንጭ | $ቢ_7$ | 46 | 240 | 1.10 |
| ድምር | | 132 | 682 | 3.2 |
| ጥቅል አማካይ | | | | 1.1 |

(grand mean) ጉልህ አማካይ ነጥብ > 0

በተማሪው መጠይቅ የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች ስልታዊ አቀራረብን በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት 1.1. ጥቅል አማካይ እንደሆነ ያሳያል::

በምልከታው ቅፅ አማካኝነት የቀረቡ መረጃዎች ጥንቅርና የገምጋሚዎች አስተያየት በክፍል ውስጥ በሶስቱም ሳምንታት በሶስቱ ክፍሎች የቀረቡት የተማሪውና የመምህሩ የክፍል እንቅስቃሴ ስልታዊ እንዳልሆነ ይጠቁማል፤ በተለይ በክፍል ኤፍና $ቢ_7$ የቡድን ሥራዎች በጭራሽ እንዳልታዩ መረጃው ያረጋግጣል (አባሪ ረን ያገናዝቧል)::

የተቋማቱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን በቃል ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣ በመማር-ማስተማሩ ሂደት በተለይ በቋንቋ ትምህርት ድርጊቶች፣ ክንውኖችና ልምምዶች በስርዓት ሲቀርቡ አልታዩም ይላሉ::

መምህራን ደግሞ ለክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ጊዜ ያስፈልገናል:: የጊዜ ዕጥረቱም ከማስተማር ልምምድ (Practice teaching) ጋር የተያያዘ ችግር ነው:: ይኸውም የማስተማር ልምምድ እንደአንድ ኮርስ (የትምህርት ዓይነት) ውጤት ያለው ሆኖ ግን በመርሀ-ትምህርቱ ላይ በዕቅድ ደረጃ ያልተያዘና ጊዜም ያልተመደበለት በመሆኑ በመርሀ-ግብሩ ለማካተት በጣም አስቸግሯል:: ልምምዱ የሚታወቀው ግንቦት ወር ሲመጣ በመሆኑ ከዚያ በፊት ያሉት ክፍለ-ጊዜያት በሙሉ በግድ መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል:: በተጨማሪ ደግሞ BESO (Basic Education System Overhoal)

መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ-ተሐዲሶ አማካሪዎች በየወሩ ተማሪው ለቅኝት ወይም ለምልከታ (assessment) በአንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች እንዲወጣ በመርሀ-ግብሩ ስላስያዙ በተለይ የቋንቋን ክፍል በመማር-ማስተማር ሂደቱ ድርጊቶችን፣ ክንውኖችንና ልምምዶችን ስልታዊ አቀራረብ በሥርዓት በሥራ ላይ ለማዋል አስቸጋሪነት አለው ብለው የሁለቱ ተቋማት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ችግሮቻቸውን በመለሱት መልስ አስገንዝበዋል:: ተማሪውም ቢሆን እንደመምህራኑ የጊዜ ዕጥረት እንዳለ ይጠቁማል፤ በተጨማሪም መምህሮቻቸው በሥርዓት እንደማያስተምሯቸው በአስተያየታቸው አረጋግጠዋል::

#### 4.3.5. የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሚና፣

በምልከታው ለክፍለ-ጊዜያቱ ተስማሚ የማስተማሪያ መሣሪያዎች እንዳልቀረቡ በምልከታው ቅፅ የተሰበሰበው መረጃና የገምጋሚዎቹ አስተያየት ያስገነዝባል:: በዚህም መምህሩ በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት የማስተማሪያ መፅሐፍ ሲጠቀም አልታየም፤ የራሱን ማስታወሻ እንጂ:: የመርጃ መሣሪያዎችን እንደማይጠቀሙ ሁሉም የምልከታ ቅፁ መረጃ ያመላክታል:: የመምህሩ ዕለታዊ የትምህርት ዝግጅትም ተስማሚና አግባብነት ያላቸውን መርጃ መሣሪያዎችን የማይጠቀሙ ሆነው ተገኝተዋል (አባሪ ሸን ያገናዝቧል)::

በፅሑፉ መጠይቁ ተማሪው የማስተማሪያ መፅሐፍ ዕጥረት እንዳለ፣ ይዘቱም እንደማይመጥነው፣ መምህራን የመርጃ መሣሪያ የግድ ሠርቶ እንዲያመጣ እንደሚያስቸግሩትና ለማጣቀሻ የሚጠቀመው መፅሐፍ ቢኖር የአንደኛ ሳይክል (ከ1-4) ት/ቤቶች መርሀ-ትምህርቶችና መፅሐፍቶቻቸውን እንደሆኑ ከሰጠው ሀሣብ ማገናዘብ ይቻላል::

በቃለ-መጠይቁ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በቂ የማስተማሪያ መሣሪያ እንደሌለ የአዋሳና የአርባ-ምንጭ መም/ማ/ተቋማት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን ጠቁመዋል::

## 4.4. <u>መርሀ-ትምህርቱን በመተግበር ከሚገኘው ውጤት አንፃር ሲታይ፣</u>

### 4.4.1. <u>የተማሪው በአስተሳሰቡና በአሠራሩ ለውጥ ማምጣቱን በተመለከተ፣</u>

<u>ሠንጠረዥ ፩ የተማሪው ትንበያ መረጃ ጥንቅር፣</u>

| መም/ማ/ ተቋም | ክፍለ መስያ | የተማሪው ብዛት | ነጥብ | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| አዋሣ | ቢ | 40 | 218 | 0.9 |
| | ኤፍ | 46 | 203 | 0.7 |
| አርባ-ምንጭ | ቢ7 | 46 | 214 | 0.8 |
| ድምር | | 132 | 635 | 2.4 |
| ጥቅል አማካይ | | | | 0.8 |

(grand mean) ጥቅል አማካይ ነጥብ > 0

በፅሑፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ጥንቅር ውጤት 0.8 እንደሆነ ያመላክታል::

በቃል-መጠይቅም የተቋማቱ የቋንቋ መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን በተማሪው ላይ ስለሚታየው የባሕርይ ለውጥ ተጠይቀው እንደመለሱት ተቋማቱ ብቃት ያላቸውን መምህራን ለማፍራት ጥረት እንደሚያደርጉና ሠልጣኙም ጥሩ የባሕርይ ለውጥ ያመጣል ብለው እንደሚያምኑ ይጠቅሳሉ:: ተማሪውም ብቃት ያለው የቋንቋ መምህር ሆኜ እወጣለሁ ብሎ ያምናል:: ሆኖም ቅድመ-ሁኔታዎችና የክፍል ተራክቦ የሚመቻችበት ማለት፤ የመርሀ-ትምህርቱ አጠቃላይ ገፅታ፣ የተማሪው ምልመላ፣ የመምህራን ምደባ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሥርጭት፣ ተማሪውንና መምህሩን የሚያነቃቁ ሁኔታዎች ካልተመቻቹ በስተቀር ጠንካራና ብቃት ያላቸውን መምህራን ማፍራት እንደማይቻል የትምህርት ባለሙያዎቹ ሳይጠቅሱ አላለፉም::

### 4.4.2. <u>በተማሪዎቹ አንፃር የትምህርት ዓላማው ግብ መምታቱን በተመለከተ፣</u>

<u>ከሥልጠናው በኋላ የተገኘው ውጤት፣</u> 72%ቱ ተማሪ ከ55-74፣ 21%ቱ ተማሪ ከ75-89፣ 5%ቱ ተማሪ ከ45-54 እና 2%ቱ ተማሪ ከ90-100 ከመቶ እንዳለው መረጃው ያመላክታል (አባሪ መን ያገናዝቧል)::

ከተማሪው፣ ከመምህራን፣ ከቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ከርዕሰ-መምህራን የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በተቋሙ በተማሪው የተገኘው የመጨረሻ ውጤት የሚከተሉት ተፅዕኖዎች አሉት:: እነርሱም፤

- የተቋማቱ የግምገማ ስልት

<u>ለምሳሌ</u>:- አዋሳ መም/ማ/ተቋም የሚጠቀመው ስልት፤

- አማካይ ከ60%
- አጠቃላይ ከ40% ወስዷል::

አርባ-ምንጭ መም/ማ/ተቋም ደግሞ፤

- አማካይ ከ80%
- አጠቃላይ ከ20% ይዟል።

ከዚህም በላይ እንደተማሪው መረጃ የሚቀርቡት ሙከራዎችና ፈተናዎች ከተማሪው ትምህርት (lesson) ጋር የማይገናኝና የማይጣጣም በመሆኑ ሁልጊዜ ተማሪው በፈተና እንደሚወድቅ ይጠቁማል። መምህራን ግን ይህንን ሀሣብ ያስተባብላሉ፤ የምንፈትነው ካስተማርነው ትምህርት ነው ብለው። የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን በዓላማ-ይዘት ማመሳከሪያ ቅፅ **(table of specification)** እንደሚቆጣጠሩ ያስገነዝባሉ።

- የመምህሩ የግል አመለካከት፣

መምህራን በውጤት አሰጣጥ አድሎ ያደርጋሉ ብሎ ተማሪው ይጠቁማል። ይህ አሰራር በአንዳንድ መምህራን አካባቢ እንደሚታይ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራንም በሰጡት ሀሣብ ያረጋግጣሉ።

- የመምህሩ የሥራ አፈፃፀም፣

መምህሩ ጥሩ አስተምሯል የሚባለው ብዙ ተማሪዎች በትምህርቱ ማለፍ ሲችሉ መሆኑ በተቋሙ እንደሚታመን ከመምህራን፣ ከርዕሰ-መምህራንና ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎች የተገኙ መረጃዎች ያመላክታሉ።

- የተማሪው ተፅዕኖ፣

ተማሪው መምህሩን ስለሚገመግም በተማሪው ውጤት ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖር ከተማሪውም ሆነ ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህም ሌላ ተማሪው ውጤት ለማግኘት በኃይል (በጉልበት) ሲጠቀም አጥኚው አዋሳ መም/ማ/ተቋም በተገኘበት አጋጣሚ ለማየት ችሏል። መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራንም ተማሪው በኃይል መጠቀም እንደሚፈልግ ይጠቁማሉ።

- የተቋማቱ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ፣

ተቋማቱ ካላቸው አሠራር ተማሪው እንዲወድቅበት አለመፈለጉና ለሚያጠፋው ጥፋት ወሳኝ እርምጃ አለመውሰዱ ከመምህራንና ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎች የተገኙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ። አጥኚውም በአዋሳ መም/ማ/ተቋም በመምህሩ ላይ ጡንቻውን ለማሳየት የሞከረው ተማሪ ያለምንም ቅጣት መለቀቁን በአካል ተገኝቶ ሊያረጋግጥ ችሏል።

በጠቅላላው፣ በተቋሙ የተማሪው ውጤት ከላይ በተጠቀሱት አሉታዊ ምክንያቶች ተፅዕኖ የተገኙ እንጂ የተማሪው የግሉ ጥረት ውጤት አለመሆናቸውን የቀረቡት መረጃዎች ያመላክታሉ፤ ከዚህም በላይ መርሀ-ትምህርቱ በትክክል በሥራ ላይ ውሎ የመጣ አለመሆናቸውንም እስካሁን የቀረቡት መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

ከዚህም በላይ ቅድመ-ሥልጠና ልምዱ፣ የክፍል ውስጥ ተራክቦውና ተማሪው በተቋም ያመጣው ውጤት ያላቸው ዝምድናና ድህረት (Correlation and Regression) በስታቲስቲክስ ስሌት ቀመር የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሀ. ቅድመ-ሥልጠና ልምድ፤

$X_1$ = ከ9-12 ያማርኛ ውጤት አማካይ ውጤት

$X_2$ = በ12ኛ ክ/መ/ፈ. ያማርኛ ውጤት

$X_3$ = የ12ኛ ክ/መ/ፈ. ጥቅል አማካይ ውጤት

$X_4$ = የመመልመያ መስፈርቶች ጥቅል ውጤት

ለ. የክፍል ውስጥ ተራክቦ፤

$X_5$ = የተማሪው የክፍል ተሳትፎ ነጥብ

$X_6$ = የመምህሩ የክፍል ተሳትፎ ነጥብ

ሐ. ድህረ-ሥልጠና ልምድ፤

Y = ተማሪው ከሥልጠና በኋላ ያመጣው ውጤት

በዚህ ሥራ ከ$X_1$-$X_6$ እንደ ኢ-ጥገኛ ተላውጦዎች (independent variables) ሲሆኑ፣ Y ደግሞ እንደ ጥገኛ ተላውጦ (dependent variable) ሆኖ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ፯. የማዕከላዊ ዝንባሌ መለኪያ መረጃ

**(Measure of Central Tendency)፣**

| Variables | Mean | Standard deviation | Minimum | Maximum | Range |
|---|---|---|---|---|---|
| $X_1$ | 63.35 | 6.64 | 45.00 | 81.00 | 36 |
| $X_2$ | 1.95 | 0.75 | 0.00 | 4.00 | 4 |
| $X_3$ | 2.28 | 1.83 | 1.20 | 3.60 | 2.4 |
| $X_4$ | 50.50 | 8.77 | 35.00 | 77.00 | 42 |
| $X_5$ | 31.99 | 5.38 | 19.00 | 51.00 | 32 |
| $X_6$ | 38.35 | 8.04 | 12.00 | 60.00 | 48 |
| Y | 67.38 | 8.68 | 48.00 | 90 | 42 |

መረጃው፣ የ$X_4$ እና የY ርቀት መለኪያ (Range) 42 ነጥብ ሥርጭታቸው ተመሳሳይ እንደሆነ ያመላክታል።

ሠንጠረዥ 8. የዝምድና መለኪያ መረጃ (**Zero Order Correlation**)፣

| Variables | $X_1$ | $X_2$ | $X_3$ | $X_4$ | $X_5$ | $X_6$ | Y |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| $X_1$ | 1.000 | | | | | | |
| $X_2$ | 0.3616* | 1.000 | | | | | |
| $X_3$ | 0.1084 | -0.0417 | 1.000 | | | | |
| $X_4$ | 0.2818* | 0.1631 | 0.2357* | 1.000 | | | |
| $X_5$ | -0.1490 | -0.1220 | -0.0387 | -0.2211* | 1.000 | | |
| $X_6$ | -0.1220 | -0.1069 | -0.0677 | -0.2353* | 0.3130* | 1.000 | |
| Y | 0.3315* | 0.2884* | 0.0156 | 0.3887* | -0.0877 | -0.0684 | 1.000 |

$P < 0.05$

* ጉልህ ነጥቦችን ያመላክታል።

በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፤ $X_1$ ከ$X_2$፣ ከ$X_4$ እና ከY፣ $X_2$ ከY፣ $X_3$ ከ$X_4$፣ $X_4$ ከ$X_5$፣ ከ$X_6$ እና ከY፣ $X_5$ ከ$X_6$ ጋር መጠነኛ ዝምድና እንዳላቸው መረጃው ያመላክታል።

ሠንጠረዥ 9. የብዙዮሽ ድህረት መለኪያ መረጃ (**Mulutiple regression**)

**/A Computer Solution for Six Predictor Variables/**፣

(n = 125)

| Multiple Correlation and related values | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Multiple R = 0.47 | Analysis of Variance | | | |
| $R^2$ = 0.22 | | DF | Sum of Squares | Mean Squares |
| Adjusted $R^2$ = 0.18 | regression | 6 | 2073.33 | 345.56 |
| Standard error = 7.85 | residual | 118 | 7266.23 | 61.58 |
| | F = 5.60 | | Sign. F = 0.0000 | |

| Values in the final step | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | Coefficient | | | | |
| Variables | B Value | Standard error (SEB) | Beta | t Value | Significant t |
| Y | 28.55 | 9.79 | — | 2.92 | 0.0042* |
| $X_1$ | 0.28 | 0.12 | 0.22 | 2.33 | 0.0186* |
| $X_2$ | 1.12 | 1.02 | 0.10 | 1.10 | 0.2717 |
| $X_3$ | -0.39 | 0.40 | -0.08 | -0.97 | 0.3345 |
| $X_4$ | 0.34 | 0.09 | 0.34 | 3.77 | 0.0002* |
| $X_5$ | 0.03 | 0.14 | 0.02 | 0.20 | 0.8435 |
| $X_6$ | 0.04 | 0.09 | 0.04 | 0.44 | 0.6603 |

$F < 0.05$

1. * ጉልህ ነጥቦችን ያመላክታል።
2. ከጉልሁ t ዋጋ በስተቀር የሌሎቹ ከነጥብ በኋላ ወደ ሁለት አሀዞች (**digits**) ተጠጋግተዋል።

<u>መፍቺያ (Key)</u>፤

**Multiple = የብዙዮሽ ዝምድናና ድህረት መለኪያ**

**Coeffient of determination ($R^2$) = መግለጫ (ውሳኔ የሚያሰጥ) መለኪያ**

**degree of freedom (df) = የነፃነት ደረጃ**

**Regression Equation = የብዙዮሽ ድህረት እኩላ (ቀመር)**

**Significant = ጉልህነት**

**Mean Square = አማካይ ካሬ**

**Critical Point = ወሳኝ ነጥብ**

**Standard error = መደበኛ ስህተት**

**Analysis of Variance = ልይይት ትንተና**

**regression Coefficient = የድህረት መለኪያ**

**population size = የተሳታፊዎች ብዛት**

**Equation = እኩላ (ቀመር)**

ለብዙዮሽ ድህረት መለኪያ በተመረጠው እኩላ የሠንጠረዡ መረጃ እንደሚያመላክተው፤

$$Y = 0.28X_1+1.12X_2+(-0.39X_3)+0.34X_4+0.03X_5+0.04X_6+28.55$$

ይሆናል።

የብዙዮሽ ዝምድናና ድህረት መለኪያው (R) = 0.47፣ የብዙዮሽ መለኪያ ካሬው ወይም መግለጪያው ($R^2$) = 0.22 እንደሆነ መረጃው ያሳያል፤ $R^2$ 22% መሆኑ ኢ-ጥገኛ ተላውጦዎች ለጥገኛ ተላውጠው አንድ ነገር እንደረዱ ወይም እንደሰጡ ይገልፃል።

የብዙዮሽ ዝምድናና ድህረት መለኪያው ጉልህ ለመሆኑ የF ዋጋ ሲታይ፤

$$F = \frac{R^2/K}{(1-R^2)/(n-k-1)}$$

**$R^2$ = Coeffient of determination**
**k= Number independent variables**
**n = Population size**

$R^2 = 0.22$
$k = 6$
$n = 125$

ስለዚህ $F = \frac{0.22/6}{(1-022) / 125-6-1)}$

$F = \frac{0.0366}{0.0066}$

F = 5.60 ይሆናል::

በስሌቱ መሠረት የF ሥርጭት በ6 እና በ118 የነፃነት ደረጃ ሲታይ 5.60 ያሳያል፤ በአልፋ 0.05 የFን ጉልህነት የሚገልፀው ወሳኝ ነጥብ 2.17 ነው:: በስሌቱ የተገኘው የF ዋጋ ከወሳኝ ነጥቡ ይበልጣል:: በቀረበው ሠንጠረዥ የF ጉልህነት 0.0000 ያመላክታል:: ይህ ማለት ደግሞ የይሆንታ ግምቱን (Probability) ከ0.0001 በታች ስለሚያደርገው ኢ-ጥገኛ ተላውጦዎቹ በሕብረት ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ያላቸው ዝምድናና ድህረት ከዜሮ በላይ መሆኑን ያረጋግጣል::

የያንዳንዱ ኢ-ጥገኛ ተላውጦ ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ያለውን ዝምድናና ድህረት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የt ዋጋ ሲታይ፤

$t = \frac{B}{SEB}$ B = Value of B.
SEB = Standard error

ለምሳሌ :- $X_1$ ከY ጋር ያለውን ዝምድናና ድህረት ለማወቅ፤

B = 0.28
SEB = 0.12

ስለዚህ $t = \frac{0.28}{0.12}$

t = 2.33 ይሆናል::

ስሌቱ በ118 የነፃነት ደረጃ የt ዋጋ 2.33 እንደሆነ ያሳያል፤ በአልፋ 0.05 የtን ጉልህነት የሚገልፀው ወሳኝ ነጥብ 1.98 ነው:: በስሌቱ የተገኘው የt ዋጋ ከወሳኝ ነጥቡ ይበልጣል:: በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ደግሞ የt ጉልህ ነጥብ 0.0186 እንደሆነ ያመላክታል:: ይህም $X_1$ ከሌሎቹ ኢ-ጥገኛ ተላውጦዎች ጋር ሆኖ በሕብረት ለY አንድ ነገር እንደሚረዳ ያረጋግጣል:: በተመሣሣይ ሁኔታ $X_4$ም ለY አስተዋፅኦ እንዳለውና የቀሩት $X_2$፣ $X_3$፣ $X_5$፣ እና $X_6$ ግን ምንም እንደማያደርጉ መረጃው ይጠቁማል::

<u>ሠንጠረዥ 10. የተማሪውን ውጤት ስመተንበይ የሚያስችሉ ተላውጦዎች መረጃ፣</u>

(n = 125)

| Multiple Correlation and related values | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Multiple R = 0.45 | Analysis of Variance | | | |
| $R^2$ = 0.20 | | DF | Sum of Squares | Mean Squares |
| Adjusted $R^2$ = 0.19 | regression | 2 | 1910.89 | 955.45 |
| Standard error = 7.80 | residual | 122 | 7428.68 | 60.89 |
| | F = 15.25 | | Sign. F = 0.0000 | |

| Values in the final step | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | Coefficient | | | | |
| Variables | B Value | Standard error (SEB) | Beta | t Value | Significant t |
| Y | 31.38 | 7.09 | __ | 4.43 | 0.0000* |
| $X_1$ | 0.32 | 0.11 | 0.24 | 2.91 | 0.0049* |
| $X_4$ | 0.32 | 0.08 | 0.32 | 4.00 | 0.0002* |

$F < 0.05$

1. * ጉልህ ነጥቦችን ያሳያል::
2. ከጉልሁ t ዋጋ በስተቀር የሌሎቹ ከነጥብ በኋላ ወደ ሁለት አሀዞች (digits) ተጠጋግተዋል::

ለብዙዮሽ ድህረት በተመረጠው እኩላ መሠረት የሠንጠረገፉ መረጃ እንደሚያመላክተው፤

**$Y = 0.32X_1+0.32X_4+31.38$ ይሆናል::**

በስሌቱ መሰረት የ**F** ዋጋ በ2 እና በ122 የነፃነት ደረጃ 15.25 ያሳይል፤ በአልፋ 0.05 የ**F**ን ጉልህነት የሚያመላክተው ወሳኝ ነጥብ 3.07 ነው:: የ**F** ዋጋ ከወሳኝ ነጥቡ ይበልጣል:: በቀረበው ሠንጠረዥ የ**F** ጉልህነት 0.0000 እንደሆነ ይገልፃል፤ ይህ ማለት ደግሞ የይሆንታ ግምቱን ከ0.0001 በታች ስለሚያደርገው **$X_1$**ና **$X_4$** በሕብረት ከ**Y** ጋር ያላቸው ዝምድናና ድህረት ከዜሮ በላይ መሆኑን ያረጋግጣል::

**$X_1$** እና **$X_4$** እያንዳንዳቸው ከ**Y** ጋር ያላቸው ዝምድናና ድህረት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የ**t** ዋጋ ሲታይ፤

በሠንጠረገፉ ላይ በቀረበው መረጃ መሠረት፣ በ122 የነፃነት ደረጃ የ**t** ዋጋ ለ**$X_1$**=2.91 እና ለ**$X_4$**=4.00 ያሳያል፤ በአልፋ 0.05 የ**t**ን ጉልህነት የሚያመላክተው ወሳኝ ነጥብ የሁለቱም 1.96 ነው:: በስሌቱ የተገኙት የ**t** ዋጋዎች ከወሳኝ ነጥቡ ይበልጣሉ:: በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ደግሞ **$X_1$**=0.0049 ና **$X_4$**=0.0002 የጉልሁን **t** ነጥብ ይገልፃል:: ስለዚህ **$X_1$**ና **$X_4$** በተናጠልም ሆነ በሕብረት ለ**Y** ድጋፍ እንደሚያደርጉ መረጃው ያረጋግጣል::

# ክፍል አምስት፣ ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1. <u>ማጠቃለያ</u>፣

ለዚህ ጥናት መሠረታዊነት አሥር ጥያቄዎች በክፍል አንድ ቀርበዋል:: የመስኩ ምሁራን እንደእምነታቸውና አመለካከታቸው በያንዳንዱ ጥያቄ አንፃር ያላቸውን ሀሣብ፣ መርሀ-ትምህርትን በመተግበር የቅድመ-ሁኔታዎች፣ የክፍል ውስጥ ተራክቦና የሚገኘው ውጤት ምን ያህል ሂደቱን እንደሚወስን በዝርዝር በክፍል ሁለት ተካቷል:: በክፍል ሶስት በጥያቄዎቹ መሠረት መረጃ ያስገኛሉ የተባሉት ሶስት ዋና ዋና መሣሪያዎች በሥራ ላይ ውለዋል:: በመሣሪያዎቹ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በክፍል አራት ተተንትነዋል:: በዚህ ክፍል ደግሞ በተተነተኑት መረጃዎች መሠረት፣ የተነሱት ጥያቄዎች የሚያገኙዋቸው መልሶች የጥናቱን ውጤት የሚወስኑ በመሆናቸው ቀደም ተብለው ተመልሰዋል፤ መልሶቻቸውም እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

### 5.1.1. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር ቅድመ-ሁኔታዎችን በተመለከተ፣

#### 5.1.1.1. መርሀ-ትምህርቱ በሰነድነቱ ሲፈተሽ ለማን እንደተዘጋጀ አይጠቁምም፤

አዘጋጁ ክፍልም የሰጠው መረጃ ዝግጅቱ ለማን እንደሆነ አያመለክትም:: የቋንቋ መምህራንና የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችም ተመሳሳይ ሀሣብ ያቀርባሉ::

ከዚህም በላይ መርሀ-ትምህርቱ በዝግጅት ወቅት ካካተታቸው የትምህርት ዓላማዎች አንፃር የተቀረፁት ይዘቶች ከተቋማቱ ዓመታዊ ዕቅድና የተማ፡ው ማስታወሻ ጋር ሲገናዘቡ በጣም አጠቃላይነት እንዳላቸው የሰነድ ምርመራው ያመለክታል:: ከመምህራንና ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎች የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ሀሣብ ከመደገፋቸውም በላይ ዝግጅቱ የአንደኛ ሳይክል የአማርኛ መርሀ-ትምህርትን መሠረት ያላደረገና ያላገናዘበ መሆኑን ይጠቁማሉ:: ተማሪዎች ደግሞ በማስተማሪያ መፅሐፋ የቀረቡት ይዘቶች ከአቅማቸው በላይ እንደሆኑ የሰጡት አስተያየት ይገልፃል::

ስለዚህ መርሀ-ትምህርቱ ከፍላጎት አለሳ፣ ከሁለተኛ ቋንቋና በአጠቃላይ ከቋንቋ ትወራ አንፃር ግልፅነት ይጎድለዋል፤ በተጨማሪም ከአጠቃላይነቱ አኳዋይ ደግሞ በተቋም ለመተግበር አስቸጋሪነት እንዳለው የተሰበሰቡት መረጃዎች ያረጋግጣሉ::

#### 5.1.1.2. በመማር-ማስተማር ሁኔታው፣ የተማሪው ሰነድ ሲመረመር በምዕመላ መሥፈርቶች አፈፃፀም ላይ አንዳንድ ችግሮች እንዳሉ ይጠቁማል:: በምዕመላው ከተሳተፉት የትምህርት ባለሙያዎች የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ሀሣብ የሚደግፉ ናቸው::

መምህራን ደግሞ በአዲሱ መርሀ-ትምህርት አንፃር ትውውቅና ሙያዊ ሥልጠና እንዳልተሰጣቸው የሰጡት መረጃ ይጠቁማል። የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች፣ የርዕሰ-መምህራንና የክልል ሥርዓተ-ትምህርት በዚህ ላይ የሰጡት ሀሣብ ተመሳሳይነት አለው። በዚህ ምክንያት ከተማሪውና ከመምህሩ አንፃር የመማር-ማስተማር ሁኔታዎች ሲታዩ የተመቻቹ አለመሆናቸውን በቀረቡት መረጃዎች አማካኝነት ተረጋግጧል።

5.1.1.3. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር ከተዘጋጁት ማስተማሪያ መሣሪያዎች መካከል አገልግሎት ላይ የዋለው የተማሪው መፅሐፍ ብቻ ነው። ይህም ቢሆን የመርሀ-ትምህርቱ ቀጥተኛ ቅጅ በመሆኑ ችግሩ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ተመሳሳይ ነው። በተጨማሪ ይህም በቁጥር አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ተማሪውን በደንብ የሚያሳትፍ መልመጃ እንደሌለው ከሰነዱ፣ ከአዘጋጁ ክፍል፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ። የቀረበው መረጃ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተሟልተው አለመዘጋጀታቸውንና የተዘጋጁትም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ አለመሰራጨታቸውን ይጠቁማል።

በአጠቃላይ ሲታይ፣ መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር ቅድመ-ሁኔታዎች አለመመቻቸታቸው በመረጃዎች ተረጋግጧል።

5.1.2. መርሀ-ትምህርቱን ለመተግበር የክፍል ውስጥ ተራክቦን በተመለከተ፣

5.1.2.1. ከተማሪው መጠይቅ የተገኘው መረጃ ጥቅል አማካይ ውጤቱ (ነጥቡ) 3.9 የሚያሳይ በመሆኑ፣ ተማሪው ስለመርሀግብሩ ያለው ዝንባሌ፣ ፍላጎትና አመለካከት አዎንታዊ እንደሆነ ይጠቁማል። ከመምህራን፣ ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ከርዕሰ-መምህራን የተገኘው መረጃም ይህንኑ ይጠቅሳል። የመምህራኑም አዎንታዊ እንደሆነ ይገልፃል። እንደመረጃው ተማሪውና መምህሩ በቋንቋው፣ በቋንቋው ትምህርትና ባጠቃላይ በመርሀ-ግብሩ ላይ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው።

5.1.2.2. የክፍል ተራክቦን በተመለከተ፣ የተማሪው ተሳትፎ በመጠይቁ መረጃ መሠረት ጥቅል ነጥቡ 2.6፣ በክፍል ውስጥ ምልከታው ደግሞ 1.96 ያመላክታል። ሁለቱ ነጥቦች ተደጋጋፊነት ባይኖራቸውም፣ መጠይቁ በተሰጠበት በያንዳንዱ ክፍልና ጥያቄ አንፃር የተማሪው ተሳትፎ አማካዩ ነጥብ ከሁለት በታች በመሆኑ በተናጠል ከፍተኛ ልዩነት አሳይቷል። በዚህ ሁለቱ መሳሪያዎች መቀራረብን አሳይተዋል። የተማሪው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ደካማ እንደሆነም ይጠቁማሉ። ገምጋሚዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን ይህንኑ በሰጡት መረጃ ያረጋግጣሉ።

5.1.2.3. የመምህሩ በመማር-ማስተማር ሂደቱ የክፍል ተሳትፎ ደግሞ ከተማሪው መጠይቅ በተገኘው መረጃ 2.3 እና በምልከታው 1.87 ጥቅል አማካይ ነጥብ ያሳያል። ይህም ቢሆን እንደተማሪው ተሳትፎ መጠይቅ በተሰጠበት በያንዳንዱ ክፍልና ጥያቄ አንጻር የመምህሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ችግር ይታይበታል፤ በክፍል ውስጥ አብዛኛው ጊዜ የመምህሩ እንደሆነ መረጃው ያሳያል። መምህራን ራሳቸው፣ ገምጋሚዎቹ፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎቹና ርዕሰ-መምህራን ተመሳሳይ ሀሳብ ሰጥተዋል።

ስለዚህ በክፍል ውስጥ ተራክቦው የተማሪውና የመምህሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተመጣጣኝ አይደለም፤ ተማሪውም ሆነ መምህሩ ሚናውን አውቆ የተዘጋጀ አለመሆኑን መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ።

5.1.2.4. የተማሪው መጠይቅ ውጤት እንደሚያሳየው፣ በክፍል ውስጥ የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የልምምዶች አቀራረብ ጥቅል አማካይ ነጥብ 0.9 ሆኗል። ሆኖም መጠይቁ በተሰጠበት በያንዳንዱ ክፍልና ጥያቄ አንጻር ልዩነቶች ታይተዋል። ክንውን በጭራሽ የሌለበት ክፍል እንዳለም ተጠቁሟል፤ ታይቷል። ለዚህ እንደምክንያት የሚቀርበው ደግሞ የጊዜ ማጠር ሲሆን፣ ይህ ሊከሰት የቻለው ልዑ መምህራን በመጀመሪያ ደረጃ (አንደኛ ሳይክል) ትምህርት ቤቶች ለቅኝትና ለማስተማር ልምምድ የመውጣት ሁኔታ ነው ብለው መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን ይጠቁማሉ።

የቀረቡት ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት በክፍል ውስጥ ድርጊቶች፣ ክንውኖችና ልምምዶች በሥርዓት አልቀረቡም።

5.1.2.5. ከገምጋሚዎች፣ ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ከርዕሰ-መምህራን የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ ከሚናቸው አንጻር ተስማሚ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ ሲቀርቡ አልታዩም።

በጠቅላላው፣ መርሀ-ትምህርቱን ከመተግበር አንጻር ጥሩ የክፍል ውስጥ ተራክቦ እንዳልታየ መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ።

5.1.3. መርሀ-ትምህርቱን በመተግበር ረገድ ከሚገኘው ውጤት አንጻር፣

5.1.3.1. ተማሪው ምን ያህል በአስተሳሰብና በአሠራር ለውጥ እንዳመጣ የሚጠቁም ከተማሪው መጠይቅ መረጃ የተገኘው ጥቅል ውጤት 0.8 ያሳያል። ይህ መጠይቁ በተሰጠበት በያንዳንዱ ተቋም፣ ክፍልና ጥያቄ አንጻር ሲታይ፣ ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ መገመት ይቻላል። ሆኖም በተማሪው ላይ መጠነኛ ለውጥ እንዳለ ያመላክታል። መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ርዕሰ-መምህራን ይህንኑ ሀሳብ በሰጡት መረጃ

ይጠቁማሉ:: ስለዚህ መርሀ-ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር በተማሪው ላይ በአስተሳሰብና በአሰራር ሁለንተናዊ ለውጥ እንዳልታየ መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ::

5.1.3.2. በተቋሙ በተገኘው ውጤት 95% ተማሪው ከመቶ 55 በላይ ውጤት ወይም ከ'ሲ'(C) በላይ ውጤት እንዳለው መረጃው ያመለክታል:: ሆኖም የየተቋሙና የየመምህሩ የግምገማ ስልት፣ የመምህሩ የሥራ አፈፃፀም፣ የተማሪው ሁኔታና የየተቋሙ የውስጥ መመሪያዎች ሁሉ ተፅዕኖ ይህ ውጤት ሲገኝ እንዳቻለ ከመምህራን፣ ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ከርዕሰ-መምህራን የቀረቡ መረጃዎች ያረጋግጣሉ:: በዚህ ምክንያት የመርሀ-ትምህርቱ ዓላማ ግቡን መታ ለማለት እንደማያስችል መረጃዎቹ ይጠቁማሉ:: በጥቅሉ፣ በተማሪው ላይ የጎላ ለውጥ እንዳልታየና ዓላማውም ግቡን እንዳልመታ የቀረቡት መረጃዎች ይገልፃሉ::

መርሀ-ትምህርትን ከመተግበር አኳዋያ የቅድመ-ሁኔታዎች መመቻቸት ለክፍል ውስጥ ተራክቦው፣ የቅድመ-ሁኔታዎችና የክፍል ተራክቦው ጥሩ መሆን ደግሞ በውጤቱ ላይ አዎንታዊ አስተዋፅኦ አላቸው:: ከዚህም በላይ እነዚህ እርስበርሳቸው የተዛመዱና የተደጋገፉ ናቸው:: ይህም በስታቲስቲክስ ስሌት ቀመር መሠረት ሲታይ፣ ቅድመ-ሁኔታው እንጂ የክፍል ተራክቦው በተቋም ከተገኘው ውጤት ጋር ምንም ዝምድናና ድህረት አላሳየም፤ የስሌቱ ውጤትም ይህንኑ ያረጋግጣል::

በመጨረሻም፣ እስካሁን ከቀረቡት መረጃዎች አንፃር የጥናቱ ውጤት ሲታይ፣ የታቀደው ያማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት በሁለቱ ተቋማት፣ በተለይ በሦስቱ ክፍሎች በትክክል ተግባራዊ አልሆነም::

## 5.2. <u>አስተያየት</u>፣

በተሰበሰበው መረጃ በመመርኮዝ የሚከተሉት አስተያየቶች ተጠቁመዋል፤

5.2.1. ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የሚዘጋጅ የአማርኛ መርሀ-ትምህርት ለማን እንደሚዘጋጅ በፍላጎት አሰሳ ላይ የተመሠረተና ግልፅ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል::

5.2.2. ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የሚዘጋጅ የአማርኛ መርሀ-ትምህርት ለመተግበር የማያስቸግርና የአንደኛ ሳይክል የአማርኛ መርሀ-ትምህርትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት::

5.2.3. አንድ አዲስ መርሀ-ትምህርት ሲዘጋጅ ለመምህራን ትውውቅ ቢደረግና ሙያዊ ሥልጠና ቢሰጥ የሥልጠናው ሂደት ውጤታማ እንደሚሆን ይታመናል።

5.2.4. የተማሪው ምልመላ ወጥነት እንዲኖረው በተቋማቱ ሠራተኞች ምልመላው ቢካሄድ የመማሯን ሁኔታ ያመቻቻል ተብሎ ይገመታል።

5.2.5. አንድ አዲስ መርሀ-ትምህርት ሲዘጋጅ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተሟልተው ቢዘጋጁለትና በትክክል ቢሰራጩ፣ በዚህ በኩል የሚከሰቱት ችግሮች እንደሚቃለሉ ይታመናል።

5.2.6. በአንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የተማሪው ቅኝትና የማስተማር ልምምድ በመርሀ-ትምህርቱ በዕቅድ ደረጃ ተይዘው የክፍለ-ጊዜ ሥርጭት ቢሰጣቸው የማሠልጠኑን ሂደት ከጊዜ አንፃር የሚያመቻች ይመስላል።

5.2.7. ተቋማት ወጥ የሆነ የግምገማ ስልት ቢኖራቸው ይመረጣል።

5.2.8. አንድ መርሀ-ትምህርት በዕቅድ ደረጃ ነድፎ ውጤቱን ብቻ ከመጠባበቅ በሥራ ላይ መዋል መቻሉ ስለመቻሉን ተከታትሎ መገምገሙ ለመርሀ-ትምህርቱ መሻሻል የበለጠ ስለሚጠቅም አዘጋጁ ክፍል ቢያስብበት ይሻላል።

# ዋቢ ፅሑፎች (Bibliography)

## A. የእንግሊዝኛ ምንጮች።


Academy of Ethiopian Languages. 1996. Science and Technology Dictionary (English-Amharic). A.A. : Artistic Printing Press.

Allwright, Dick. 1988. Observation in Language Classroom. London: Longman group UK Ltd.

______.1991. Focus on Language Classroom : An Introduction to Classroom Research for Language Teachers. Cambridge : Cup.

Amdeselassie G/Kirkos. 1993. "Assessign The TTI Amharic Syllabus." AA: AAU (M.A. thesis).

Barnes, Douglas. 1982. Practical Curriculum Study. London: Routledge and Kegan Paul.

Becher, T. and Maclure, S. 1978. The Poletics of Curriculum Change. London : Hutchinson & Co. Ltd.

Bender, M.L., et al. (ed). 1976. Language in Ethiopia. London : OUP.

Best, Pon and others. 1988. Library Provision and Curriculum PlanningU : An Evaluation of ESSEX Secondary School Education. London : ESSEX.

Brandt, R.S. (ed). 1981. Applied Strategies for Curriculum Evaluation: Washington : Assoceation for Supervision and Curriculum Development.

Brown, H.D. 1994. Principles of Language Learning and Teaching. (3rd ed). Englewood Cliffs, New Jersey : Prentice Hall regents.

Celce - Murcia, M. 1991. Teaching English as a Second or Foreign Language. (2nd ed). Boston : Massachusetts Himle Pubs.

Cronbach, Lee J. 1983. "Course improvement through Evaluation." in Madaus Evaluation Models : View Points and Human Services in Evaluation. Boston: Kluwer Nijhoff Publishing.

**Division of Secondary Education, Ministry of Education and Fine Arts. 1964 E.C. Curriculum Policies and Standards, Teacher Training Institutes. A.A.**

**Doll, R.C. 1977. <u>Curriculum Improvement : Decision Making and Process.</u> (3rd ed). Boston : Allyn and Bacon, Inc.**

**Dubin, F. 1988. <u>The Roles of L2 Teachers, Learners and Materials Developers in the Context of New Technologies</u>. California : in Matters for Language Learning and Teaching; Anthropology Series 22.**

**Dubin, F. and Olsrtain, E. 1986. <u>Course Design Developing Programs and Materials for Language Learning</u>. Cambridge : CUP.**

**Dunkin, M.F. and Biddle, B.F. "A Model for Classroom Teaching." in Lee, Victor and Zeldin David. 1986 (ed). <u>Planning in the Curriculum</u>. London : Hodder and Stoughton.**

**<u>Evaluation of Education</u>. 1973. Educational Technology Series No.11. New Jersey : Englwood Cliffs.**

**Evans, W. and Berhamn E.H. 1977. <u>Strategy for Evaluating Implementation</u>. Curriculum. Studies. Vol.9, No.1, 75-80.**

**Flanders, N.A. 1970. <u>Analyzing Teaching Behavior</u>. Massachusetts : Addison-Wesley Pub. Camp.**

**Fullan, M.G. 1992. <u>The New Meaning of Educational Change</u>. (2nd ed). London : Cassell educational Ltd.**

**Getachew Endalemaw. 1994. "An Evaluation of the Lower Primary School Social Studies Syllabus." AA. : AAU (M.A. Thesis).**

**Giroux, H.A. and Others. 1981. <u>Curriculum and Instruction</u>. Berkeley : Mc. Cutchan Pub. Corporation.**

**Griessman, B.E. 1973. "An Approach to Evaluating Comprehensive Social Projects." in <u>Evaluation of Education</u>. Educational Technology Series No.11. New Jersey : Englwood Cliffs.**

**Guba, E.G. and Lincoln, Y.S. 1983. <u>Effective Evaluation</u>. (3rd ed). San Francisco : Jossey - Bass Inc.**

Hailu Dinku. 1991. "Assessment of Teachers' Performance in Curriculum Implementation." AA : AAU (M.A. Thesis).

Hammond, R. 1973. "Context Evaluation of Instruction in Local School Districts." in Evaluation of Education. Educational Technology Series No.11. New Jersey : Englwood Cliffs.

Harmer, J. 1991. The Practice of English Language Teaching. London: Neil and Comp. Ltd.

Hawes, H. 1979. Curriculum and Reality in African Primary Schools. Singapore : Longman group Ltd.

Hinkle, D.E. and Others. 1994. Applied Statistics for the Behavioral Science. (3rd ed). Boston : Honghton Mifflin Campany.

Holden, Susan. 1979(ed). Teacher Training. Hong Kong. ME Pub. Ltd.

Holt, M. 1978. The Common Curriculum. London : Routledge and Kegan Paul.

Jacobsen, D.E.P. and Kauchek, D. 1989. Metheods for Teaching : A Skills Approach. (3rd ed). New Jersey : Mac Millan Pub. Compan.

Johnson, R.K. 1989. The Second Language Curriculum. Cambridge: Cup.

Lewy, A. 1977 (ed). Hand Book of Curriculum Evaluation. New York: Longman Inc.

Madaus, G.F. and Others. 1983. Evaluation Models : View Points on Educational and Human Services Evaluation. Boston : Kluwer Nijhoff Pub.

Mager, R.F. 1991. Making Instruction Work. London : Kogan Page Ltd.

Malamah, T.A. 1991. Classroom Intraction (3rd ed). Oxford : Oup.

Marsh, C. and Morris, P. 1991. Curriculum Development in East Asia. London : The Falmer Press.

**Mc Cargar, D.F. 1993. The Teacher and Student Role Expectation : Cross-Cultural Differences and Implications. Modern Language Journal, Vol.77. No.ii.**

**Mellese Bedane. 1992. "An Evaluation of grades 9-12 English Curriculum and its implementation in Schools at Capitals of Ethiopian Administrative Regions As Causes for Students' deficiency in English." AA : AAU (M.A. Thesis).**

**Nunan, D. 1988. The learner-Centered Curriculum : A Study in Second Language Teaching. Cambridge : Cup.**

**_____ 1989. Syllabus Design. Oxford : Oup.**

**_____ 1991. Language Teaching Methodology. New York : Pretice Hall.**

**Oliva, P.F. 1988. Developing the Curriculum (2nd ed). London : Scott, Foresman and Company.**

**Ornstien A. C. and Huinkins, F.P. 1988. Curriculum Foundations, Principles and Issues. New Jersey : Prentice Hall.**

**Pankhurst, E.S. 1955. A Cultural Histrory. ESSEX : Lalibela House.**

**Payne, D.A. 1974. Curriculum Evaluation Commentaries on Purpose, Process and Product. Toronto : D.C. Health and Camp.**

**Posner, G.J. 1992. Analyzing the Curriculum. New York : Mc. Graw-Hill, Inc.**

**Pratt, D. 1980. Curriculum : Design and Development. New York: Harconrt Brace Jovanovich, Pubs.**

**Provus, M. 1973 "Educational Technology Research." in Evaluation of Education. Educational Technology Series No.11. New Jersey : Englwood Cliff.**

**Richards, J.C. 1985. The Context of Language Teaching. Cambridge: Cup.**

**_____ 1990. The Language Teaching Matrix. Cambridge : Cup.**

**Richards, J.C. and Nunan, D. 1990. Second Language Teacher Education. Cambridge : Cup.**

**Richards J.C. and Rodgers, J. 1982. Method : Approach, Design and Procedure. TESOL Quarterly Vol.16, No.2.**

**____________________ 1986. Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge : Cup.**

**Rossner, R. and Bolitto, R. 1990. Currents of Changes in English Language Teaching. Oxford : Oup.**

**Russell, J. and Latchman, J. 1979 (ed). Curriculum Development in Further Education. (3rd ed). Bristol : The Further education Staff College.**

**Salia-Bao, K. 1987. An Introduction to Curriculum Studies in Africa. London : Mac Millan Pub. Ltd.**

**Saylor and Others. 1981. Curriculum Planning for better Teaching and Learning. New York : Holt Rinchart Winston.**

**Scriven, M.C. 1991. Evaluation Thesaurus. (3rd ed). California : Edge Press.**

**Stufflebeam, D.L. "Towards Science of educational Evaluation." in Evaluation of Education. 1973. USA : ETR Series No.11.**

**Stake, R.E. 1967. "The Contenance of educational Evaluation." Teacher College Record, Vol. 68, No.7.**

**Stenhouse, L. 1975. An Introduction to Curriculum Research and Development. London : Routledge and Kegan Paul Ltd.**

**Stern, H.H. 1983. Fundamental Concepts of Languege Learning and Teaching. Oxford : Oup.**

**Strevens, P. 1983. New Orientations in the teaching of English. Oxford Oup.**

**Tyler, R.W. 1949. Basic Principles of Curriculum and Instruction. Chicago : Cup.**

**Urevb, A.O. 1985. Curriculum Studies. Syngapore : Longman group.**

**Wallace, M.J. 1991. Training Foreign Language Teachers. Cambridge : Cup.**

Wright, T. 1987. Roles of Teachers and Learners. Oxford : OUP.

## B. የአማርኛ ምንጮች

ትምህርት ሚኒስቴር:: 1985:: በብሔረሰብ ቋንቋዎች መደበኛ ትምህርት ለመስጠት ከሽግግር መንግሥት የተሠጠ ውሳኔ:: ከትምህርት ዓለም፣ በሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት የሚዘጋጅ:: አዲስ አበባ፤ በት.መ.ማ.ማ.ድ.::

______________ 1986:: «የትምህርት አጀማመር በኢትዮጵያ» ከትምህርት ዓለም፣ አዲስ አበባ፤ በት.መ.ማ.ማ.ድ. ::

ሥርዓተ-ትምህርት:: 1987:: ከአዲሱ አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ አኩዋያ የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1ኛ-4ኛ) ክፍሎች ለሚያስተምሩ መምህራን የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት (ያልታተመ)::

______________ :: 1987:: የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን መምህራን ማሠልጠኛ መፅሐፍ (ያልታተመና ለሙከራ የቀረበ)::

አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ:: 1986:: የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት:: አዲስ አበባ፤ (ያልታተመ)::

አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ:: 1985:: በሽግግር መንግሥት:: የጠ/ሚ/ጽ/ቤት የማህበራዊና አስተዳደር ጉዳይ ዘርፍ:: አዲስ አበባ፤(ያልታተመ)::

የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ:: 1986:: አዲስ አበባ፤ በት.መ.ማ.ማ.ድ.::

ጌታቸው ገብረፃድቅ:: 1986:: ነባሩን ሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ከአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ አኩዋያ አሻሽሎ ለማዘጋጀት ምን መደረግ አለበት? (ያልታተመና ለውይይት የቀረበ)::

## አባሪ ሀ፣ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

### የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፍ ክፍል

### የድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

በ1990 ዓ.ም. በአርባ ምንጭና በአዋሳ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም በመሰልጠን ላይ ባሉ ዕጩ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ፦

የተከበራችሁ ዕጩ መምህራን፡

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ፡ በ1987 ዓ.ም. ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት (ሲለበስ) ከተዘጋጀለት ስነ-ዘዴ አኳያ ሲተገበር (በሥራ ላይ ሲውል) ያጋጠሙትን ችግሮች መርምሮ መፍትሄ ኃሳብ ለመጠቆም ለተዘጋጀው ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው። ከጥናቱ ገንቢ አስተያየት እንዲገኝ ጥያቄዎቹን በግልፅነት እንድትመልሱለት አጥኚው በትህትና እየጠየቀ ለመልካም ትብብራችሁ በቅድሚያ ያመሰግናችኋል።

ማሳሰቢያ፡-

1. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም።
2. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው።
3. ለጥናቱ ውጤታማነት የናንተ ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ስለሚታመን ትክክለኛ መረጃ መስጠት ከያንዳንዳችሁ ይጠበቃል።

**<u>ክፍል አንድ</u>፥** ከዚህ በታች የተተውቱትን ባዶ ቦታዎች በመሙላት ለተጠየቁት መረጃዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ(ጪ)።

1. ፆታ_____ ዕድሜ _____ የአፍ መፍቻ ቋንቋ_______________
2. አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰብህ(ሽ) ጋር የምትጠቀም(ሚ)በት ቋንቋ_______________
3. አብዛኛውን ጊዜ ከጓደኛህ(ሽ) ጋር ለጨዋታ የምትጠቀም(ሚ)በት ቋንቋ _______________
4. አብዛኛውን ጊዜ ከአካባቢህ(ሽ) ጋር የምትግባባ(ቢ)በት ቋንቋ _______________
5. 12ኛ ክፍልን የጨረስክ(ሽ)በት ዓመተ ምህረት _______________
6. የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤት ለማሻሻል ፈተናውን ለስንት ጊዜ ተቀበልክ (ሽ)? ዓመተ ምህረቱንም ጥቀስ(ሽ)። _______________
7. 12ኛ ክፍልን ከጨረስክ(ሽ) በኋላ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም እስከገባህ(ሽ) ድረስ ምን ትሰራ(ሪ) ነበር? የሥራውን ዓይነት ግለጽ (ጪ)።_______________
_______________
8. መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ከመግባትህ (ሽ) በፊት በትምህርትም ሆነ በሌላ ሥራ መስክ ስልጠና የወሰድክ(ሽ)ው ካለ ጥቀስ (ሺ)።_______________
_______________

**<u>ክፍል ሁለት</u>፥** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ከመረጥክ(ሽ) በኋላ ከሰንጠረዡ ላይ የመረጥክ(ሽ)ውን ሣጥን ይዟል ከምትለ(ዪ)ው ሆሄ ሥር የ(X) ምልክት አድርግ (ጊ)።

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ መ. ዝቅተኛ
ለ. ከፍተኛ ሠ. በጣም ዝቅተኛ

| | | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያለህ(ሽ) አዎንታዊ አመለካከት፥ | | | | | |
| 2. | በአማርኛ ቋንቋ ለመገልገል ያለህ(ሽ) ፍላጎት | | | | | |
| 3. | የአማርኛ ቋንቋን የአነጋገር ዘይቤ የማድነቅ ስሜት | | | | | |
| 4. | የአማርኛ ቋንቋ መምህር ለመሆን ያለህ(ሽ) ፍላጎት | | | | | |
| 5. | በአማርኛ ቋንቋ አስተማሪህ(ሽ) ላይ ያለህ(ሽ) አዎንታዊ አመለካከትና ግምት | | | | | |
| 6. | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለህ(ሽ) አዎንታዊ አመለካከት | | | | | |
| 7. | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ለሚደረጉ ክንውኖች ያለህ(ሽ) ግምትና የመውደድ ስሜት | | | | | |
| 8. | በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለህ(ሽ) አዎንታዊ አመለካከትና ግምት | | | | | |

ክፍል ሶስት፦ ሀ. ከዚህ በታች የአማርኛን ትምህርት በሚመለከት የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴን የሚያመለክቱ ዐረፍተ-ነገሮች ከ1-14 ቀርበዋል። በቀረቡት የክንውን ዓይነቶች ምን ያህል እንደተሳተፍክ(ሽ) ከተሰጡት አማራጮች መርጠህ(ሽ) ከሠንጠረዡ ላይ የመረጥከ(ሽ)ውን ትክክለኛ መልስ ይዟል ከምትለ(ዪ)ው ሆሄ ሥር የ (X) ምልክት አድርግ(ጊ)።

ሀ. ሁልጊዜ ሐ. በመጠኑ መ. አንዳንድ ጊዜ

ለ. ብዙ ጊዜ ሠ. በጭራሽ አላደርግም

| | | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ክፍል ውስጥ | | | | | | |
| 1. | የመምህሩን ገለጻ በትኩረት አዳምጣለሁ። | | | | | |
| 2. | በመምህሩ ክንውን ላይ አተኩራለሁ /አተኩሬ እመለከታለሁ/። | | | | | |
| 3. | መምህሩ በሚያቀርቡት ገለጻና ክንውን ማስታወሻ እወስዳለሁ። | | | | | |
| 4. | ያልገባኝን ሁሉ በቃል እጠይቃለሁ። | | | | | |
| 5. | የሚቀርበውን የቃል ጥያቄ ሁሉ ለመመለስ እሞክራለሁ። | | | | | |
| 6. | ንቁ ተሳታፊ ሆኜ ክፍለ ጊዜውን ለቋንቋ ትምህርት ብቻ እጠቀማለሁ። | | | | | |
| 7. | ነፃ መድረክ ሳገኝ የራሴን ቀልዶች፣ ጭውውቶች፣ ወዘተ በንግግር ለክፍሉ አቀርባለሁ። | | | | | |
